

"የቤተክህነት ኃላፊዎች የሚያመልኩት ሥርዓቱን ነው"

"በተጠና ሁኔታ የዘር ማጥፋት ዘመቻ እየተካሄደ ነው"

"አሁንም ድንበር እየተገፋ መሬታችን ለሱዳን እየተሠጠ ነው"

አባ ገብረየሱስ ኪዳነ ማሪያምና አባ ገብረስላሴ ወልደኃይማኖት

"አሸባሪ አላየሁም ፤ ወደ ሽብር የሚገፉ መከራዎች ግን ብዙ ናቸው"

ዘላለም ወርቅአገኘሁ

"ሕዝባዊ ሲኖዶስ ሊቋቋም ይገባል"

ዘሪሁን ሙላቱ (ዶ/ር)

መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 6 ግንቦት 2010 ዓ.ም

ዋጋ 14.99



## ወልቃይትን እንደ ካሽሚር

ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ



## ‹‹ቤተሠቤ በትግል የተፈጠረ፤ ለትግል የሚኖር ነው››

ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ (ከአሜሪካ)

## የአማራ ምሁራንና ብአዴን ከጣውንትነት ወደየት?

ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)

ግዮን

ቅጽ 1 ቁጥር 6 ቅዳሜ ግንቦት 04 2010 ዓ.ም



**ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ
ግንቦት 18
ይጠብቁን!**




**ቁጥር 5 ዕትም**


# 26 “ሕዝባዊ ሲኖዶስ ሊቋቋም ይገባል”

ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
የጥንታውያን ቋንቋዎችና
ጽሑፎች ተመራማሪ

20 የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፋሽስት ለተፈጸመባት ግፍና ጭፍጨፋ ፤ የጣሊያን መንግሥት ይቅርታ ሊጠይቅና ካሣ ሊክስ ይገባዋል!

ተረፈ ወርቁ



2 ወልቃይትን እንደ ካሽሚር

ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ

6 ኢህአዴግ እና የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ የቁልቁለት ጉዞ

8 <<ቤተሠቤ በትግል የተፈጠረ፤ ለትግል የሚኖር ነው>>
እስክንድር ነጋ(ከአሜሪካ)

10 የአማራ ምሁራንና ብአዴን ከጣውንትነት ወደየት?

ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)

12 ግንቦት ወር በታሪክ ውስጥ


13 ከአርበኛው ጋር በአርበኞች ቀን

በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

14 የሃሳብ ልዩነት ይውደም¡¡¡

ሁሴን ከድር

16 “የቤተክህነት ኃላፊዎች የሚያመልኩት ሥርዓቱን ነው”



አባ ገብረየሱስ ኪዳነ ማሪያምና
አባ ገብረስላሴ ወልደኃይማኖት

24 ከ82 ዓመት በፊት የኢጣሊያ ወረራ ዋዜማ ጃፓን እንደ ምክንያት

ብሩክ መኮንን

28 “አሸባሪ አላየሁም፤ ወ ደ ሽብር የሚገፉ መከራዎች ግን ብዙ ናቸው”



ዘላለም ወርቅአገኘሁ

31 መገናኛ ብዙኃን የገነቡት "ያልተገነባው የኢትዮጵያ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ"

32 <<ወደ ከፍታ ለመድረስ የጀመርኩት ጉዞ አይቆምም!>>
አባይነሽ ጀምበር

# ወልቃይት እንደ ካሽሚር

## ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ

*የወልቃይት መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴዎች እና የዋልድባ መነኮሳትን ጨምሮ ከመቶ በላይ ከእስር ቤት የተለቀቁ የዲሞክራሲና የፍትህ ተቆርቋሪ ታጋዮች በታሪካዊቷ ጎንደር ከተማ ግንቦት 2 ቀን 2010 ዓ.ም በተደረገላቸው የክብር እራት ግብዣ ላይ የተገኘው ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ለታዳሚው ያደረገውን ንግግር ለአንባብያን እንደወረደ በሚከተለው መንገድ አቅርብነዋል:: በዕለቱም ለህሊናህ እስረኞች የተለያየ ስጦታም እንደተበረከተ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል::*

እዚህ የተሰበሰባችሁ ታላላቆቼም፣ ታናናሾቼም በመጀመሪያ እንኳን ለዚህ ዕለት አበቃችሁ፤ አበቃን:: በተለይም ባለፉት ሁለት አስርታት የወልቃይትን ሕዝብ የማንነት፣ የፍትሕ፣ የዴሞክራሲ እና የፖለቲካ ጥያቄ አደባባይ እንዲወጣ በተወለዳችሁበት አፈር ላይ ተተክላችሁ ለከፈላችሁት ውድ ዋጋ ጥልቅ አክብሮቴን ለመግለጽ እፈልጋለሁ:: ከዚህ በኋላም ለሚመጡ ተጋፋጮች እናንተ መልካም ምሳሌ ናችሁ እና:: እንደ ጋሽ ሲሳይ ታከለ እና ጎቤ መልኬ (ዋዋ) የመሳሰሉ ሰማዕታትንም ታሪክ ለዘንተ ዓለም እንደሚዘክራችሁ አምናለሁ:: በተጨማሪም፤ የጎንደር እናቶች የደርግ የቀይ ሽብር ጭፍጨፋ ያሳረፈባቸው መጥፎ ጠባሳ ሳይበግራቸው፤ ከአርባ ዓመታት በኋላ በጃን ተከል ዋርካ ሥር የተሰባሰቡ የሕዝባዊ እምቢተኝነት አራማጆችን፣ የውሃ ጥም ለማርካት ከእንስራዎቻቸው ቀድተው በማጠጣት አጋርነታቸውን ያስመሰከሩበትን ላቅ ያለ አበርክቶት እስር ቤት ሆኜ ስሰማ ያሳደረብኝን ሐሴት ቃላት አይገልጸውም:: በትግሉ ተዋፅዖም የሴቶች ተሳትፎ አናሳ በሆነበት አውድ የእነዚህ እናቶችና ለዕድሜ አቻዎቿ ዓርአያ መሆን የቻለችው የንግሥት ይርጋ ጀግንነትም ከፍ ያለ ዋጋ እንዳለው አይካድም:: ጎንደርም ከመካከለኛው ዘመን የስልጣኔ እምብርትነት በዘለለ፣ የ21ኛው ክፍለ-ዘመን የፀረ-ጭቆና ብርሃን ፈልቃቂ ከተማ የመሆኗን ጉዳይ ባለፉት ሁለት ዓመት ያየነው ሃቅ ይመሰክራል:: በዚህ አጀንዳ ላይ ያለኝን አጭር አስተያየት ከማቅረቤ በፊት፤ ከወልቃይት የማንነት ጥያቄ ጋር ተያይዞ ባለፉት አርባ ዓመታት በግፈኛው ሥርዓት ሕይወታቸው ላለፈ ወገኖቻችን የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት እንድናደርግ በትህትና እጠይቃለሁ:: .....አመሰግናለሁ::

ዛሬ በመላ ሀገሪቱ ለተከሰቱና ለመከሰትም እያንዣበቡ ላሉ ምስቅልቅሎሽና ግጭቶች አንደኛ ተከሳሽ የሆነው ከደደቢት የተነሳው ዘውገኛ ብረት-ነካሽ የጠዋት ማኒፌስቶ በግላጭ እንደሚነግረን "ነጻ የትግራይ ሪፐብሊክ"ን በመመስረት ቅዠት መለከፉን ነው:: ግና፤ በወቅቱ ቅዠቱን ለማስፈጸም የሚችልባቸው "ደጋፊ-አቃፊ ሁኔታዎች" ስላልተሟሉ፣ ስልታዊ የአቋም ለውጥ አድርጎ፣ የትግሉን አጀንዳ በ"ብሔር-ጭቆና" ስም በመጥለፍ አያሌ ሀገራዊ ጥቅሞቻችንን ለምዕራባውያንና ለአረብ ሀገራት ጭምር በመስዋዕትነት አቅርቦ ለስልጣን በቅቷል:: ወያኔ የነጻ መንግስት ጥያቄውን ለጊዜው መሳቢያ ውስጥ ቢከተውም፤ ለግንጠላ ያዘጋጀውን የበረሃ ካርታ ግን ከመተግበር ያገደው አንዳችም ኃይል አልነበረም:: በዚህ ምክንያትም ከጎንደር እና ከወሎ ግዛቶች የተነጠቁ በርካታ መሬቶችን "እወክለዋለሁ" ለሚለው ማሕበረሰብ እንደ አንባሻ ሸንሽኖ ማከፋፈሉን ሁላችንም የምናውቀው ሐቅ ነው::

የሆነው ሆኖ በሽፍታ-መራሹ ስብስብ የተጫረው "ወያኔያዊ አብዮት" ሁለት-ግቦችን በአምድነት የተሸከመ ሲሆን፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ፤ ግዛት ማስፋፋትን ታሳቢ አድርጎ ባካሄደው ሥር-ነቀል አብዮት የትግራይን ወሰን ተሻግሮ በጠብ-መንጃ ወርሮ በያዛቸው ግዛቶች ነባሩን ማሕበራዊ መዋቅር አፈራርሶ በአዲስ ተክቷል፤ የማሕበረሰቡን ርዕዮተ-ዓለማዊ ምልከታንም በዓይነቱ አዲስ በሆነ ገዥ-ሃሳብ ቀይሯል:: ሌሎች ስር-ነቀል እርምጃዎችንም ወስዷል:: እነሆም በዚህ መልኩ ወደ መሬት ያወረደውን ደም-የጠገበ ፖሊሲን ነው የ"ታሪክ ማስረጃ" እያለ ረብ-የለሽ ሙግት አንስቶ የሚያነታርከን::

የሶሻል ሳይንስ ምሁራን ትንታኔ እንደሚያፍታታው "የዛሬ ፖለቲካ የነገ ታሪክ ነው::" በዚህ ሥነ-አመክንዮ መሰረትም፣ ትላንት የተጭበረበረ ፖለቲካ፣ ዛሬ ወደ ታሪክነት ሲቀየር የተጭበረበረ ከመሆን የሚያነጻው አንዳችም የንስሃ ዘይት አለመኖሩን እንረዳለን:: ነገር ግን አበው "የሌባ አይነ ደረቅ..." እንዲሉ፤ ወያኔና የጥቅም ተጋሪዎቹ ይህንን የትላንት ብላሽ ፖለቲካ የአባቶቻቸው እውነተኛ ታሪክ አድርገው ከመውሰዳቸውም ባለፈ፤ አካባቢው "የትግራይ ማህበረሰብ ይዞታ ነው" ለሚሉት ሙግት በማስረጃነት በማቅረብ እኛም አምነነን እንድንቀበል ለመጋት ሲዳዳቸው በትዝብት እየተመለከትን ነው:: መላው ኢትዮጵያዊ እውነቱን እንዳያውቅ የወያኔ ግርዶሽ የጨለማ ምርጊት ሆኖበታል:: የመቀሌ ዩንቨርሲቲን የመሰለ ወገንተኛ ተቋም አሁንም "የሸዋ የበላይነት ሊመጣ ነው!" የሚሉ ትርኪ ምርኪ ጥናቶችን በቅምጥ ምሁራን እያዘጋጀ ህዝባዊ ትግሉን ለማደናቀፍ እየሞከረ ነው:: እዚህ ጋ መዘንጋት የሌለበት ቁም ነገር፤ የወልቃይትና አዋሳኝ መሬቶች በድህረ የካቲት አብዮት ለተነሱ የሽምቅ ተዋጊዎች ሁሉ ዋነኛ መፋለሚያ መድረክ ሆኖ በመቆየቱ መረጃዎች በቃጠሎ፣ በዘረፋ፣ በመበላሸት እና በመሳሰሉት መንገዶች የመጥፋት እድላቸው ሰፊ መሆኑን ለመገንዘብ የጥናት ሪፖርት መጠበቅ አያሻንም:: ስለዚህም በዘመናዊ ዓለም መሠል ግጭቶች በሚፈታበት ህዝበ ውሳኔ (የሪፈረንደም ጽንሰ ሀሳብ) የወልቃይትም ጉዳይ እንዲበየንበት መገፋፋት ካስነዋሪ የሕወሓት ቧልትነት ያለፈ ፋይዳ የለውም:: ምናልባትም 'በጠብ-መንጃ ክምችት እና በሰራዊት ብዛት የትኛውንም ህጋዊ ጥያቄ እየደፈቅን ለዘላቂው እንቆያለን' የሚል መታበይ ከተጣባቸውም የታሪክ ድርሳናትን ጠንቅቀው እንዲያነቡ እንመክራለን:: "ዓለምን ከእግሬ ጫማ በታች አሳድራታለሁ" እያለ መቄዶኒያን በሽለላ ሲያርዳት የነበረው ታላቁ እስክንድርም ወድቋል:: ለጀግንነቱም ሆነ ለብልህነቱ ወደር ያልተገኘለት ናፖሊዮን ቦናፓርቲም ተሸንፏል:: አውሮፓን በብረት መዳፉ የጨበጠው አዶልፍ ሂትለርም የማታ ማታ የውርደትን ጽዋ ተጎንጭቷል:: ክንደ ብርቱው መንግስቱ ኃይለማርያም ለአሳፋሪ ስደት ተዳርጓል:: እውነት እውነት እላችኋለሁም የወያኔ መዘባበትና ዕብሪትም ከዚህ የተለየ ዕጣ ፈንታ ሊገጥመው አይችልም::

የወያኔ ሁለተኛው አብዮት ዕቅድ፤ መዳረሻውን ምኒልክ ቤተ-መንግስት በማድረግ በተቀረው የሀገሪቱ አካባቢ የአዛዥ ናዛዥ ሚና እንዲኖረው የሚያስችሉትን ሁለት መላዎችን ዘይዶ ያስፈፀመበትን እናገኛለን:: የመጀመሪያው፤ በመናኛ ሀሳብ ቡትቶ ፌዴራሊዝም ማንበር ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ፤ በሁሉም ክልሎች የአሻንጉሊት አስተዳደር መመስረትን ግቡ ያደረገ ነው:: ሙሉ በሙሉም ተሳክቶለታል::

## በግልባጩ እንደ ከዚህ ቀደሙ በወያኔ ጥላ ስር እዝናናለሁ የሚል ከሆነ ባለፉት ሦስት ዓመታት ከፊል ክልሉን የነቀነቀው ህዝባዊ ቁጣ ክሽፈቱን አርሞ፣ ኃይሉን በብዙ እጥፍ አግዝፎ እየመጣ ነውና አንገቱን ለጊሎትን ማሽን ከማዘጋጀት ውጭ አማራጭ እንደማይኖረው ከወዲሁ አምኖ መቀበል አለበት



ቢሮክራሲውን፣ ኢኮኖሚውን፣ ሠራዊቱን፣ ደህንነቱን በስግብግብነትና በዓይን አውጣነት ጠቅልሎ ይዟል:: ይህን ዕኩይ ሴራ ለማስፈፀም መደላድል ይሆናሉ ተብለው ቡራኬ ከተቀበሉ ድርጅቶች መካከልም ብአዴን በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል:: አብዛኛው የድርጅቱ አመራርም ከኤርትራና ትግራይ ቤተሰብ የተገኘ ቢሆንም የጎጃሜውን ገብሩ አስራትና የወለየውን ሳዕረ መኮንንን ፈለግ በመከተል ለወጣበት ማህበረሰብ ከመታመን ይልቅ ለደደቢት ፍሬዎች በመንገድ መሪነት አገልግሏል:: እያገለገለም ነው:: በወረራ የተያዙት መሬቶች ጥንትም የትግራይ ለመሆናቸው ለሚቀርቡት የኑፋቄ ሐቲት በደቀ መዛሙርትነትም ተሰልፎ በሰሚ አልባ ጩኸቱ አደንቁሮናል:: በግብረ-አበርነት በመሳተፍም የወልቃይትና የአካባቢው ነባሩ ማህበረሰብ የጅምላ ፍጅትና ሰንፋጭ ጭቆና እንዲፈፀምበት አድርጓል::

ለዚህም ነው ብአዴን በትጉኃን የህዝብ ልጆች ቁጥጥር ስር መዋል አለበት የምንለው:: በነገራችን ላይ ዘግናኙ ጭፍጨፋ ልባችንን በሀዘን ቢሰብረውም ደመ ቁጡ ወጣቶች ትግሉን እንዲቀላቀሉ ገፊ ምክንያት በመሆኑ ደግሞ እንፅናናለን:: ከሞላ ጎደልም እንደ ተድላ ባይሩ እና ዋቆ ጉቱ ሁሉ እነ ኮሎኔል ደመቀ ዘውዴ፣ አታላይ ዛፌ፣ መብራቱ ጌታሁን እና መሰል ብርቱ ጓዶችን እየፈጠረ እንደሆነ በዓይናችን ተመልክተናል:: እናንተ ዐውደ ብርሀንን የተጎናፀፋችሁ ጀግኖችም በጨለማው ላይ እንደምትሰለጥኑም አምናለሁ:: በአናቱ በወልቃይት ጉዳይ እናንተ የመጨረሻዎቹ ታጋዮች ትሆኑ ዘንድ የፍትህና ዴሞክራሲ ወገን ሁሉ ከጎናችሁ እንዲቆም መወትወት አለባችሁ::

በጥቅሉ የወያኔና ደጋፊዎቹ ማንአህሎኝነት፣ መዘባነን፣ የፖለቲካ መሰሪነትን በጥልቅ ሀዘን ስናስተውል ኧረ ለመሆኑ በወልቃይት ጥያቄ ላይ ጉጅሌው ቡድን እንዲህ እንዲሳለቅ "ሊቼንሳ" የሰጠው ማነው? ስንል አጥብቀን እንጠይቃለን:: እዚህ ጋ ሳልጠቅስ የማላልፈው ከቀይ ሽብርም የከፋ ግፍ በአካባቢው ተወላጆች ላይ መፈፀሙ የማይስተባበል ዕውነታ ነው:: በደጉ ቀይ ሽብር ዘመን የጥቃት ዒላማ የፖለቲካ አቋምን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን የወልቃይት ግን ማንነትን ተንተርሶ የተፈፀመ የዘር ማፅዳት ወንጀል ነው::

በመጪዎቹ ጥቂት ወራትም ይህንን ጉዳይ በሠላማዊ መንገድ፣ በህጋዊ እና በቅንነት መፍታቱ በዜጎች ማህበራዊ ግንኙነትም ሆነ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሊከሰት የሚችለውን ጽንፈኝነትና በጦር ሜዳ መሸናነፍ ላይ ማዘንበልን ይታደጋል ብዬ አምናለሁ:: ሂደቱ ያለ ግጭት እንዲያልቅ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለማፍያውና አፋኙ ሕወሓት የጎን ውጋት መሆን እንዳለበትም ለማስታወስ እወዳለሁ:: ጊዜው የህግ እንጂ የውንብድና መሆኑ አንድ ቦታ ላይ መቆም አለበት:: በተቀረ ጥያቄውን በተለመደው መንገድ እወጣዋለሁ የሚለው ሕወሓታዊው ዕብሪት ለሕንድ እና ለፓኪስታን ዛሬም ድረስ ራስ ምታት የሆነችውን "የካሽሚር ግዛት" ክሱት እንዳደረገው ሁሉ፤ እዚሁ ዓይናችን ሥርም "ጥቁሯን ካሽሚር" ማዋለዱ አይቀሬ መሆኑን ለመናገር የነብይነት ፀጋን አይጠይቅም:: "ጭቆና ቀቢፀ ተስፋን ያስፋፋል" የሚሉ ጸሐፍትም ከግዙፉ የአመድ ክምር ስር ፍም-ረመጥ የሚፈለቅቅ ሞት አይፈሬ ትውልድ ለመምጣቱ ምልክቶቹን እንዲያስተውሉ እመክራለሁ::

እናም በዋናነት ትግርኛ ተናጋሪውን ጨምሮ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከግፉአን ጎን መቆም እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተን እንናገራለን:: ይህንን ጥያቄ ወደ አደባባይ ማምጣቱ የማህበረሰብን ኅልውና ያናጋል የሚለው ሙግትም ጊዜ ያለፈበት መድህኒት ነው፤ የሚገድል እንጂ የማያሽር:: የተማረው መደብም ምሁራዊ አይናፋርነቱን ገትቶ የመፍትሔ ሀሳቦችን ሊጠቁሙ የሚችሉ ስራዎች ላይ ማተኮር እንደሚኖርበት እናሳስባለን:: ልሂቃኑም የሕሊና ፍርድ ሊሰጡ ግድ ይላቸዋል:: ከሁሉም በላይ ግን ብአዴን የተባለው የክልሉ አስተዳዳሪ "መልከ ሕወሓት" ጭምብሉን አውልቆ በመጣል የጥያቄው ባለቤት ሊሆን እንደሚገባው ነጋሪ መፈለግ የለበትም እንላለን::

በግልባጩ እንደ ከዚህ ቀደሙ በወያኔ ጥላ ስር እዝናናለሁ የሚል ከሆነ ባለፉት ሦስት ዓመታት ከፊል ክልሉን የነቀነቀው ህዝባዊ ቁጣ ክሽፈቱን አርሞ፣ ኃይሉን በብዙ እጥፍ አግዝፎ እየመጣ ነውና አንገቱን ለጊሎትን ማሽን ከማዘጋጀት ውጭ አማራጭ እንደማይኖረው ከወዲሁ አምኖ መቀበል አለበት:: ስለምን ቢሉ በእንዲህ አይነቱ የህዝብ ፍርድ የዘረፋና የጭቆና ሀሳብ አመንጪው ሕወሓት ብቻ ሳይሆን፤ ተባባሪው ብአዴንም ከታዳኝነት አያመልጥምና ነው:: ነገር ግን እንደ ኦህዴድ ጓዶቹ የራሱን ህዝብ በምርኩዝነት ተጠቅሞ ጥያቄውን ከማስፈፀም ባሻገር ቅጥ ያጣውን አፈና፣ እስር፣ ግድያ፣ መሬትን ጨምሮ ሁለንተናዊ ንብረት ነጠቃን የማስቆም ሽራፊ ወኔ ካለው ያን ያህል አዳጋች እንደማይሆንበት የማህበረሰቡን መነቃቃት ጠቅሰን እናስገነዝባለን:: በአናቱም የጭቆናውን ቀንበር የማላላት፣ የብዝበዛውን ሸክም የማቅለል፣ ፖለቲካዊ ኃላፊነቶቹን መዘንጋት የለበትም:: ከዚህ በኋላ በእንዲህ ዓይነት ጉዳይ መሞት-ካለመሞት፤ መታሰር-ካለመታሰር የሚኖርበት ግብር ሰብሳቢው፣ ሀብት አስተዳዳሪው፣ በስልጣን ተምነሽናሺው… ብአዴን ብቻ መሆኑን ለማስታወስ እወዳለሁ:: በመጨረሻም ይህንን ቃል ለዓመታት ብየዋለሁ፤ ዛሬም እናንተ ፊት እደግመዋለሁ፡- በሞት ሽለቆ ሳይታለፍ ታሪክ መቀየር አይቻልም::

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# የዜጎች መፈናቀል፣መታሠር፣መሰደድ በአስቸኳይ ይቁም !

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ  አሁንም በለውጥ ፈላጊነት ተስፋ ላይ ነው። ተስፋው ግን ‹‹ላም አለኝ በሰማይ…›› እንደሆነ ቀጥሏል። ሕዝቡ ነፃነትን ለዘመናት ቢመኝም የሚፈለገው ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ-ሀብታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ዜግነታዊ ነፃነት በተግባርና በተግባር ለብዙኃኑ የለም። የሀገራዊ ሀብት ተጠቃሚነት በዕኩልነት ሊሆን የሚችልበት አንዳች ምልክት ከቶውንም አልታየም። ዜጎች የአብሮነታቸው ዐምድ፣ ዋልታና ማገር፣ ነባራዊና ዘላቂ የሕልውናቸው ዋስትና የሚሆነውን ብሔራዊ አንድነት ቢሹም፤ በተግባር ወደዚህ ሊያመራ የሚችልና በተለይም ከገዥው ፓርቲ አባላት የሚጠበቅና ሊታመኑበትም የሚችል ተጨባጭ ፍንጭ አልተስተዋለም። ‹‹ምሁራኖች›› የሚባሉትም፤ ከሀገር፣ ከዜጎችና ከኢትዮጵያ የማንነቷ ታሪክ ሐቅ ይልቅ፤ ዳቦ እያነቃቸው፣ በእስተርጅና የዕድሜ ዘመናቸው ሳይቀር የመኖር ስስት ትውልድን በሚያስደምም ሁኔታ እያጨናነቃቸው ነው፡ ፡ የኢትዮጵያን እውነት በአደባባይ ለመመስከር ወኔ  አጥተው፤ በቀዝቃዛው የውቅያኖስ ዕምብርት ውስጥ ላብ ሲያሰምጣቸው እያስተዋልን ነው።

ያም ብቻ አይደለም! በኢትዮጵያችን መንግሥታዊ መዋቅር፣ ‹‹የተሃድሶ መስመር›› የምናስተውለው፤ በግለሰብ ደረጃ እንጂ በገዢው ፓርቲ ደረጃ ሥር-ነቀል የአመለካከት ለውጥ አለመኖሩን ነው። ዛሬም! በተለይም በዚህ ሰዓት! ከወራት በፊት ተስፋ ያጫረብን የለውጥ ቃል ነፋስ፤ ያው ነፋስ እንጂ የሚበቅል፣ ፍሬ የሚያፈራ፣ ያፈራውም ፍሬ የሚጎመራ፤ አንድም ለረሃብ ማስታገሻ፣ ሁለትም ለመድኃኒት ሊሆን የማይችል መሆኑን እያስተዋልን ነው።

እንዲህ ብለን ስንልም፤ በንግግር ደረጃ የተገባውን ቃል ለማኮሰስ እና በእኛም በኩል ከወራት በፊት ጀምሮ ለናሙና ያህል የተወሰዱና እሥረኞችን እንደ መፍታትና የፖለቲካ ክሶችን እስከመሰረዝ… ድረስ የዘለቁ ርምጃዎችን ያደነቅንባቸውን አግባቦች ተገቢ አልነበሩም በማለት የስሜት ዝቅታ አይደለም። ይልቁንም እንዲህ ብለን የምንለው፤ አሁን እየታዩ የሚገኙና የሥርዓቱን አለመለወጥ፣ በይበልጥ በፖለቲካዊ ችግሮቹ መጠመዱ ያባባሳቸውን ችግሮች ለመቅረፍ አለመቻሉ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከምንግዜውም ይበልጥ በቃል ደረጃ ለሕዝብ የተሰጠውን ተስፋ ‹‹የዜሮ ድምር›› ያደረገው በመምሰሉ፤ በበኩላችን የሚታየን ብሔራዊ አደጋ በእጅጉ ያሳሰበን መሆኑን ለመግለጽ ነው።

ምንም እንኳ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር በጎረቤት ሀገሮች ባደረጉት ጉብኝት በሀገራቱ ታሥረው የሚገኙ ዜጎቻችን ይፈቱ ዘንድ ግፊት ቢያደርጉም፤ በቅድሚያ ግን በሀገራችን ኢትዮጵያ ለነፃነታቸው፣ ለዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው መከበር ሲሉ በአደባባይ ድምፃቸውን በማሰማታቸው ምክንያት፣ ወይም ደግሞ ‹‹የዓይናቸው ቀለም አያምርም›› ተብሎ፣ ወይም ‹‹ሐሣባችንን የመግለጽ መብት አለን…›› በማለታቸው ወዘተ. ለእሥራት የተዳረጉ፣ ተሸማቀውና ተሳቀው ለመኖር የተገደዱ፣ ሀገር ለቀው የተሰደዱ ዜጎቻችን ሁኔታ፤ የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ለመጠቆምም እንወዳለን።

ሌላው በሀገራችን ‹‹የለውጥ ነፋስ እየነፈሰ ነው! መንግሥት ወይም ገዥው ፓርቲ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊያን የሚበጀውን አቅጣጫ ለመከተል እየፈለገ ነው…›› በሚባልበት በዚህ ወቅት፤ ዜጎች ከመኖሪያ ቀያቸው እየተፈናቀሉ መገኘታቸው፣ ለስደት እየተዳረጉ መሆናቸው፣ መገደላቸው፣ የእሥራቱም ሂደት እንደቀጠለ መሆኑ አያሳስበንም አንልም። ‹‹መነሳት አለበት›› የተባለው ‹‹የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ›› እና ‹‹የኮማንድ ፖስቱ›› ሥልጣን፤ ዛሬም የዜጎችን ድምፅ በመድፈቁ… ሂደት የመቀጠሉም ጉዳይ በራሱ አስጨናቂ ነው። በሞያሌ፣ በቢኒሻንጉል፣ በለገ-ደምቢ፣ በጌዲኦና ጉጂ ዞን ወዘተ. የምናስተውለውና ከየሥፍራዎቹም የምንሰማው ዜና የሚያመለክተው፤ በኢትዮጵያችን ከተስፋ ይልቅ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች እየበረከቱ የመሄዳቸውን እውነት መሆኑን በምንም ዓይነት ማስረጃ ማስተባበል አይቻልም። ስለዚህ በገዛ ሀገር የዜጎች መፈናቀል፣ የወገን አልኝታ ነው በሚባለው ሠራዊት የዜጎች መገደል፣ መታሠር፣ መሰደድ፣ ሀገር አልባ መሆን፣ ተሳቆና ተሸማቆ መኖር፣ በነፃነትና በዴሞክራሲያዊ መብቶች ናፋቂነት መቀጠል፣ በሕግና በሕገ-መንግሥት ስም የዜጎች መበደል፤ በቀጠሮ ነገ፣ ከነገ ወዲያ ሳይሆን በአስቸኳይ ይቁም! እንላለን።


## ግዮን መጽሔት

ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና
ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር
በየ 15 ቀኑ ለኅትመት
የምትበቃ መጽሔት

ማኔጂንግ ዳይሬክተር
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

ዋና አዘጋጅ
ፍቅር ሠይድ
አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር 314

አዘጋጆች
ሮቤል ምትኩ
ብሩክ መኮንን

አምደኞች
አበባው አያሌው
ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ
ተረፈ ወርቁ
መስፍን ጌታቸው
ሁሴን ከድር
በሀይሉ ገ/እግዚአብሔር
ሠሎሞን ለማ

ክርኤቲቭ ዲዛይን
ሀብታሙ መኮንን

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 951693
ኢ-ሜይል፡
Gihon2010meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu

አታሚ
ቢኒያምና በቀለ የሕትመት አገልግሎት
አድራሻ
ክ/ከተማ የካ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 07
የቤት ቁጥር 363
ስልክ ቁጥር  0922446324

# በሞያሌ ዳግሞ ግጭት ተቀሰቀሰ

በሞያሌና አካባቢው ባሉ የሶማሌና የኦሮሞ ነዋሪዎች መካከል በተነሳው ግጭት ከ10 ያላነሱ ዜጎች ህይወታቸው ማለፉን ቢቢሲ ዘግቧል። የቦረና ዞን የጤና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባሮባ ደንጌን ጠቅሶ ቢቢሲ እንዳወራው በግጭቱ ምክንያት ወደ ሞያሌ ሆስፒታል ከ50 በላይ ወገኖች ለህክምና ተወስደዋል። የያቤሎ ሆስፒታል ተጠሪ አቶ አሬሮ ቢቂቻ በበኩላቸው በግጭቱ ተጎድተው ሪፈር ከመጡ አስራ አንድ ሰዎች መካከል ሁለት የፀጥታ አስከባሪዎች ሕይወታቸው ማለፉን ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ክልል የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ ዶክተር ነገሪ ሌንጮ በይፋዊ የፌስቡክ ገፃቸው ላይ በሞያሌ በዜጎች ላይ እየደረሠ ያለውን ጥቃት አውግዘዋል።

የጀርመን ራዲዮ አማርኛው ክፍል በበኩሉ በሞያሌ ከተማ ቴሌ፣ ባንክ እና የመናኽሪያ አካባቢዎች የከባድ መሳሪያ የተኩስ ልውውጥ የበረታባቸው ሲሆን የከተማዋ የፀጥታ ኃይሎች የተኩስ ልውውጡን ለማስቆም የወሰዱት እርምጃ እንደሌለ የሞያሌ ነዋሪዎችን እማኝ አድርጎ ዘግቦታል።

# በኦሮሚያ ህዝባዊ ተቃውሞው አልበረደም!

የሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ኮንትራት መራዘም የተነሳ ላለፉት ሁለት ሳምንታት ያልተቋረጠው የሻኪሶ፣ የጉጂና አካባቢው ህዝባዊ ተቃውሞ ዛሬም አልበረደም። ወደ ለገደምቢ የወርቅ ማምረቻ የሚያልፉ የመብራትና የውሃ መስመሮች በተቃውሞው ከጥቅም ውጭ ሆነዋል።

የማዕድን ኩባንያዉ በጉጂና በሻኪሶ ከተማ አቅራቢያ ከሚገኘው ከለገደምቢ ወርቅ ማውጫ የሚለቃቸዉ በካይ ኬሚካሎች በሰዎችና በአካባቢው ተፈጥሮ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አድርሰዋል በማለት ነዋሪዎች ተቃዋሞአቸውን ዳግም ካለፈው ማክሠኞ ዕለት ጀምሮ በማሰማት ላይ ናቸው።

# ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በቀይ ባሕር

ከኢትዮጵያ እየፈለሱ በጅቡቲ በኩል ቀይ ባሕርን የሚሻገሩ ስደተኞች ከሆነላቸው ወደ አውሮፓ ካልቀናቸው ደግሞ ሳውዲ አረቢያን የሚያልሙ ናቸው። የጅቡቲ ፖሊስ እንደሚለው ከሆነ ከኢትዮጵያ ወደ እዚህችው መሸጋገሪያ ሃገር በየቀኑ 200 ኢትዮጵያውያን ድንበር ተሻግረው በድብቅ ይገባሉ።

ፋይል ግሎባል ዴቨሎፐመንት የተባለን ተቋም ጠቅሶ ዘ ጋርዲያን እንደ ዘገበው ከፍልሰተኞቹ መካከል አብዛኞቹ ከኦሮሚያ ክልል የተሰደዱ ናቸው ።

አለም አቀፉ የፍልሰተኞች ድርጅት አይ.ኦ.ኤም በየካቲት ወር ሪፖርቱ እንዳረጋገጠው 17ሺ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን በጅቡቲ መዝግቧል። አቦክና ታጁራ በተባሉ የቀይ ባሕር ዳርቻ ከተሞች ወደ የመን ለመሻገር የተዘጋጁ ናቸው ተብሏል።

ግሎባል ዲቨሎፐመንትን ጠቅሶ ዘጋርዲያን እንደ ዘገበው በየአመቱ ብቻ አንድ መቶ ሺ የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን ቀይ ባሕርን ይሻገራሉ። ፍልሰተኞቹ ወደ የመን፣ ሳውዲ አረቢያና አውሮፓ በቀይ ባሕር በኩል ብዙ ውጣ ውረድ አልፈው የሚሰደዱት በኢትዮጵያ የሚፈጸምባቸውን ሰቆቃ ለመሸሽና በኑሮ ውጣ ውረድ ምክንያት መሆኑን ዘ ጋርዲያን ዘግቧል።

# የያሬድ ጥበቡ "ወጥቼ አልወጣሁም" መጽሐፍ ለገበያ ቀረበ




በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያላቸው አቶ ያሬድ ጥበቡ "ወጥቼ አልወጣሁም" በሚል ርዕስ ያሳተሙት መጽሐፍ በገበያ ውሏል።

በወጣትነት ዕድሜአቸው የኢህአፓ አባል በመሆን የፖለቲካ ተሳትፎአቸውን የጀመሩት አቶ ያሬድ ጥበቡ ዘግየት ብሎ ከጥቂት ጓዶቻቸው ጋር የቀድሞው ኢህዴን የአሁኑን ብአዴን መስርተው በትጥቅ ትግሉ ወቅት ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርገዋል።

አቶ ያሬድ ኢህዴን ውስጥ እያሉ ከሕወሓት አመራሮች በተለይም ከአቶ መለስ ዜናዊ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ሊስማሙ ባለመቻላቸው ድርጅቱን ጥለው ወደ አሜሪካ ተጉዘዋል። በባህር ማዶ ቆይታቸው በተለያየ መንገድ በሀገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ ከመሳተፍ ባሻገር በርካታ በሳል ጽሑፎችን ለህዝብ ሲያቀርቡ ቆይተዋል።

"ጌታቸው ጀቤሳ" በሚለው የብዕር ስማቸው በይበልጥ የሚታወቁት ያሬድ ጥበቡ ሰሞኑን ለገበያ ያቀረቡት "ወጥቼ አልወጣሁም" የተሰኘው መጽሐፋቸው በሦስት ቀናት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ በመታተሙ ከወዲሁ መነጋገሪያ ሆኗል።

# አንጋፋው ደራሲ አሰፋ ገብረ ማሪያ ከዚህ አለም በሞት ተለዩ



በቀድሞ መንግስት ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር የሆነው ‹‹ኢትዮጵያ ቅደሚ›› ደራሲ አቶ አሰፋ ገብረ ማሪያም በ82 አመታቸው አረፉ:: በ1928 ዓ.ም አዲስ አበባ የተወለዱት አንጋፋው ደራሲ በአርበኞችና በጄኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤቶች መደበኛ ትምህርታቸውን መከታተላቸውን ታሪካቸው ያስረዳል:: በሩሲያ ሌኒን ግራድ ዩኒቨርሲቲ እና ከእንግሊዝ ኤድንብራ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ድግሪያቸውን ያገኙት ደራሲ አሰፋ ገ/ማሪያም ‹‹የመስከረም ጮራ›› እና ‹‹ዘ ቮይስ›› የተሰኙ የግጥም መድብሎችን፣ በርካታ የሥነ-ፅሁፍ ስራዎችን ከማበርከታቸው ባሻገር ‹‹ጁሊየስ ቄሳር›› እና ‹‹ዋናው ተቆጣጣሪ›› የመሳሰሉትን ቴአትሮች ተርጉመው ለመድረክ ያበቁ አንጋፋ ባለሙያ ናቸው:: የራሳቸው ወጥ ስራ የሆነው ‹‹ከለንደን አዲስ አበባ›› የተሰኘው ተወዳጅ ቴአትር ደግሞ በይበልጥ ተጠቃሽ ያደርጋቸዋል:: የአንጋፋው ደራሲ አሰፋ ገ/ማሪያም ስርዓተ ቀብር በስደት በሚኖሩባት አገር አሜሪካ /ላስቬጋስ ነገ እሁድ ይከናወናል:: ግዮን መፅሔት ለቤተሰቦቻቸውና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው መፅናናትን ትመኛለች::

# ኢህአዴግ እና የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ የቁልቁለት ጉዞ

ፕሬስ የሚለው ቃል በአብዛኛው የህትመት መገናኛ ብዙሃንን ለመወከል ጥቅም ላይ የሚውል ቢሆንም በኤሌክትሮኒክስ፣ በዲጂታልም ይሁን በህትመት መገናኛ ብዙሃን ላይ የሚሰሩ ጋዜጠኞች የወል ስም ሆኖ ሲያገለግል ግን ዘመናት ተቆጥረዋል። በዚህም ምክንያት ይመስላል "ፕሬስ" ሲባል ሁሉንም የመገናኛ ብዙሃን (Media) የሚወክል ቃል መሆኑ ተለምዷል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ታሪክ ከኢትዮጵያ ጥንታዊ ሃገርነትና ቀደምት ስልጣኔ አንጻር ሲታይ ጭብጥ የማይሞላ፣ ኢንዱስትሪውም እንደሌላው ዘርፍ ከማደግ ይልቅ በጊዜ ሂደት እየቀረቀዘ ሄዶ በማህበረ ኢኮኖሚና ፖለቲካ ተዋስዖ ውስጥ የተጫወተው ሚና የጫጨ ቢሆንም፤ እንደአቅሙ ግን እየወጣና እየወረደም ቢሆን አራት መንግስታትን ተሻግሯል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ከዓጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ እስከ ዘመነ ኢህአዴግ ድረስ በመንግስታዊ ጭቆና ውስጥ የወደቀና በንስር ዓይን ሥር የኖረ ኢንዱስትሪ ነው። በኢትዮጵያ ከአወዳሽ ሚዲያው ውጭ ያለው ፕሬስ እንዳይወቅስ እና እንዳይከስስ፣ ህዝብን እንዳያነቃና ለመብት ጥያቄ እንዳያነሳሳ ፣ መረጃ እንዳያሰራጭና ለውጥ እንዳይፈጥር መንገዱን የእሾህ ጋሬጣ ሲያበጁበት በኖሩት ገገር መንግስታት ሳቢያ ከዳዴ ጉዞ ፈቅ ሳይል አንድ ክፍለ ዘመን አብቷል። በተለይም የኢህአዴግ መንግስት በሃገሪቱ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ህገ-መንግስታዊ በሆነበት ማግስት ሊያብብ የጀመረውን ፕሬስ በክፉ ዱላ ከመታውና ጋዜጠኞችን ማዋከብ የህልውና ጥያቄ አድርጎ ከተነሳ ወዲህ፤ ዛሬ ይህ የፕሬስ በተለይም የነጻው ፕሬስ ዘርፍ "የደፈረ ብቻ" የሚገባበት "ቀይ ዞን" እንዲሆን ምክንያት ሆኗል።

> በአቶ መለስ ዜናዊ ጊዜ "እስክንድር ነጋን እጃችንን ጠምዝዘው ያስፈቱት እንደሁ እናያለን" እስከማለት የደረሰ እልህ የተጋባችው ይህች ሃገር ፕሬስን በተመለከተ አስካሁንም የቆሸሸ ገጽታ ይዛ የተቀመጠችው መንግስት በተከተለው አጥፊ ስነልቡና ነው

## በ 108 ዓመት 11 ጋዜጣ

በዓፄ ምንሊክ ዘመን በ1902 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው "አዕምሮ" የአማርኛ ጋዜጣ መታተም ሲጀምር የኢትዮጵያ ፕሬስ ታሪክም አሃዱ አለ ። ኢትዮጵያዊ አንባቢ "ከአዕምሮ" ቀጥሎ በሃገሩ ሁለተኛ ጋዜጣ ለማየት 39 ዓመታት መጠበቅ ነበረበት። "አዲስ ዘመን" በመንግስት የሚታተም ሁለተኛ ጋዜጣ ሆኖ ለአንባቢ የደረሰው በ1941 ዓ.ም ነው። የዓፄ ኃይለ ሥላሴንና የደርግን ዘመን ተሻግረው አሁን የኢህአዴግ ዘመን ድረስ የዘለቁትን እነአዲስ ዘመንን የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጦችን ጨምሮ በ1902ዓ.ም. አሃዱ ተብሎ የተጀመረው ጋዜጣ በ2010 ዓ.ም (ከ108 ዓመት በኂላ ማለት ነው) መድረስ የቻለበት የብዛት ጣሪያ 11 ብቻ ነው። ከህትመት ዘርፉ ጋዜጣን እንደምሳሌ ካየን፤ እንግዲህ ይህ አሃዝ የሚያመለክተን በኢትዮጵያ በአማካይ በየ10 አመቱ አንድ ጋዜጣ ብቻ የህትመት ኢንደስትሪውን እንደተቀላቀለ ነው።

## ፕሬስ በዘመነ ኢህአዴግ

ኢህአዴግ በግንቦት 1983 ዓ.ም ወደ ሥልጣን ሲመጣ ካደረጋቸው መልካም ነገሮች አንዱ በሐምሌ ወር የሽግግር ቻርተር በማውጣት ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ቢያንስ በህግ ደረጃ ማስፈሩ ነው። ይህንን ተከትሎ የቅድመ ምርመራ (ሳንሱር) ህግ በመነሳቱ የነጻ ፕሬስ መንፈስ እንዲቀሰቀስና ኢንደስትሪውም ብዛት ያላቸው ተዋናዮችን እንዲያሳትፍ መሰረት ጥሏል። ወደ ገበያው ብቅ ያሉ እንደ ጋዜጣና መጽሄት ያሉት የፕሬስ ውጤቶች ምንም እንኳን በአብዛኛው ሊባል በሚችል መልኩ በባለሙያ የሚሰሩ ባይሆኑም፤ ለአንባቢው ግን በምርጫ ቀርበውለት ነበር። 1985 ዓ.ም የፕሬስ አዋጅ ቁጥር 34/85 ሲደነገግ "ወርቃማ ዘመን" ተብሎ የሚጠራው የፕሬስ አብዮት በኢትየጵያ ፈነዳ።

## የኢትዮጵያ ፕሬስ ወርቃማ ዘመን

በኢትዮጵያ ታሪክ ቀደሞም ያልነበረ ኂላም ያልተደገመ የህትመት ውጤቶች ቁጥር የተመዘገበው በ1985 እና 86 ዓ.ም ነበር። በ1985 ዓ.ም በኢትዮጵያ ውስጥ 28 ጋዜጣና 65 መጽሄቶች የነበሩ ሲሆን፤ በ1986 ዓ.ም ደግሞ ይህ ቁጥር አሻቅቦ 79 ጋዜጣና 38 መጽሄቶች በድምሩ 117 የህትመት ውጤቶች ገበያውን አጥለቀለቁ። በጊዜው የዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ የገነነበት፣ ህዝቡ በሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ከምንግዜውም በላይ ያገባኛል ያለበት ወቅት ስለነበር፤ አዲስ ከነበረው የዴሞክራሲ ጽንሰ ሃሳብ ጋር ተዳምሮ ዛሬ ላይ መልሶ የሚደገም የማይመስል ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ተንሰራፋ። ይህን ተገን ያደረገው የኢትዮጵያ ፕሬስ በተለይም የግሉ ፕሬስ በመንግስት አሰራሮች ላይ ብቻ ሳይሆን በማህበረ ኢኮኖሚ ተሳትፎውም የጎላ ድርሻ መያዝ ጀመረ።

አሳታሚዎች በተለያየ አቀራረብ ይዘዋቸው ብቅ ከሚሉት የፕሬስ ውጤቶች ከሲሦ በላይ የሆኑት የፖለቲካ ይዘት ያላቸው ነበሩ። ጊዜው የጋዜጦች ብቻ ሳይሆን የመጽሄቶች አብዮትም የፈነዳበት ነበር። በፍቅርና ጾታዊ ግንኙነቶች፤ እንዲሁም በፋሽን ጉዳይ ላይ በሚያተኩሩ መጽሄቶች ተጣቦ የነበረው ገበያ ቀስ በቀስ ፖለቲካዊ ይዘት ወዳላቸው መጽሄቶች በመምጣቱ የሚቀርቡት መረጃዎች ለአንባቢውም የመወያያ አጀንዳ በመፍጠር ሃገራዊ ጉዳዮች ወደ ህዝባዊ የፖለቲካ ተዋስዖ መድረኮች እንዲመጡ እስከማድረግ የደረሰ አቅም ፈጥረዋል። በአንጻሩ በብዛት እና በስፋት የፖለቲካው ጉዳይ ላይ አትኩረው ይሰሩ የነበሩ የግል ፕሬሶች ማበብ በተቃራኒው የመንግስት የፕሬስ ውጤቶች የፕሮፓጋንዳ ማሽን ይዘት ያላቸው ሆነው እንዲቀጥሉ አድርጓል።

ይህ በመጥፎ ጎኑ የኢትዮጵያ ፕሬስ በሁለት ጽንፍ ተደራጅቶ ግንብ እንዲያበጅ ምክንያት ሆኗል። በመንግስት መገናኛ ብዙሃን ነጻው ፕሬስ ኢ- ተዓማኒና በስሜት የሚነዳ፤ እንዲሁም በተዛባ መረጃ የህዝቡን ሰላም ለማደፍረስ የሚሰራ ተደርጎ መወቀሱ፤ በነጻው ፕሬስም በኩል በመንግስት ይዞታ ስር የሚገኙ የፕሬስ ውጤቶች ከፕሮፓጋንዳ ስራ እና ከውሸት ሪፖርቶች የዘለለ የህዝቡን

ድምጽ የመስማት አቅም የሌላቸው ተደርገው መወሰዳቸው፤ በኢትዮጵያ የግልና የመንግስት ፕሬስ የሚባሉ ሁለት ፕሬሶች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡

## "አወዳሽ" እና "ከሳሽ" ፕሬስ

ጄኒፈር ፓርሜሌ የተባለች በ1990ዎቹ እ.ኤ.አ መጨረሻ አካባቢ ቪኦኤ የምስራቅ አፍሪካ ተጠሪ የነበረች ጋዜጠኛ "የኢትዮጵያ ፕሬስ ሁለት ጽንፍ፤ አንዱ አይኑን ጨፍኖ የሚያወድስ፤ አንዱም አይኑን ገልጦ የሚከስስ ተቋም አድርጎታል፣ ይህንን በሁለት ግንብ የተከፈለ "የመንግስት" እና "የግል ፕሬስ" ወደ አንድ የማምጣት ስራ ጊዜ ሊፈጅ ቢችልም የግድ መሆን ያለበት ነገር ነው " ብላ ነበር፡፡ በርግጥም በሃገሪቱ እዚህም እዚያም የሚታዩ የፍትህ፣ የመልካም አስተዳደርም ይሁን የሙስና እንዲሁም የፖሊሲ ችግሮችን አይቶ እንዳላየ በማለፍ ኗሪው ህዝብ ከሚያውቃት ኢትዮጵያ ውጪ የሆነች ኢትዮጵያን ለመሳል የሚለፋ የመንግስት ፕሬስ ባለበት ሃገር የግሉ ፕሬስ በልማት ጋዜጠኝነት ስም ተመሳሳይ ተግባር ውስጥ ቢሰማራ ተገቢም አይሆንም ፣ የመረጃ ብዝሃነትም አፈር ይግጥ ነበር፡፡ የመንግስት ፕሬሶች ጭልጥ ወዳለ አፍቃሬ መንግስት ግብር ሲገቡና የህዝቡን ህይወት ረስተው የፓርቲ ፖለቲካ ማናፈሻ መድረኮች ሲሆኑ፤ በተቃራኒው የግሉ ፕሬስ የመንግስት ፕሬሶች በማይነኩት ችግሮችና ስህተቶች ላይ ብቻ አተኩሮ ሲሰራ፤ የፕሬስ 'ተዓማኒነት' ድንበር የቱ ጋ እንደሆነም ለማወቅ እስኪያስቸግር ድረስ ተደባለቀ፡፡

ህዝቡ የሰለቸውን የራዲዮ እና ቴሌቪዠን ፕሮፓጋንዳ ሸሽት በነጻው ፕሬስ መረጃ ጥላ ስር ራሱን መቅበሩ በአወንታዊ ጎኑ የማንበብ ባህልን አዳብሮ የጋዜጣና መጽሄት ህትመት እንዲሰፋ ቢያደርግም፤ በዚያው ልክ በነጻው ፕሬስ በተቃውሞ እና ክስ ላይ ካላተኮረ በቀር፣ በሚዛናዊነት የሚሰራውን ስራ የማግለል እና የመፈረጅ ባህል እንዲሰፍን ምክንያት ሆነ፡፡ ቲሞቲ ስፔንስ የሚባል በ1994 እስከ 1998 ድረስ በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ትምህርት ይሰጥ የነበረ የጋዜጠኝነት ባለሙያ እንደሚናገረውም የኢትዮጵያ ፕሬስ በሁለት ጫፍ ተይዞ በአንባቢ ምርጫ የሚጎተትና የራሱን አጀንዳ መቅረጽ እንዳይችል ተጽዕኖ ውስጥ የወደቀ ፕሬስ እንዲሆን ምክንያት ሆነ፡፡

## የፕሬስ የቁልቁለት ጉዞ

በኢትዮጵያ በከፍተኛ ቁጥር አድጎ የነበረው የህትመት ውጤቶች ገበያ ማሽቆልቆል የጀመረው እንደሚባለው ከወረቀት ዋጋ መወደድ እና ከሶሻል ሚዲያው መስፋት፣ እንዲሁም ከአሳታሚዎች አቅም ማነስና ከማስታወቂያ እጦት ጋር በተያያዙ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ብቻ አለመሆኑን በተደጋጋሚ መድረኮች የፕሬስ ባለሙያዎቹም ይሁኑ ጉዳዩን የሚያጠኑ ምሁራን የሚገልጹት ሃቅ ነው፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ህትመት ኢንደስትሪ ውስጥ የግልና የመንግስት ጋዜጣና መጽሄቶች ተደምረው ቁጥራቸው ወደ 24 ባሽቆለቆለበት ሁኔታ፣ በተግባር ከ100 ሚሊዮን በላይ ለሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ በብሄራዊ ቋንቋ የሚታተሙ የግል ጋዜጦች ቁጥር ወደ 3 በወረዱበት ሁኔታ፣ ብዛት ያላቸው በሃገሪቱ ውስጥ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣትና ጤናማ ማህበረ ፖለቲካ ለመገንባት አቅም የነበራቸው መጽሄቶች ከገበያው እንዲጠፉ ተደርገው የህትመት ዘርፉ በቀጨጨበት ሁኔታ በኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት ተከብሯል ብሎ መናገር አባይነት ይሆናል፡፡

ዘንድሮ ሚያዝያ 25 ቀን በሃገር አቀፍ ደረጃ በተከበረው የፕሬስ ነጻነት ቀን ላይ ከተሳታፊዎች እንደተነገረው የኢትዮጵያ የፕሬስ ጉዞ በቁልቁለት መንገድ ላይ ነው፡፡ መንግስት፤ የፕሬስ ነጻነትን የሚያረጋግጡ ህጎች ማውጣቱንና፣ እነዚህ ህጎች ለብቻቸው በሃገሪቱ የፕሬስ ነጻነት መከበሩን እንደሚያረጋግጡ ደጋግሞ ቢናገርም፤ በተቃራኒው ኢትዮጵያ ፕሬስ አፋኝ ሃገር መሆኗ ሪፖርተርስ ዊዝአውት ቦርደርስ በተባለ ተቋም በ2018(እ.ኤ.አ) አለም አቀፉ የፕሬስ ፍሪደም ኢንዴክስ ላይ ከ180 ሃገራት ያገኘችው 150ኛ ያሽቆለቆለ ደረጃ ብቻ አይቶ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሰነዱ ቃል በቃል "….Ethiopia at 150th place out of 180 countries, is one of the worst places for press freedom and journalists" ይላል፡፡

እዚህ ጋ በ1987 ዓ.ም ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት በህ-ገመንግስቱ ተደንግጎ፣ እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን የመረጃ ነጻነት አዋጅ በ2000 ዓ.ም ታውጆ በአንጻራዊነትም ፕሬስ የህግ ማዕቀፍ ተቀምጦለት ባለበት ሁኔታ፣ ፕሬሱን ወደ ቁልቁለት መንገድ የነዳው ምንድነው የሚለውን መጠየቅ ግድ ይሆናል፡፡

## የኢኮኖሚና ፖለቲካ ግፎች

የኢትዮጵያ ፕሬስ እንዲያሽቆለቁል የኢህአዴግ መንግስት ለአመታት ሆን ብሎ ብዙ ለፍቷል፡፡ በተለይ የ1997ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ በሃገሪቱ የተፈጠረው ህዝባዊ ተቃውሞ ኢህአዴግ ከየትኛውም ነገር በላይ ፕሬስንና ብዕርን እንዲፈራ ስላደረገውና ለዚህ ህዝባዊ ተቃውሞ መሰረታዊ አነሳሽ ፕሬሱ ነው የሚል ጭፍን ድምዳሜ ላይ ስለደረሰ የተለያዩ አፋኝ ህጎች በማውጣት የፕሬሱን አቅም ለመሰባበር ሙከራ አድርጓል፣ ተሳክቶለታልም፡፡ ተከትሎም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና አመራሮችን በማሰር፣ ጋዜጠኞችን በሃገር መክዳት ወንጀል ወህኒ በማጎር፣ ያንን ተከትሎም እንደ ጸረ ሽብር ህግ እና የመሳሰሉትን አፋኝ መመሪያዎች በማውጣት ሃሳባቸውን በነጻነት ለመግለጽ የሚታትሩና በሃገራቸው ፖለቲካ ውስጥ የህዝብ መደመጥንና ጥቅምን ለማረጋገጥ መረጃን በማዳረስ ሙያዊ ግዴታቸውን የሚወጡ ጋዜጠኞችን በሽብር ህግ እየከሰሰ ወደ ወህኒ አውርዷል፡፡ እንደነእስክንድር ፣ ተመስገን፣ ርዕዮት፣ውብሸት እና ሌሎችንም በዚህ የመንግስት የፕሬስ እቀባና ፍራቻ ጦስ የተለያዩ ክሶች ተመስትሮባቸው ወደ ወህኒ ተወርውረው የነበሩ ጋዜጠኞችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ አልበቃ ብሎም በርዝራዥ የተረፉ የነጻ ፕሬስ ውጤቶችን "የግንቦት ሰባት እና አሸባሪ ድርጅቶች ድጋፍ ያደርጉላቸዋል፣ ሃገሪቱን ለማፈራረስና ህገመንግስቱን በሃይል ለመናድ ይሰራሉ፣ በመረጃ ነጻነት ሰበብ ጥፋት ተግባር ላይ ተሰማርተዋል" ወዘተ በማለት የህትመት ውጤቶቹ እንዲዘጉ እና አሳታሚዎችም እንዲከሰሱ በማድረግ ብዛት ያላቸው መጽሄቶች ከገበያ እንዲወጡ አድርጓል፡፡ በተካሄደው የታቀደ የማዋከብና የማስፈራራት ሥራ በኢንደስትሪው ውስጥ አወንታዊ ሚና መጫወት የሚችሉ ብዛት ያላቸው ባለሙያዎች ስደት ገብተዋል ፡፡

ኢህአዴግ እነዚህን ሁሉ የተቀነባበሩ ጥቃቶች በፕሬሱ ላይ ሲፈጽም፤ በአንድ በኩል ጋዜጠኛን አልከሰስኩም እያለ መግለጫ በመስጠት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጋዜጠኛው የሚሰራበትን ሚዲያ እንዳይተርፍ አድርጎ እያጠፋ ተግባሩን በማይታረቅ ተቃርኖ ውስጥ ከትቶ ነው፡፡ ይህ መንግስት በፕሬሱ ላይ ከሰነዘረው ቀጥተኛ ጥቃት ባሻገር ፕሬሱን በኢኮኖሚ እንዳይዳብርና በኪሳራ እንዲከስም ማስታወቂያ የሚሰጡ ድርጅቶችን በማስፈራራት፣ ማተሚያ ቤቶችን እንዳያትሙ በመከልከል፣ የህትመት እና ወረቀት ዋጋን በማናር እና የመጽሄት እና ጋዜጦችን ስርጭት ለመግታት የህትመት ውጤቶችን ሰብስቦ እስከማሰር የደረሱ ከአንድ መንግስት የማይጠበቁ የወረዱ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ይህንን ተከትሎ አቅማቸው የሳሳ እና ገበያውን የመቋቋም አቅም አጥተው የከሰሙ የፕሬስ ውጤቶችን "በኢኮኖሚያዊ ጫና ምክንያት በገበያው መዝለቅ ባለመቻላቸው የተበተኑ" የሚል ስም አውጥቶ ራሱን ከደሙ ንጹህ ለማድረግ ሞክሯል፡፡

## አጥፊ ስነ-ልቡና

"ስነልቡናው በማጥፋት የተለከፈ የማልማት በር የቀዳዳ ያህል አይታየውም፡፡ " እንደሚባለው ኢህአዴግ ፕሬሱ ላይ ካለው ቂም እና መሰረተ ቢስ ውንጀላ የተነሳ ነጻው ፕሬስ እንዲያብብ አይፈልግም፡፡ በአንጻሩ በነጻ ሚዲያ ስም በገበያው ውስጥ ከፍተኛ በጀት መድቦ የሚሰገስጋቸውን የህትመት ውጤቶች የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እየነሰዙ የኢትዮጵያ ፕሬስ ሃላፊነት የጎደለው እንደሆነ እንዲሰብኩ ሲያተጋ ኖሯል፡፡ በዚህም ወጣ በዚያም ወረደ መንግስት ኢትዮጵያን ለጋዜጠኞች ምቹ ካልሆኑ ብቻ ሳይሆን ጋዜጠኝነትን ለመተግበር የሲዖል ያህል ከከፉ ሃገራት አንዷ ተደርጋ ከመታየት ግን አላገዳትም፡፡ የአለም አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ድርጅት ሲፒጄ፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሌሎችም ተቋማት ኢትዮጵያን በብዙ ሲከስሱና መንግስት ከዚህ ተግባሩ እንዲታቀብ ሲጠይቁ ኖረዋል፡፡ በአቶ መለስ ዜናዊ ጊዜ "እስክንድር ነጋን እጃችንን ጠምዝዘው ያስፈቱት እንደሁ እናያለን" እስከማለት የደረሰ እልህ የተጋባችው ይህች ሃገር ፕሬስን በተመለከተ እስካሁንም የቆሸሸ ገጽታ ይዛ የተቀመጠችው መንግስት በተከተለው አጥፊ ስነልቡና ነው፡፡

## "ለፕሬስ አጥፊ ፌስቡክን ያዝለታል"

ዛሬ መንግስት በተደጋጋሚ "በሶሻል ሚዲያው ሃላፊነት የጎደለው እና የሃሰት ዘገባ ይሰራጫል፣ ህዝብና ህዝብን የሚያቃቅሩ መረጃዎች ይወጣሉ፣ ጠባብነት ሰፍኗል የተቃውሞ ባህል ብቻ ዳብሯል" ወዘተ እያለ እሮሮ ያሰማል ፣ ይወተውታል፡፡ በህግ ተመዝግቦና አድራሻው ታውቆ ተገቢ ግብር ከፍሎና ህጋዊ ሆኖ የሚሰራ፣ የህትመት ይዘቶቹ ተገምግመው ሲያጠፋም እየታረመ መልካም ሲሰራም አይዞህ እየተባለ መቀጠል ይችል የነበረውን ነጻ ፕሬስ አውድሞ አንድ ድምጽ ብቻ እየሰማ በሰላም ለመቀመጥ ያሰበ መንግስት የእጅህን አግኝ ሲለው የቴክኖሎጂ ትሩፋት የሆነው፣ ማንም የማያዘውና የሚለቀቀውን መረጃ ምንጭ ለማወቅ የሚከብደውን ፌስ ቡክን አዘዘለት፡፡ እነሆም በዚህች ሃገር ዛሬ የመጣው ለውጥ በዋናነት የተዘጋውን የመረጃ አማራጭ ወለል አድርጎ በከፈተው ነገር ግን በአግባቡ መጠቀም ካልተቻለ አደጋም ያለው ፌስቡክ በስፋት ጥቅም ላይ በመዋሉ ነው፡፡ " ሁሉም በር ሲዘጋ ግድግዳም በር ነው" እንደሚባለው መንግስት የመተንፈሻ በሮችን ሁሉ ዘጋግቶ የተቃውሞ ድምጽ ግድግዳውን እንዲያፈርሰው አድርጎታል፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካም ዛሬ ይሆናል ተብሎ ባልተጠበቀ መስመር እየተጓዘ ያለው በዚሁ የታፈነ ድምጽ በፈጠረው ማዕበል እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ መንግስት መረጃን እያረጋጋ እና ሚዛናዊነትን እያሰፋ በህግ የሚመራውን ፕሬስ ምህዳር እንደጀመረው እያጠበበ ከሄደ ዛሬ የተረጋጋ የሚመስለው የፖለቲካ መስመር ዳግም እዚህም እዚያም በሚበታተኑ መረጃዎችና ባልተጠኑ ውሳኔዎች በማንኛውም ጊዜ ስላለመናወጡ ዋስትና የለም፡፡

# <<ቤተሠቤ በትግል የተፈጠረ፤ ለትግል የሚኖር ነው>>

## ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ (ከአሜሪካ)

*ጋዜጠኛ የሰብዐዊ መብት ተሟጋቹ እስክንድር ነጋ ከስድስት ዓመት ተኩል እስር በኋላ ከሌሎች የነፃነት አርበኞች ጋር ሲፈታ በሀገር ውስጥ የተጀመረው ደማቅ የጀግኖች አቀባበል ድንበር ተሻግሮ ከሆላንድና ኬንያ መልስ አሁን ባለቤቱና ልጁ ወደሚገኙበት አሜሪካ አድርሶታል:: የዋሽንግተኑ ታሪካዊ የነበረው አቀባበል በሽዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሠንደቅ የደመቁበት ነበር:: የአሜሪካ የፀጥታ ኃይልን ጫና ውስጥ የከተተው ይኼው ደማቅ የአቀባበል ዝግጅት ለእስክንድርም እንግዳ ነበር:: ለእስክንድር ነጋ ዋሽንግተን ዳላስ ኤርፖርት ላይ አቀባበል እንደሚደረግ አስቀድሞ ለፖሊስ ተነግሯል። በስፍራው ተመድቦ የነበረው የፖሊስ ኃይል የገጠመው ነገር ከተጠበቀው በላይ ያልገመተው በመሆኑ በእጅጉ አሳስቦታል። ግልብጥ ብሎ የወጣው የዲሲና አካባቢው ሕዝብ የአውሮፕላን ማረፍያውን አጨናንቆታል። መንገድ ተዘግቷል። መንገደኞች ያለችግር ይተላለፉ ዘንድ የእስክንድር ጉዳይ በአፋጣኝ ማለቅ ነበረበት።*

*እስክንድር በዚያ መንገድ ወጥቶ ባንዲራዋን ይዞ የሚጠብቀው ወገን ጋር ተቀላቀለ። የፖሊሶቹ ስጋት ግን አሁንም አልቀረም። ከብዙ ጭንቅንቅ በኋላ በተዘጋጀለት ሊሞዚን ወጥቶ በአጀብ ወደ ማርቲን ሉተር መታሰብያ ፓርክ ሄደ። ከአዳልስ ኤርፖርት እስከ ፓርኩ ድረስ በፖሊስ ታጅቦ አመራ። መንገዱ በመኪና ተሞልቶ የትራፊክ ጭንቅንቁ አይጣል ነበር። ፅኑው ታጋይ በኢትዮጵያ ባንዲራ አሸብርቆ በመቶዎች በሚቆጠር መኪና በፖሊስ ታጅቦ ሲሄድ ልዩ ነበር።*

*ከ24 ዓመታት በፊት አሜሪካን ሃገር ሲኖር ጥዋት እየተነሳ የሚሮጥበት ፓርክ፣ አሁን የማርቲን ሉተር ሐውልት ሰፍሮበታል። እስክንድር ያንን ጊዜ እያስታወሰ ደስታውን በእጥፍ ሞላው።*

*እኛም አስገራሚ በሆነው አቀባበል ላይ በሽዎች ለሚቆጠሩ የእናት ሀገራቸውን መፃኢ የነፃነት አየር ለሚናፍቁት ኢትዮጵያውያን ፊት ቆሞ ያደረገውን ሙሉ ንግግር አስቀድመን እና በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በስልክ ያደረገውን ቃለ ምልልስ አስከትለን እንደሚከተለው አቅርበነዋል::*



## እስክንድር ነጋ በአሜሪካ ያደረገው ሙሉ ንግግር!

በቅድሚያ ባለቤቴ ሠርካለም ያስተላለፈችውን መልዕክት እኔም በመድገም ልጀምር:: ወደዚህ አገር መጥቶ በሥደት ይቆያል፤ ሀገሩ አይመለሥም ብለው የሚያሥቡ ካሉ ሠርካለም ለኢትዮጵያ ህዝብ "ልጃችሁን በቶሎ እመልሣለሁ አታሥቡ" ብላለች::

የዴሞክራሲ ጥማት፤ የፍትሕ ጥማት፤ የዕኩልነት ጥማት፤ የዕውነት ጥማት፤ የወንድማማችነት፣ የአንድነትና የፍቅር ጥማት ያንገበገባችሁ የሀገሬ ኢትዮጵያ ልጆች በብዙ ልፋት እጅግ የደመቀና አሥደማሚ የሆነ አቀባበል ሥላደረጋችሁልኝ ከልብ አመሠግናችኋለሁ:: እኔን እንዳከበራችሁኝ ሁሉ የሁሉ ነገር መጀመሪያና መጨረሻ የሆነው ፈጣሪ ያክብራችሁ::

በዚህ አጋጣሚ እዚህ ዋሽንግተን፣ በመላ አሜሪካና በተለያዩ ሀገራት የምትገኙ ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ደከመኝ፣ ሠለቸኝ ሣትሉ ላለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት ለዴሞክራሲና ለሠብዐዊ መብት ላሠማችሁት ድምጽ በኢትዮጵያ ህዝብ ሥም አመሠግናለሁ እላለሁ::

በሰው ልጅነታችን በተፈጥሮ የተጎናፀፍናቸው መሠረታዊ የሆኑት የመናገር፣ የመሠብሠብ፣ የመደራጀት፣ የማሠብና የማወቅ መብቶቻችን በአምባገነኖች ተደፍጥጠው በኖሩባት ኢትዮጵያ ብዙኃኑ ዲያስፓራ ድምጹንና ወገንተኝነቱን፣ የሕጻናትንና የንጹሃንን ደም በግፍ ካፈሠሡት ጎን ሣይሆን ከሠማዕታት ተርታ ተሠልፏል::

እንዲሁም ድምጹንና ወገንተኝነቱን ቤተመንግሥት ውስጥ ካሉት ገዥዎች ጋር ሣይሆን በየእሥር ቤቱ ከሚማቅቁት የዴሞክራሲ አርበኞች ጋር አውሏል:: የምርጫ ድምጹን ለተቀማው ህዝብ ሠጥቷል::

በአጠቃላይ የጭቆናቹ አለኝታና መከታ ሆኖ ደማቅ ትግል ጽፏል፣ አሁንም እየፃፈ ይገኛል:: ዳግም ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያንን

እናመሠግናለን::

በዚህ ሒደት ህዝብ እና ኢህአዴግ ሥለ ዲያስፖራው ያላቸው ዕይታ የቀንና የጨለማ ያህል ተለያይቷል:: በአምባገነኖች ግንዛቤ ዲያስፖራው አክራሪ፣ ሽብርተኛ፣ ትምክህተኛ፣ ጠባብና ስለ አገሩ በቂ መረጃ የሌለው አላዋቂ ነው:: በህዝቡ ሚዛን ግን ዲያስፖራው የዴሞክራሲ ጠበቃ፤ የሰብዐዊ መብት ተሟጋች፤ የጭቁኖች አለኝታና የአገር ሀብት ነው::

እኔ ዛሬ በመካከላችሁ የምገኘው ይህንን የህዝብ ደምጽ ይዤ ነው:: ለዴሞክራሲ ዘብ መቆም፣ መታገል፣ አክራሪነትና ሽብርተኝነት አይደለም:: ሰብዐዊ መብት ይከበር ማለት፤ ሕጻናትና ንጹሃን አይገደሉ ማለት፤ ሠላማዊ ሠልፈኞች ላይ አይተኮስ ማለት፤ አገር ቤት ሥላለው ተጨባጭ ሁኔታ በቂ መረጃ የሌለው ዲያስፖራ መሆን ማለት አይደለም::

እንዲያውም ከዚህ በተቃራኒው አገሩን ጠንቅቆ ማወቅ ነው:: አገሩን መውደድ፤ ሰውን በሰው ልጅነቱ መውደድና ማክበር ነው፤ ከዚያም ባሻገር የሞራል ሰው ሆኖ መገኘት ነው::

ዲያስፖራው በያዘው አቋም ፀንቶ ኢትዮጵያ የነፃነት አየር የሚተነፈስባት አገር እስክትሆን ድረስ የሚችለውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክት በተከበረው የኢትዮጵያ ህዝብ ሥም አበክሬ እጠይቃለሁ::

በመጨረሻም የአገራችን የዴሞክራሲ ጥያቄ ሥር ነቀል በሆነ መፍትሔ እንጅ በጥገናዊ ለውጥ ምላሽ የሚያገኝ አይደለም:: ይህ ሥር ነቀል የሆነ መፍትሔ እንዲመጣ ደግሞ ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይገባቸዋል:: እነዚህም፦

**አንደኛ**፦ የግንቦት ሠባቱን አንዳርጋቸው ፅጌና የኦነጉን መስፍን አበበን ጨምሮ ሁሉም የፖለቲካ እሥረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፈታት ይገባቸዋል::

**ሁለተኛ**፦ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መነሣት ይገባዋል:: በዚህ አላስፈላጊ አዋጅ ሣብያ የታሠሩና አሁንም እየታሠሩ የሚገኙት ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፈታት ይገባቸዋል::

**ሦስተኛ**፦ የደቡብ አፍሪካን ተሞክሮ መሠረት አድርጎ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች የሚያካትት፤ ሁሉን ዓቀፍ ድርድር እንዲደረግ በመንግሥት በኩል ጥሪ መቅረብ ይገባዋል:: በዚህ ሁሉን ዓቀፍ ድርድር ውስጥም በሽብርተኝነት የተፈረጁ ድርጅቶችም መካተት ይገባቸዋል::

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አህመድ ድርጅታቸውንና መንግሥታቸውን ለጥገናዊ ሣይሆን ለሥር ነቀል ለውጥ ያሠልፉታል ብዬ እኔም እንደ ብዙኃኑ ህዝብ ከልብ እመኛለሁ:: ነገር ግን ሥር ነቀሉን ለውጥ ትተው ጥገናዊ መንገዱን ከመረጡ ግን ሠላማዊ የህዝብ ትግል ከመቼውም ጊዜ በላይ ተጠናክሮ እንደሚመለስና፤ በዚህ ትግል ውስጥም የቀድሞ እሥረኞች በአገር ቤት ውስጥ ሆነን ፊት ለፊት የምንሠለፍ መሆናችንን እንደገና ቃል በመግባት አረጋግጣለሁ::

አምባገነንነት በቅቶናል! በትግላችን የተሟላ የዴሞክራሲ ሥርዓት ዕውን እናደርጋለን! እውነት ከእኛ ጋር ነው! ታሪክ ከእኛ ጋር ነው! ህዝብ ከእኛ ጋር ነው! ከሁሉም በላይ ደግሞ ፈጣሪ ከእኛ ጋር ነው!

**አመሠግናለሁ ድል ለዴሞክራሲ!**

**ግዮን፦ እስኬ እንኳን ከቤተሰቦችህ ጋር በሠላም አገናኘህ እንኳን ደስ ያለህ::**

**እስክንድር፦** አመሠግናለሁ:: እግዚአብሔር ያክብርልኝ::

**ግዮን፦ አሜሪካ ስትደርስ የነበረው አቀባበል አስገራሚ እንደነበር ታዝበናል:: ባለፉት ዓመታት እንዲህ ዓይነት ትልቅ አቀባበል አላየንም ፤አንተስ ጠብቀኸው ነበር፤ ምን ስሜት አደረብህ?**

**እስክንድር፦** የሚገርም አቀባብበል ነበር ያደረጉልኝ:: ግን ደጋግሜ ላሰምርበት የምፈልገው አቀባበሉ ለኔ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው ሰላማዊ ትግል የተደረገ አቀባበል ነበር:: በዚያ ደረጃ የተዘጋጀ ስለነበር በጣም ከፍተኛ ህዝብ ነው አቀባብል ያደረገልኝ:: ነገሩ የተጀመረው ገና ከአውሮፕላኑ ስወጣ አንስቶ ነው:: መረጃው ስለነበራቸው በሩ ላይ ፓሊሶች ጠብቀው፤ ከሌላው መንገደኛ ነጥለው በኢምግሬሽን በኩል አልፌ ነው ወደሚጠብቁኝ ኢትዮጵያውያን የተወሰድከት:: እጅግ ቁጥሩ የበዛ ህዝብ ሊቀበለኝ ስለ ወጣ በአካባቢው ብዛት ያለው የፀጥታ ኃይል በከፍተኛ ጥንቃቄና ዝግጅት የተሰማራበት ነበር:: ከዛ በፊት እንዲህ አይነት የኢትዮጵያውያን አቀባበል ስላልታየ የአሜሪካ ፖሊሶች ከአውሮፕላን ተቀብለው ግርግሩን ሊቀንስ ይችላል ያሉትን መንገድ ተጠቅመዋል:: ከህዝቡ ጋር በተገናኘሁበት ጊዜ ደግሞ ኢትዮጵያዊያን ለለውጥ ያላቸውን ፍላጎትና ተስፋ በአቀባበሉ ላይ አንፀባርቀዋል::

ያን ያህል ከፍተኛ ሰው የመጣው እኔን ለመቀብል አይደለም፤ በዋናነት ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ያስፈልጋል ለማለት ብቻም አይደለም፤ በአገር ውስጥ ያለው ስሜት ነፀብራቅ ተጋሪ ለመሆን ነው:: በአገር ውስጥም ተመሳሳይ ነገር ነው ያለው:: አገሪቱ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ታፍና ነው እንጂ ይሄ ባይኖርና ህዝቡ የመሰብሰብ እድሉን ቢያገኝ በዋሽንግተን ያየነው ልዩ ነገር አይሰማም ነበር:: አቀባበሉ በአገር ቤት ያለውን ስሜት ነው ያስታወሰኝ::

**ግዮን፦ ከሰባት ከባድ የእስርና የመከራ ዓመታት በኋላ ከምትወዳቸው ባለቤትህና ልጅህ ጋር ተገናኝተሃል ፤እነሱን ስታገኝ የነበረህ ስሜት ምን ይመስላል?**

**እስክንድር፦** መጀመሪያ ላይ ብዙ ህዝብ ስለነበር ባለቤቴ ሰርካለምን ለይቼ አላገኘኋትም፤ ቅድሚያ ሊቀበለኝ የመጣውን ሰው ነው ያስተናገድኩት:: በኋላ ሰርኬን ባገኛትም አላወራኋትም:: በመሐል ያልታሰበ ስሜት ተፈጥሮ ህዝቡ ወደ አልሆነ አቅጣጫ እንዳይሄድና ስሜቱ እንዳይረበሽ፣ እንዳይደናገጥ ተብሎ ልጄን(ናፍቆትን) ወደ ጎን አድርገውት ነበር:: ልጄንም ያገኘሁት መኪና ውስጥ ከገባሁ በኋላ ነበር:: ያን ጊዜ ልዩ ስሜት ነው የተሰማኝ:: ቃላቶች ዓቅም የላቸውም፤ ያንን ስቀይና መከራ ተቋቁሞ እስካሁን ድረስ በፅናት የዘለቀ ቤተሰብ ነው:: መኪና ውስጥ ከቤተሰቦቼ ጋር እያለሁ ሰርካለም ለደወሉላት ሚዲያዎች የተናገረችው ነገር ዘላለም ልቤ ላይ ታትሞ ይኖራል:: ለኢትዮጵያ ህዝብ ያስተላለፈችው መልዕክት ‹‹ልጃችሁን እመልሳለሁ›› ነበር ያለችው:: አልተነጋገርንበትም፣ አልተመካከርንበትም ግን ውስጧ የነበረውን ስሜት ነው ለህዝቡ የገለፀችው:: ምን ያህል አገርና ወገኗ በውስጧ እንዳለ፤ ለህዝብ ያለባትን ኃላፊነት እንደማትዘነጋና እንደማትረሳ የገለፀችበት መንገድ ነው:: ልጃችሁን እመልሳለሁ ያለችው በቁም ነገር ሁሌም ከልቤ የማይጠፋ ታሪካዊ ቃሏ ነው::

**ግዮን፦ አንዳንድ ፖለቲከኞች ቅድሚያ እንደመስፈርት አድርገው የሚያስቀምጡትና ከፖለቲካው የትግል ሜዳ ወደኋላ ሸሸት የሚሉበት የትዳርና የልጅ ጉዳይ ነው:: የፖለቲካ ትግልና የቤተሰብ ህይወትን እንዴት ታይዋለህ ?**

**እስክንድር፦** ሁሉም ሰው በዚህ መንገድና በእኔ መስመር መጓዝ አለበት ማለት ያስቸግራል:: ሁላችንም የራሳችን አቋምና የግል መሠረታዊ መነሻ ስላለን፤ ለቤተሰባቸው ቅድሚያ መስጠት የመረጡትንም ማክበር አለብን:: የእኛ ቤተሰብ ትንሽ ለየት የሚለው በመጀመሪያ ደረጃ እኔና ሰርካለም የተገናኘነው በትግል መድረክ ላይ ነው:: በትግል መድረክ የተመሰረተ ግንኙነት ውስጥ ነው ልጃችን ናፍቆት የተወለደው:: በትግል መድረክ ላይ እያለን ማለቴ ነው:: ከዛም በኋላ የጋራ ህይወታችን የተጀመረው በዚሁ የትግል መድረክ ውስጥ ነው:: ከስር መሰረቱ ጀምሮ ህይወታችን በአጠቃላይ ከትግሉ ጋር የተሳሳረ ነው፤ ስለዚህ የእኛ ውሳኔ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ውሳኔ ነው:: የኛ ቤተስብ በዚህ በኩል የተለየ ነው:: ሁሉም ሰው ደግሞ በዚህ አይነት ሒደት ውስጥ ማለፍ አለበት ተብሎ አይታሰብም:: ሊያልፍም አይችልም:: ወደድንም ጠላንም ሁላችንም የራሳችን ጠበብ ያለ ቤተሰብ አለን፤ ሰፋ ሲል የህዝብ ቤተሰብ አለን:: ህዝቡም የቤተሰባችን አካል ነው:: ስለዚህ አጠቃላይ ቤተሰባችን ደግሞ ህዝቡ በመሆኑ ለህዝቡ የምንወስነው አለ:: የቤተሰባችን ህልውና ከህዝቡ ህልውና ጋር የተመጣጠነ ምልክታችን ነው:: ቤተሰብን ማስቀደም የሚል ሰው ካለ መልካም ነው እረዳዋለሁ:: ደካማ ሰው አድርጌ አልመለከተውም፤ እንደ ሰውዬው ጉዳይ መታየት አለበት፤ አይ ህዝቤ ይበልጥብኛል ያለውም ሰው እንደ ጀግና መታየት የለበትም:: ይሄ ጀግና አያሰኝም፤ ወይም አገራችንን ይበልጥ ስለምንወዳት አይደለም::

**ግዮን፦ ከዓመታት በኋላ በስደት ያሉ የነፃው ፕሬስ አባላትን አግኝተሃቸዋል፤ የነበረህ ቆይታ እንዴት ነበር?**

**እስክንድር**፦ በጣም ደስ የሚል አጋጣሚ ነበር:: ከኬኒያ ልጀምር፤ ወደ አሜሪካ ከመምጣቱ ከቀናት በፊት ኬንያ ሄጄ ነበር፤ በርካታ የነፃው ፕሬስ አባላቶች አሉ:: በኬኒያ አራትና ከዛ በላይ ዓመታት ያስቆጠሩ፤ አገራቸውን ሳይወዱ በግድ ለቀው በስደስት ተቀምጠዋል:: ከእነሱ ያነሰ ምክንያትና መረጃ ያላቸው ከኋላቸው መጥተው ቀድመው አውሮፓና አሜሪካ ገብተዋል:: እነዚህ ግን አሳማኝ ማስረጃና ረጅም ጊዜ የነበራቸው ግን ወደኋላ ተጎትተዋል:: ቤት ኪራይ ቀርቶ የሚመገቡበት ገቢ የላቸውም:: አሳዛኝ ነው:: የነሱንም ጉዳይ በተገኘንበት መድረክ እያስረዳን ነው:: እዚህ አሜሪካ በስድት የገቡ ጋዜጠኞችንም አግኝቻለሁ:: እነ ሲሳይ አጌና፣ ዳዊት፣ አበበ፣ ቶማስን የመሰሉ የፕሬስ ልጆችን አግኝቻለሁ:: ሙያቸውን ሳይለቁ የኢትዮጵያን ህዝብ ጭቆናና በደል፤ ሰቆቃና ግፍ፤ ዴሞክራሲና ነፃነት ላጣው ወገናቸው ድምፅ ሆነው እየጮኹለት ይገኛሉ:: በአካል ከዓመታት በኋላ ስንገናኝ ደግሞ ከፍተኛ ደስታ ነው የተሰማኝ:: ተጨዋውተናል፤ ትግሉ መቀጠል እንዳለበትና የዲሞክራሴ ጥያቄ እስኪመለስ ድረስ ማፈግፈግ እንደሌለ ተነጋግረናል::

**ግዮን፦ ሀገር ውስጥ ላለው ወገንህ የምታስተላልፈውን መልዕክት የውይይታችን መቋጫ አድርገውና እንሰነባበት?**

**እስክንድር፦** አመሠግናለሁ:: ዋናው ጥያቄአችን የዴሞክራሲ ጥያቄ ነው:: ይሄ ጥያቄ አልተመለሰም:: በተጨማሪ በየማጎሪያው ያሉ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ሙሉ ለሙሉ አልተለቀቁም:: ሁሉንም ያማከለ ሽብርተኛ የተባሉትን የፖለቲካ ኃይሎችን ጭምር ያቀፈ አገራዊ ውይይት አልተካሄደም:: ከዛ ባለፈ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁም አልተነሳም፤ እነዚህ ጉዳዮች ምላሽ እስኪያገኙ ድረስ ትግሉ ይቀጥላል፤ እኔም እመጣለሁ፤ አሜሪካ ለመቅረት ለሰከንድ አላስብም::



ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)

# የአማራ ምሁራንና ብአዴን ከጣውንትነት ወደየት?

ከሚያዝያ 12-14 በውቢቱ ባህር ዳር ከተማ የተካሄደው የአማራ ምሁራን የምክክር መድረክ ፣ በዓይነቱ ለየት ያለና በክልሉና ከክልሉ ውጭ የሚኖሩ ከ300 በላይ ምሁራንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የታደሙበት ነበር:: በዚህ የክልሉ መንግስት በጠራው የሶስት ቀን ጉባኤ በዋነኝነት ም/ርዕሰ መስተዳድር አቶ ብናልፍ አንዷለምና የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ሃላፊው አቶ ንጉሡ ጥላሁን የተገኙበት ሲሆን ፣ ርዕሰ መስተዳድሩ አቶ ገዱም ከጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ጋር በሁለተኛው ቀን ከመጡ በኋላ የመድረኩን መሪነት ተረክበው እስከመደምደሚያው ዘልቀዋል::በተረፈ በፀረ-አማራነታቸው የሚመፃደቁት አሮጌ የህወሃት-ብአዴን አምበሎች አንዳቸውም ዝር አላሉም:: በትክክል የዘመኑ ንፋስ መለወጡን አሸትተው ይሆናል::

ይህ የምክክር መድረክ ከጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ጉብኝትና ከጣና የመሪዎች ፎረም ጋር መደራረቡ ፣ ጉልህ የጥድፊያ ምልክቶች የሚታይበት መሆኑ ፣ እንዲሁም በመድረኩ መርሃ ግብር በመነሻ ሃሳብነት ሊቀርቡ ከተዘረዘሩት ወረቀቶች ውጭ የውይይቱን አቅጣጫና መድረሻ ግብ የሚጠቁሙ ትልሞች አለመኖራቸው ሲታይ ፣ የክልሉ መንግሥት በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የምሁሩን ትርታ ከመሰለል ያለፈ ፍላጎት አለው ወይ ያሰኛል::

በተጨማሪም በኦሮምያና በትግራይ ከተጠሩት ተመሳሳይ መድረኮች በኋላ የተከተለ በመሆኑ የበላይ ትዕዛዝ ዓይነት ጥርጣሬ በታዳሚው ዘንድ አሳድሯል:: ነገር ግን የክልሉ ባለስልጣናት ለረዥም ጊዜ አቅደነው የከረመ ጉዳይ ነው ሲሉ አስተባብለዋል::

የኢህአዴግ ግርፍ የሆነው ብአዴን ከምሁሩ መደብ ጋር በቋጠረው ደመኝነት የተነሳ ፣ አገልጋይ ሲያሰኘው ብቻ እየመለመለ ያሰማራል እንጂ ከአማራ ምሁራን ጋር ከልብ ተመካክሮ አያውቅም:: እንዲያውም የአማራ ምሁራን የኢህአዴግ መንግሥት ዋነኛ ዒላማዎች ሲሆኑ ፣ በውሃ ቀጠነ ከየስራቸው ሲባረሩ ፣ በሃላፊነት እንዳያገለግሉ ሲገለሉ ፣ በእኩልነት ተወዳድረው የሚኖሩበት ፍትህ ሲነፈጋቸው ፣ በየስብሰባው ስምና ታርጋ እየተለጠፈላቸው ሲወገዙ ፣ በአጠቃላይ ከጨዋታ ውጭ እንዲሆኑና አንገታቸውን እንዲደፉ ሲዘመትባቸው ብአዴን በፊታውራሪነት ተሳትፏል:: ስለዚህም ከዚህ የህብረተሰብ ክፍል ጋር አይተማመንም ፣ ከናካቴው የሚግባባበት የጋራ ቋንቋ እንኳን የለውም::

በድንገት ወደ ጉባኤው የተጠራው ምሁር የመጀመሪያ ጥያቄ ‹‹ስለምንድነው የምንመካከረው?›› የሚል ቢሆን አያስገርምም:: ነገር ግን ተሰብሳቢው በአማራው ህዝብ እጣፈንታ ላይ ካደረበት ተቆርቋሪነት በመነሳት ፣ በአንድ መንፈስ የምክክሩን ሂደት አቅጣጫና ግብ ለማስተካከል ሞክራል::

ጥሪውን አክብሮ የመጣው አካዳሚያዊ ትንታኔዎችን ለማዳመጥ ሳይሆን ፣ በአማራ አንገብጋቢ ብሄራዊ ጥያቄዎች ዙሪያ መወያየትና ለመፍትሄው ከክልሉ መንግሥት ጋር መሥራት ይችል እንደሆን ለመወሰን መሆኑን በአፅንኦት አስገንዝቧል:: በዚህም መሰረት በሶስቱ ቀናት ውይይቶችና ምክክሮች ያጠነጠነባቸው አበይት ርዕሶች የአማራውን ህዝብ የህልውና አደጋ ፣ የብአዴንን ያለፈና መፃኢ ሚና ፣ እንዲሁም የአማራ ብሄርተኝነትና የምሁሩን ሚና የሚመለከቱ ነበሩ:: በአጭር በአጭሩ ላቅርባቸው::

## ሀ. አማራና ህልውናው

ለአማራ ብሄር እንቅልፍ ላለመስጠት የተማማለው በትህነግ/ወያኔ የሚመራው ኢህአዴግ ፣ የአማራውን ህዝብ በሁሉ መንገድ ለማዳከም ለ27 ዓመታት በመሬቱ ፣ በሀብቱ ፣ በክብሩና ማንነቱ ላይ ግልፅና ስውር የጥቃት ዘመቻ ከፍቶበታል:: አማራው ከብሄራዊው ማህበረሰብ አባልነቱ ተዋርዷል ፣ ከጋራ ማዕዱ እንዳይቋደስ ተገፍቷል:: በገዛ አገሩ ተዘዋውሮ እንዳይኖር ፣ እንዳይሰራ ፣ እንዳይነግድ ፣ ሀብት እንዳያፈራ ተፈርዶበታል:: አማራው ክልልህ የተባለው ግዛት እንኳን ባለቤት አለመሆኑ ፣ ከሌሎች ክልሎች ህገ መንግሥቶች በተለየ በወረደለት ህገ መንግሥቱ በግልፅ ተደንግጎበታል::

አማራው በክልሉም ከክልሉም ውጭ ለከፍተኛ የህይወትና የንብረት ኪሳራ ፣ ለፅኑ የሥነልቡና ጥቃት ተጋልጧል:: ታሪኩ ተበርዟል ፣ ጠልሽቷል:: ለአገር የከፈለው ልፋቱ ፣ መስዋዕትነቱ ተክዷል:: ጥላቻና ቅጥፈት በፖሊሲ ተቀርፆ ፣ በሥርዓተ ትምህርት ታግዞ ተነዝቶበታል:: በዚህ ሁለገብ ወረራ አንገቱን ለመድፋት ፣ ማንነቱን ለመሸሽ ተገድዷል:: ‹‹አማራ ነኝ›› ከማለት ይልቅ ‹‹ከአማራ ክልል መጣሁ›› ፣ ‹‹አማርኛ








ከቤኒሻጉል የተፈናቀሉ አማራዎች በባሕር ዳር

ተናጋሪ ነኝ›› ይላል:: አልፎም ‹‹ኢትዮጵያዊ እንጂ አማራ የለም›› የሚል የሸሸት ስልት የሙጥኝ እስከማለት ተደርሷል::

በዚህ ሞልቶ በፈሰሰ ግፍና ጥቃት ምክንያት ፣ በምክክሩ ወቅት ከተነሱት ርዕሶች ጎልቶ የወጣው የአማራው ህዝብ በህልውናው ላይ ካንዣበበው አደጋ እንዴት ይውጣ የሚለው ጉዳይ ነበር:: በተለይም ደግሞ የወልቃይትና የራያ ህዝቦች ፣ የተከዜና የአባይ ምላሽ ግዛቶች ፣ እንዲሁም ከአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ውጭ የሚኖሩ ብዙ ሚሊዮን አማሮች እጣፈንታ የአማራ ብሄርተኝነት የደም ስር እንደሆነ ታይቷል::

በ‹‹አባይ ትግራይ›› የተስፋፊነት ቅዠት የሚናውዙ ጊዜ የሰጣቸው ልሂቃን ፣ ለአማራው አባቶቹ በደማቸው ያኖሩለትን አፅመ ርስቱን ነጥቀውታል ፣ አስነጥቀውታል:: በየዘመኑ ከሚነሱ ወራሪ ሃይሎች በህይወቱና በአካሉ ለመከተላቸው ውለታ ክፍያ በገዛ ባድማው ባይተዋርና ተሳዳጅ አድርገውታል:: የትግራይንም ህዝብ በሰሜን ከኤርትራ በደቡብ ከአማራ በግዛት ይገባኛል ስንጥቅ ውስጥ ከትተውታል:: ጉልበት የወሰደውን ጉልበት እስኪመልሰው ድረስ በነዚህ ወንድማማች ህዝቦች መካከል የሰላም እንቅልፍ አይኖርም::

ትህነግ/ወያኔ እስከዛሬም የጠላትነት ማኒፌስቶውን አልቀደደም:: በአማራው ህዝብ ላይ በፈፀመው ግፍ አልተፀፀተም ፣ ይቅርታም አልጠየቀበትም:: እንዲያውም የጦር ድቤ እየጎሰመ ነው:: ለመሆኑ ከጓሮው ባድሜን ለማስመለስ አቅም ያጣ ቡድን ፣ የአማራን መሬት ነጥቄና አስነጥቄ በዋዛ ፈዛዛ እኖራለሁ ብሎ ማሰቡ የጤንነት ነውን ? ይህንን ትልቅ አስተዋይነት የጎደለውና ትውልዶችን ደም የሚያፋስስ ጉዳይ እንደ ተራ የህገ መንግሥት ጥያቄ ማየት ታሪክ ይቅር የማይለው ስህተት ነው:: ይልቅስ ብቸኛው መፍትሄ ሰከን ብሎና ሃፍረትን ዋጥ አድርጎ ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ መሬቱን ለባለቤቱ መመለስ ነው::

በትጋት የተሰራበት የአማራን ህልውና የማጥፋት ዘመቻ ፍሬው በገሃድ እየታየ ነው:: በአለማቀፍና አገራዊ ጥናቶች እንደተረጋገጠው የአማራ ክልል በትምህርት ፣ በጤና ፣ በመሰረተ ልማት ፣ በኢንዱስትሪ በየትኛውም ሰብዓዊ ልማት መለኪያ የአገሪቱ ጭራ ነው:: በህፃናት አቀንጭር ፣ በወላድ እናቶች ሞትና በመሳሰሉት ወሳኝ የህልውና መስፈርቶች ደግሞ ፊት መሪ ነው:: እጅግ የሚከነክነው ክልሉ ከአፈፃፀሙ በብቸኝነት የተሳካለት የቤተሰብ ምጣኔ ጉዳይ ነው:: ይህ ከመስመር ያፈነገጠ ‹‹ስኬት›› ሁለትና ሶስት ሚሊዮን ህዝብ እንደዘበት ጠፋ በሚባልበት ክልል ብዙ ጥያቄ ያስነሳል::

እንደሚታወቀው በቤተሰብ ምጣኔና በዘር ማጥፋት መካከል ያለው ቀጭን መስመር ፈቃደኝነት ይባላል:: በታህሣሥ 1941 የጸደቀው A/RES/260A(III) ደንብ ‹የዘር ማጥፋት ወንጀልን ስለመከላከልና መቅጣት ስምምነት› አንቀጽ 2 መሰረት፣ ዘር ማጥፋት የሚባለው አንድን ብሄረሰብ ፣ ዘውግ ፣ ዘር ወይም ኃይማኖታዊ ማህበረሰብ በጠቅላላው ወይም በከፊል ለማውደም በማሰብ የሚከተሉት አምስት ተግባራት ሲፈጸሙ ነው:: 1/ የቡድኑን አባላት መግደል፤ 2/ በቡድኑ አባላት ላይ ፅኑ አካላዊ ወይም አእምሮአዊ ጉዳት ማድረስ ፤ 3/ ሆን ተብሎ በማህበረሰቡ አኗኗር ላይ በሙሉ ወይም በከፊል አካላዊ ጥፋት ለማስከተል የተሰላ እርምጃ መውሰድ፤ 4/ በማህበረሰቡ ውስጥ ወሊድ እንዳይደረግ የታለመ እርምጃ መጫን ፤ 5/ የማህበረሰቡን ህጻናት በግድ ወደሌላ

ትህነግ/ወያኔ እስከዛሬም የጠላትነት ማኒፌስቶውን አልቀደደም:: በአማራው ህዝብ ላይ በፈፀመው ግፍ አልተፀፀተም ፣ ይቅርታም አልጠየቀበትም:: እንዲያውም የጦር ድቤ እየጎሰመ ነው:: ለመሆኑ ከጓሮው ባድሜን ለማስመለስ አቅም ያጣ ቡድን ፣ የአማራን መሬት ነጥቄና አስነጥቄ በዋዛ ፈዛዛ እኖራለሁ ብሎ ማሰቡ የጤንነት ነውን ?

ማህበረሰብ ማዛወር ናቸው:: የአማራው ህዝብ ከነዚህ ውስጥ ምን ያልደረሰበት ነገር አለ ? ከያቅጣጫው እንደምንሰማው ክልሉ ይህንን ውጤት አስመዘገብኩ ብሎ የሚኩራራው እናቶችን ያለፈቃዳቸው በማምከን ፣ በገዛ ወገኖቹ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል እየፈፀመ ነውን ? ገና ይህንን ክስ የሚያስተባብል ወገን አልታየም::

## ለ. የብአዴንን የማያኮራ ሚና በተመለከተ

ኢህዴን የተባለው የብአዴን አባት መጀመሪያ ኢህአፓን በኋላም አማራውን የሸጠ ከዳተኛ ጥርቃሞ ነው:: ገና ከማለዳው በአማራው ላይ ለተፈፀሙት አበይት ወንጀሎች አባሪ ተባባሪ ነበር::

እንደሚታወቀው በሃምሌ 1983 ዓ.ም የሰላምና ዲሞክራሲ ጉባኤም ሆነ በሽግግሩ መንግሥት ግልጽ ውክልና ያላገኘ ብሄረሰብ ቢኖር አማራው ነበር:: ጥቂት ቆይቶ አማራው ከየአካባቢው ሲዋከብና ሲገደል ፣ ተቆርቋሪ አጣ ሲባል ቆዳ መቀየር የተካነው ኢህዴን የአማራው አባት እኔ ነኝ ብሎ ብቅ አለ::

ይህ ቡድን የመከፋፈል ሴራውን የጀመረው በ1984 ዓ.ም በባህር ዳር ባደረገው ‹የጭቁን አማሮች› በተሰኘው አስቂኝ ጉባኤ ነበር:: ለጥቆም አማራውን መነጠል ፣ ማዋከብና ማምከን በእጅ አዙር ኢትዮጵያዊነትን የማጥፊያ ስልት አድርጎ መሰረተ:: አማራውን መስደብ በኢህዴን ዘንድ የሚያሾም የሚያሸልም ሆነ::

ይህ ማህበረሰብ የታሪክን ጉድፍ እንዲሸከም ፣ የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማው ግልጽና ረቂቅ የስነልቡና ዘመቻዎች አወጀ:: የማንነት ቀውስ የሚንጣቸው የኢህዴን ወፌፌ ካድሬዎች አማራውን ግዳይ ጥለው ለመሸለም መሽቀዳደም ዋነኛው መለያቸው ሆነ::

ታዲያ ብአዴንስ የእባብ ልጅ አይደለምን? የአማራው ህዝብ ለሁለት አሥርት አመታት ፍዳውን የሚያስቆጥር ርብርቦሽ የተደረገበት በብአዴን ጋሻ ጃግሬነት ነበር:: ብአዴን እስከዛሬ ከክልሉ ውጭ ከቀያቸው በሚፈናቀሉ ፣ በውሃ ቀጠነ ከሥራቸው በሚባረሩ አማሮች ላይ ሲመቸው ይሙት በቃ እየፈረደ ፤ሳይመቸው ከደሙ እጁን እየታጠበ ቆይቷል:: ከክልሉ ውጭ ለሚኖር አማራም እቆማለሁ የሚል ደምፁን በለሆሳስ ያሰማው ከ20 ዓመታት በኋላ ዘንድሮ ገና የፊጥኝ ሲያዝ ነው:: በዚህ የከረፋ ማህደሩ የተነሳ ዛሬም ብአዴን ከችግሩ ወደ መፍትሄው አካልነት ለመሸጋገርና ቁርጠኛ የሰላም ሃይል ሊሆን ስለመቻሉ ብዙዎች ጥርጣሬ አላቸው::

በውይይቱ የተነሳው ፅኑ ወቀሳም ብአዴን የአማራን ህዝብ ቁመና የማይወክልና የአማራ ወዝ የሌለው ጎፍላ ድርጅት ነው የሚል ነበር:: ታዳሚው የሰነዘራቸው ‹‹አማራን በአናቱ ላይ ቂጥ ብለው የሚዛበቱበትን መሪዎች አቅፋችሁ እስከመቼ ነው የምትዘልቁት?›› ‹‹የአማራ ብሄር ጠላቴ ናት ብሎ ከሚሰብክ ድርጅት ጋር ተጋብታችሁ የምትኖሩትስ በማን ስም ነው ?›› የመሳሰሉት ጥያቄዎች ከብአዴን አመራሮች አጥጋቢ ምላሽ አላገኙም:: እስከ ዶቃ ማሰሪያችን ብትነግሩን እንቀበላለን በሚል ታልፈዋል::

ነገር ግን በቅርብ ጊዜ በድርጅቱ መካከለኛና የበታች አመራር ውስጥ እየተጠናከረ የመጣው የአማራ ተቆርቋሪነት ፣ ድርጅቱ በብሄራዊው የፖለቲካ መድረክ ያንፀባረቀው የነፃነት አቋምና በአጠቃላይ በአገሪቱ የናኘው የለውጥ ንፋስ ተደራርበው ብአዴን አዎንታዊ ሃይል ሊሆን የሚችልበት ጭላንጭል የሚታያቸው አልጠፉም:: አንድ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ብአዴን ራሱ ፅኑ የህልውና አደጋ ተጋርጦበታል:: ስለዚህም በወቅታዊ አቋሙ ከጌቶቹም ከህዝቡም ያጣ መሃል ሰፋሪ ሆኖ መቀጠል አይችልም:: እንዴት እንሂድበት እንመካከር የሚለውም መድረክ ከዚህ የመውጫ ቀዳዳ ፍለጋ የመነጨ ይመስላል::

ብአዴን ከህዝብ የመጣበትን የበቀል ቁጣና ከአማራው ብሄራዊ ንቅናቄ ያንዣበበትን ማዕበል ለመቋቋም ፤ አጋሩ ኦህዴድ እንዳደረገው የህዝብን አመኔታ ለማግኘትና አነቃንቆ ከጎኑ ለማሰለፍ እንደገና መወለድ ይኖርበታል:: ይህ ከተፈለገ ርዕዮታዊ ፣ ስልታዊና መዋቅራዊ አብዮት ማካሄድ የግድ ነው:: በመጀመሪያ ራሱን ከባርነት ነፃ አውጥቶና መቅለስለሱን ትቶ በግልፅ የአማራ ወገንተኝነት ማሳየት አለበት:: የጌቶቹን ፊት እያየ ሳይሆን የአማራውን ጥቅም እያሰበ ፣ ከህዝብ የሚያቀራርብ ስራ በመሥራት ለሃጢአቱ ንሠሃ መግባት ይኖርበታል:: ሁለተኛ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ፣ ልማታዊ መንግሥት ፣ ብሄር ብሄረሰቦች ምንትሴ የሚባሉትን ውዥንብሮች ወዲያ ጥሎ ፣ የአማራን ብሄርተኝነት በኢትዮጵያዊነት ማዕቀፍ ውስጥ ለማራመድ መዘጋጀት ወሳኝ ነው:: በአማራው ውርደት የከበሩ ቅጥረኞችንና ፊርማቶሪዎችን ከመዋቅሩ ጠራርጎ በማስወገድ ፣ በአዳዲስና ለህዝባቸው ቀናኢ በሆኑ ወጣት አመራሮች መተካትም ያስፈልገዋል::

ለዚህም መላውን የአማራን ህዝብ

ቀሪውን በገጽ 22 እና 23 ይመልከቱ

# ግንቦት ወር በ ታ ሪ ክ ው ስ ጥ

**ግንቦት 1 ቀን 1849 ዓ.ም.**
ልዑል ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል የሸዋ ንጉስ የነበሩ፤ ከሳህለ ሥላሴ ልጅ ከልዕልት ተናኘ ወርቅና ከደጅአዝማች ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ አባጉራች በ1849 ግንቦት 1 ቀን ጎላ ወረዳ ደርፎ ማሪያም በሚባል ስፍራ ተወለዱ።

**ግንቦት 9 ቀን 1860 ዓ.ም.**
የዓፄ ቴዎድሮስ ሚስት የልዑል አለማየሁ እናት እቴጌ ጥሩወርቅ በዚህ ቀን አረፉ።

**ግንቦት 17 ቀን 1870 ዓ.ም.**
ዓፄ ዮሐንስ ዘ ኢትዮጵያ እና የሸዋው ንጉስ ምንሊክ በተገኙበት በወሎ ቦሩ ሜዳ ላይ የተካሄደው የኃይማኖት ክርክር እልባት አገኘ።

**ግንቦት 15 ቀን 1907 ዓ.ም.**
አቤቱ እያሱ አባታቸውን ራስ ሚካኤልን ደሴ ላይ ንጉሠ ወሎ ወትግሬ ብለው አነገሷቸው።

**ግንቦት 25 ቀን 1921 ዓ.ም.**
የግብፅ ቤተክርስትያን ቅዱስ ሲኖዶስ የመጀመሪያዎቹን አራት ኢትዮጵያዊያንን፤ አቡነ አብርሐም የጎንደር እና የጎጃም፣ አቡነ ይስሃቅ የትግሬ እና የሠሜን፣ አቡነ ጴጥሮስ የወሎ እና የላስታ፣ አቡነ ሚካኤልን የኢሉባቡር እና የምዕራብ ኢትዮጵያ ጳጳሳት ሆነው በግብፃዊው ሊቀጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ በካይሮ ላይ ተቀብተው ተሾሙ።

**ግንቦት 1 ቀን 1928 ዓ.ም.**
የኢጣልያ ንጉሥ ቪክቶር ዓማኑኤል ሳልሣዊ ከዚህ ቀን ጀምሮ የኢትዮጵያ ህዝብና ግዛት የኢጣልያ አስተዳደር ስር መሆናቸውን ለዓለም መንግሥታት አሳወቁ። ከዚያን ዕለት ጀምሮ በኢጣልያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት እንደራሴ ማዕረግ በሚሾሙት ተወካዮችዋ አማካኝነት ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን እንደምታስተዳድር የሚገልፅ አዋጅ ይፋ አደረጉ።

**ግንቦት 8 ቀን 1930 ዓ.ም.**
የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት መሥራች ኢትዮጵያዊው የሙዚቃ ምኁር ዶክተር አሸናፊ ከበደ ግንቦት 8 ቀን 1930 ዓ. ም. ተወለዱ። በተወለዱ በስድሣ ዓመታቸው በዚሁ ቀን 1990 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

**ግንቦት 1 ቀን 1952 ዓ.ም.**
ዓፄ ኃይለ ሥላሴ በአገራቸው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የሚገቡ ኃይሎች መኖራቸውንና፤ እነዚህም ኃይሎች መንግሥታቸውን እንደተፈታተኑት በመግለፅ ከፈረንሳይ፣ አሜሪካ፣ ግብፅ፣ ሶቪየት ህብረት፣ ብሪታኒያ እና ዩጎዝላቪያ ዲፕሎማቲክ ሚሽን ተጠሪዎች ጋራ ተወያዩ።
በስብሰባቸው ማግስት አምባሳደሮቹን ጠርቶ ለማነጋገር የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የተገደደው በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ጉዳዮች ላይ የባዕዳንን ጣልቃ ገብነት በብርቱ እንደሚቃወም እና በኢትዮጵያ ግዛትና ሉዐላዊነት ላይ ለሚሠነዘሩ ማንኛቸውም ጣልቃ ገብነቶችን ለመመከት ዝግጁ መሆኑን እንዲገነዘቡ ለማሳሰብ መሆኑን አሳወቁ።

**ግንቦት 9 ቀን 1952 ዓ.ም.**
የኤርትራ የህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትተዳደር ተስማምቶ የፈቀደውን ህገ-መንግሥት በመሻር የኤርትራን የራስ ገዝ አስተዳደር መንግሥት ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት መንግስት ጋር እንድትዋሃድ የሚያስችላትን ውሳኔ አፀደቀ።

**ግንቦት 24 ቀን1953 ዓ.ም.**
በኢትዮጵያ ታሪክ እስከ አሁን ተወዳዳሪ ያላገኘ በሬክተር ሥኬል ስድሥት ነጥብ ሠባት የተመዘገበ የመሬት መንቀጥቀጥ ተከስቶ በሰሜን ሸዋ የምትገኘውን የማጀቴን ከተማ ሲደመስስ አጎራባችዋን ካራቆሬን ደግሞ ከመቶ እጅ አርባ አምስት ፐርሰንቱን አወደመ።
በካራቆሬ በስተሠሜን ከአዲስ አበባ አስመራ የሚያገናኘው መንገድ ላይ ያሉ ድልድዮችን ከመጉዳቱ በላይ መቶ አስራ ሠባት ኪሎ ሜትር የድንጋይ ናዳ ጉዳት አድርሷል።

**ግንቦት 15 ቀን 1955 ዓ.ም.**
የ32 የአፍሪካ አገራት መሪዎች አዲስ አበባ ላይ ተሰብስበው የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን መሠረቱ ።

**ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም.**
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ሁለተኛው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ አቡነ ቴዎፍሎስ ሥርዐተ ሲመት በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተከናወነ።

**ግንቦት 15 ቀን 1963 ዓ.ም.**
በአዲስ አበባ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አደባባይ በመውጣት በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ከማሠማታቸው በተጨማሪ የአንበሳ ከተማ አውቶብሶችና የመንግሥት ንብረቶችን አወደሙ። ይህንንም ተከትሎ አስር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተወሠነ ጊዜ እንዲዘጉ ተደረገ።

**ግንቦት 15 ቀን 1966 ዓ.ም.**
የኤርትራ ነፃነት ግንባር አባላት ጊንዳ ውስጥ በሉተራን ሚሲዮን ሆስፒታል ውስጥ የሚሠራ ኢጣልያዊ ዶክተርን ለመጥለፍ ሞከሩ፤ በዚህ እንቅስቃሴያቸው አንዲት አስታማሚ ኢጣልያዊት ነርስ ተገደለች።

**ግንቦት 15 ቀን 1966 ዓ.ም.**
የጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን መንግሥት የሚኒስትሮች ለውጥን ይፋ አደረገ። በዚህም መሠረት የአገር ግዛት ሚኒስትር የነበሩትን ደጃዝማች ዘውዴ ገብረስላሴን ወደ ውጪ ጉዳይ ሚኒስትርነት ማዘዋወሩን አሳወቀ።

**ግንቦት 23 ቀን 1966 ዓ.ም.**
የየካቲቱን ህዝባዊ ዓመፅን ተከትሎ በንጉሠ ነገሥቱ ይሁንታ የተቋቋመው የመርማሪ ኮሚሽን ሥራውን የሚሠራበት ህግና ማዕቀፍ በህዝብ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት ፀደቀ።

**ግንቦት 17 ቀን 1966 ዓ.ም.**
የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የአሩሲ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ የነበሩትን አቶ ተስፋዬ ቡሽን የጠቅላይ ግዛቱ ህዝብ ከሥልጣናቸው አባሮ አስወጣቸው።

**ግንቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም.**
በኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማርያም የሚመራውን የኢሕድሪ መንግሥት ከሥልጣን ለማሥወገድ በአገሪቱ ከፍተኛ የጦር አዛገሮች የተቀነባበረ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ተካሄደ።
መፈንቅለ መንግስቱ በኮሎኔል መንግስቱ ታማኝ ወታደሮች ጥረት የከሸፈ ሲሆን በመንግሥት ግልበጣ ኩዴታው ላይ የተሳተፉትን የጦር አዛገሮች በሙሉ በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ትዕዛዝ በሞት እንዲቀጡ ተደረገ።

**ግንቦት 7 ቀን 1983 ዓ.ም.**
ህዝባዊ ግንባር ለፍትሕና ለዴሞክራሲ (ሻዕቢያ) መላዋን ኤርትራ በመቆጣጠር በኤርትራ ጊዜያዊ መንግሥት መመሥረቱን አሳወቀ። ከዚህ ዕለት አንስቶ የእሥራኤል መንግሥት በኢትዮጵያ ይገኙ የነበሩትን 14 ሺህ 325 ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን በ36 ሠዓት ውስጥ በ44 የእሥራኤል አውሮፕላኖች አጓጉዛ ወሰደች።

**ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም.**
የኢሕድሪ ፕሬዝዳንት፤ የኢሠፓ ዋና ጸሐፊ እና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አገር ጥለው በመኮብለል ወደ ዙምባብዌ ተሰደዱ።

**ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም.**
የኢህአዴግ ጦር መላውን የኢትዮጵያ ግዛት መቆጣጠሩን አሳወቀ። በወቅቱ የኢህአዴግ ጦር ወደ መዲናይቱ አዲስ አበባ እንዲገባ የወሠኑትና በለንደን የሰላም ድርድሩን ይመሩ የነበሩት የአሜሪካ ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ሚኒስትር ኸርመን ኮኸንን ፈቃድ ተከትሎ ኢህአዴግ አዲስ አበባን ተቆጣጠረ። የጊዜያዊ መንግሥቱ ፕሬዘዳንት መለስ ዜናዊም ቀናት ሳይቆዩ አዲስ አበባ ገቡ።

**ግንቦት 4 ቀን 1990 ዓ.ም.**
በፕሬዚዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ የሚመራው የኤርትራ መንግሥት ጦር በሰሜን ኢትዮጵያ የሉዓላዊነት የግዛት ድንበርን በመጣስ ወረራ አካሄደ። በዕለቱ የተጀመረው የሁለቱ አገራት የድንበር ውዝግብ አሁንም መፍትሄ ሳያገኝ በእንጥልጥል ላይ ይገኛል።



በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

# ከአርበኛው ጋር በአርበኞች ቀን

በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

‹‹ልጄ!››

‹‹አቤት አባባ!››

‹‹ይኼን አሮጌ ፎቅ ማን እንደሠራው ታውቃለህ?›› ፊት ለፊት ወደሚታየው አሮጌ ህንፃ እየጠቆሙኝ፡፡

‹‹አላውቅም አባቴ!››

‹‹ጥልያን ነው፤ ያ ፈሳም ጥልያን!››

‹‹ይገርማል!›› አልኩ ለማዳነቅ ያህል፡፡

‹‹ጥልያንንስ ፈሱን እያስረጨ ታገር ያስወጣው ማን እንደሆነ ታውቃለህ?››

‹‹አውቃለሁ አባቴ!››

‹‹ማን ነው?››

‹‹እናንተ ናችኋ፤ ጀግኖች አባቶቻችን!››

በጣም ደስ አላቸው፡፡ ደረታቸው ላይ የደረደሩትን ሜዳሊያ በፈገግታ እየቃኙ፤ ‹‹እውነት ነው፤ ያን ሶላቶ ታገር ያበረርነው እኛ ነን!››

ዕድሜያቸው ወደ ሰማንያዎቹ መጨረሻ የሚጠጋ አዛውንት ናቸው፡፡ ከወገባቸው ሰበር ብለዋል፡፡ በለበሱት ዕድሜ የተጫነው ኮት ላይ ሦስት ያረጁ ወርቃማ ሜዳሊያዎችን አንጠልጥለው፣ በአረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለም የተሽለመ አጭር ዱላ ይዘው፣ በባንዲራ ጥለት ዙሪያውን የተቀመቀመ የወታደር ቆብ አድርገው በዝግታ እየተራመዱ ነው፡፡ ድንገት ቀና ብለው የመኪና መንገድ ሊሻገሩ ሲያንገራግሩ አጠገባቸው ደርሼ፣ ‹‹አባባ ላሻግርዎ?›› አልኳቸው፡፡

‹‹እሺ!›› አሉኝ አንድ እጃቸውን ወደኔ እየሰደዱ፡፡ እጄን ሰጠኋቸው፤ ጠበቅ አድርገው ያዙኝ፡፡

‹‹ወዴት እየሔዱ ነው?›› አልኩ ጥቂት ከተጓዝን በኋላ፣ ጨዋታ ለመጀመር ያህል፡፡

‹‹ወደ አርበኞች መታሰቢያ ሐውልት!››

‹‹የት ነው እሱ?›› አልኳቸው ድንገት የነገሩኝን ብዙም ግምት ሳልሰጠው፡፡

‹‹አራት ኪሎ ነዋ! …አይ እናንተ!›› በትዝብት ዓይነት ራሳቸውን ነቀነቁ፤ ሐውልቱን አውቀዋለሁ፤ ልብ ሳልል እሳቸውን በመጠየቄ እፍረት ተሰማኝ፡፡

‹‹ታሪክን ሳታውቁ፣ ባንዲራ ለብሳችሁ ወዲያ ወዲህ ብትሉ ምን ዋጋ አለው!? …ዙሪያችንን የሚከቡን ወጣቶች ሁሉ በዚህ በስልክ ፎቶ ማንሳት፣ በእጀ ጠባብና በቀሚስ ተሸቀርቅሮ ከመውጣት ውጪ ታሪኩን ምኑንም አያውቁት!››

‹‹እውነትዎን ነው!›› አልኩ ራሴንም ተወቃሽ አድርጌ፡፡

‹‹ይምጡ ባይ፣ ይሰብሰቡ ባይ፤
ሲሰበሰቡ አነሱብኝ ባይ፤
ይምጡ፣ ይምጡ ይከማቹ፤
ለአንድ ሰው እንዲመቹ!

‹‹…እያልን እየፎከርን ነው ጥልያንን ፈሱን እያስረጨን ካገር ያስወጣነው፡፡››

ዛሬ ሚያዚያ 27 ነው፤ የአርበኞች ቀን፡፡ አባትም በጠዋት ከቤታቸው የወጡት ይህንኑ በዓል ለማክበር ነበር፡፡

‹‹ይኸው በየዓመቱ በዓል በመጣ ቁጥር ይጎትቱናል!›› አሉ አዛውንቱ በመታከት፡፡

‹‹እነማን አባቴ?››

‹‹ሰዎቹ!››

‹‹እነማን ናቸው ሰዎቹ!?››

‹‹አዬ ልጄ፤ …ተወው እስኪ!››

የምናገረው ባጣ ዝም አልኩ፡፡ ትልቅ ብሶት ሆዳቸው ውስጥ ሲገላበጥ ይሰማኛል፡፡ ቀና ብዬ ፊታቸውን አስተዋልኩት፤ ከዕድሜም በላይ ሐዘን የተጫነው ክብ ፊታቸው ፈታ ቋጠር ይላል፡፡

‹‹ተወው እስኪ ሽጋዬ፤ እንዲሁ ደህና ደህናውን እናውጋ!›› ጥቂት ቆይተው ራሳቸውን ነቀነቁና እንዲህ አሉ፤ ‹‹በሌላው ጊዜ፤ አላችሁ ወይ፤ ወዴት ናችሁ? እንዴት ናችሁ አይሉንም! በዓል በመጣ ቁጥር ግን ከየወደቅንበት ይጠሩንና የትሌቢዥን ማሳመሪያ ያደርጉናል!››

‹‹እርስዎ ግን አርበኛ ነበሩ እንዴ?›› ድንገት በመሃል ጠየቅኩ፣ ትካዜያቸውን በሌላ ጨዋታ ለመተካት፡፡

‹‹እንዴታ ልጄ!›› አሉ ድምፃቸውን ይሁነኝ ብለው እያጎረነኑ፤ ‹‹እንዴታ! ያውም አውራው ነኛ! ያውም እሳቱ ነኛ!›› ጭንቅላታቸውን በወኔ ነቀነቁ፤ ዱላ የያዘ እጃቸውን ወዘወዙ፡፡

‹‹ጥልያንን እንደ ሚዳቆ ያሮጠው ማን ሆነና!? …ያውም ነብር እንዳየ ሚዳቆ!›› እየተርገፈገፉ ሳቁ፤ ‹‹ያን ነጭ ሁሉ እንደ አህያ ነዳነው፡፡ …

‹‹‹የጠቅል አሽከር የባለ ዘውዱ፤
መግደል መማረክ የዕለት ልማዱ!›

…ተተባለላቸው ጀግኖች መሃል ነበርኩ ልጄ፡፡ …ምን ዋጋ አለው!?›› አሁንም ትካዜ ተጫናቸው፡፡ ‹‹እናንተ ታሪኩን ባታውቁት አይፈረድም፡፡ እላይ ያሉትም ያው ናቸው!›› እጄን ጠበቅ አድርገው፣ አንዳች ሚስጥር እንደሚያወራ ሰው ድምፃቸውን ዝቅ አደረገው እንዲህ አሉኝ፤

‹‹ልጄ የላይኞቹ ከእናንተ ባይብሱ ብለህ! …ያለሁት ቀበሌ ቤት ነው፡፡ እሷኑ ሊያስለቅቁኝ ያንገራግሩኛል፡፡ ምን ልሁን? የት ልውደቅ? …ጣራው አፍስሶ አድሱልኝ ለማለት አቤት ብል፣ ‹አይቻልም› አሉኝ፤ ለምን ብል፣ ‹ቤቱ ለልማት መነሳቱ ስለማይቀር› ይሉኛል፡፡ ልማቱ ቤቱን እስኪያፈርሰው እኔ ቀድሜው እየፈረስኩ ነው!… አዬ ጉድ! ዋ ሆዬ፡፡ ስንቱን ዘመን ተንፏቅቄ ተንፏቅቄ፣ ሰው ክብር ያጣበት ጊዜ ላይ ደረስኩ ይኸውልህ!››

‹‹የትኛው ጦርነት ላይ ነው የተሳተፉት?››

‹‹የጥልያኑ ላይ ነዋ!›› አሉ በሞቀ ንግግር፤ ‹‹ያን ሶላቶን አምስት ዓመት ሙሉ በዱር በገደል ሳስጨንቀው ነው የከረምኩት፡፡

‹‹ሄደ መንኖ፤ ሄደ መንኖ፤
እንደናቱ ልጅ መውዜሩን አምኖ!››

ተብሎ የተዘፈነው ለእኛም አይደል!? …አርበኛው እስ በሱ እየተነጋገረ ድፍን ጦቢያን ለባዕድ አላስነካም ብሎ ነው አገር ያቆየው፡፡ ዛሬ አገሪቱ ለገዛ ልጆቿም አልሆነች!›› አሁንም በረዥሙ ተንፍሰው ፀጥ አሉ፡፡ ጨዋታቸውን ብወድላቸውም የወጋቸው ሁሉ ማሳረጊያ ቁጭትና ትካዜ መሆኑ አሳዘነኝ፡፡

‹‹ባገራችን መቀመጫ አጣን፤ ክብር አጣን፤ ተመልካች አጣን! …ማን ይሙት እኔ ደህና ቤት ስጡኝ አልኩ? ወጣኝ? እንደ ሌሎቹ ኮንዶሚ ስጡኝ አልኩ? …እኔ ካደኩበት ደብር ኖሬ ነው መሞት የምፈልገው! ይህቺኑ አድሼ ልቀመጥ ብል እንቢ አሉኝ!››

…የምላቸው ጠፋኝ፤ ‹‹አይዞት አባቴ!›› አልኩ አፌ ላይ እንደመጣልኝ ለማፅናናት ያህል፡፤

‹‹አዬ ተወኝ እስኪ፤ ከእኔ አንደኛቸውን የሔዱት ይሻላሉ፡፡ የእኔ ኑሮ ከኑሮ ተቆጥሮ ነው? እንደውም ይባስ ብለው የስንቱን አርበኛ አፅም ለቅመው መጣል ጀመሩ፡፡ ከሞትኩ በኋላ እንዳሻቸው ያድርጉኝ፡፡ ብቻ በቁሜ ባላሰቃዩኝ!››

በዚህ መሃል አንድ ወጣት ሞባይሉን በእጁ አንከርፍፎ ወደ እኛ መጣ፡፡ ጠጋ ብሎ፣ ‹‹ፍሬንድ ከአባባ ጋር ፎቶ አንሳኝ?›› አለኝ ሞባይሉን ወደኔ እየዘረጋ፡፡

‹‹አባባ!›› አልኳቸው እኔ፡፡

‹‹አቤት!››

‹‹ልጁ ከእርስዎ ጋር ፎቶ ልነሳ ይላል፡፡››

‹‹እሺ!›› አሉ ሽመላቸውን ወደ ላይ ወድረው ፈገግ ለማለት እየጣሩ፡፡

ልጁ አጠገባቸው መጥቶ ተለጠፈ፡፡ ሞባይሉን ተቀበልኩት፤ እንደሚፈልገው ሦስት አራት ፎቶ አነሳሁት፤ ሔደ፡፡

የአርበኞች ቀን የሚዘከርበት ሐውልት ጋ ተቃርበናል፡፡

‹‹አባት ደርሰናል!›› አልኳቸው የአራት ኪሎን ሐውልት የከበቡ ብዙ ሰዎች እያሳየኋቸው፡፡

‹‹አዎ ደርሰናል!›› አሉ እሳቸውም ሕዝቡን በፈገግታ እያዩ፡፡

ተሰናብቼ ተለየኋቸው፡፡ ጥቂት አለፍ እንዳልኩ ዞር ስል በባንዲራና በአርበኞች ምስል ያሸበረቀ፣ ‹‹ክብር እና ሞገስ ለአርበኞች›› የሚል መፈክር ያረፈበት ቲሸርት የለበሱ ወጣቶች አዛውንቱን ከብበቻዋል፡፡ በቡድን፣ በተናጠል እየተቀባበሉ አብረዋቸው ፎቶ እየተነሱ ነው፡፡

አዛውንቱ ውስጥ ያለው ሐዘን ፊቴ ላይ ተገተረ፡፡ ያን ሐዘን ማን ይይላቸው? ውስጣቸው ያለውን የመገፋት ስሜት ማን አንብቦ ይረዳቸው!? …‹‹ክብር እና ሞገስ ለአርበኞች›› የአዛውንቱን ልብ የሚሰብር ትልቅ ሽሙጥ፡፡



ሁሴን ከድር

# የሃሳብ ልዩነት ይውደም!!!

**እምነት ካለህ ተራራውን ወደ ወርቅነት ታስቀይራለህ! ከሌለህስ?**

ማይሰራ የልጁ መጠርያ ስም ነው:: በልጅነቱ ምንም የማይሰራ ነው ተብሎ በመታሰቡ ነው ‹‹አይጠቅምም፣ አይሰራም፣ ዋጋ የለውም›› በሚል ወጥቶለት የነበረው:: ዛሬ የማይሰራን ትክክለኛ ስም እንኳን የአካባቢው ሰው ወላጆቹም የረሱት ይመስላል:: ቤተሰቡ ከሚሰራው ሥራ ምንም ጉዳይ የለውም:: ቁርሱን በልቶ ከቤት በመውጣት ብረት እየለቃቀመ አንዳች ቅርጽን መሥራት የሚያስደስተው ተግባር ነበር:: በየቀኑ ይለቃቅማል፣ ይቀጠቅጣል፣ ያጣምማል፣ ያቃናል::

ሰዎች ስለእርሱ ከመጨነቅ እርሱን ወደመርሳት አምርተው ነበር:: ለትምህርት ደንታ አጣ፣ለሚቀጠቅጣቸው ሥራዎች ግን የበለጠ ትኩረት ሰጠ:: በሂደት በአካባቢው ስለመኖሩም ተረሳ:: ባሻገር የሆነ የሚቀጠቀጥ፣ ለጆሮ የሚረብሽ ነገር ቢሰማ እንጂ ስለቀጥቃጩ ሥራዬ ብሎ የሚያስብ ጠፋ:: ታዲያ ማይሰራ ብዙ አደጋዎችን ተጋፍጧል:: አሲድ ፈሶበታል፣ በተቀመጠበት የመኪና ጎማ እግሩ ላይ ቆሞበታል፣ የሚቀጠቅጠው ብረት በእጁም በእግሩም አደጋ አድርሶበታል:: በተደጋጋሚም ወደ ሕክምና ተቋም አምርቷል::

**ከልማድና ከዘይቤያዊ ድግግሞሽ ኑሮ የሚያናጥቁና ከእንቅልፍ የሚያባንኑ አዲስ ክስተቶች ሲፈጠሩ ለምን? እንዴት? እንዲህስ ቢሆን? የሚልን ደፋር ጠያቂና ቆም ብሎ የሚያሰላስልን ደጋፊና ተሟጋች ለማግኘት ብዙ ርቀት መሄድን የሚጠይቅበት ዘመን ላይ ያለን ይመስላል**

ማይሰራ የደረሰበት ሁሉ ለጊዜው ቢሰማው እንጂ እንደ ጉዳት ቆጥሮ በአእምሮው አስቦትም አያውቅ:: ሰውነቱ ላይ የሚታዩ ጠባሳዎችን እስከመኖራቸውም ልብ አይልም:: በዚህ ሁኔታ ከልጅነት እስከ እውቀት የገፋው ማይሰራ፤ በሂደት ከአካባቢው ሾልኮ የወጣ፣ የበቃ እልል የተባለለት መካኒክ ሆነ:: በሁለገብ የፈጠራና ቴክኒካል ሥራ ማንም አጠገቡ የማይቆም፤ በሁሉም ዘንድ ተፈላጊ፣ ለደቂቃ ፋታ የማያገኝ ባለሙያ ሆነ:: ዓይን አይሞላ የነበረው ማይሰራ ለመድሃኒትነት እንኳ የማይገኝ ውድ ሰው ሆነ:: አካባቢው ዓይቶት የማያውቅ በባትሪ የሚፈለግ ታላቅ ባለሙያ::

በዚህ ሁኔታ ሳለ ነው ለአያቱ ለቅሶ ገጠር በገባበት ተራራውን ልብ ብሎ በማየት ለማኅበረሰብ ጠቀሜታ መዋል እንደሚችል የተረዳው:: የገጠሩ ማኅበረሰብ ውሃ የሚጠጣው በበጋ ከምትደርቀው በክረምት ሞልታ ሰውም እንስሳም ከምትወስደው ‹‹ወይራ›› ከምትበል ወንዝ ነው:: ይህች ወንዝ ለልብስ ማጠብያ፣ ሰውነት መታጠብያ፣ ለመጠጥ፣ ለከብት ማጠጫ ... በአጠቃላይ ለሁሉም ነገር አገልግሎት መስጫ መሆኗ ማይሰራን ምቾት አልሰጠውም:: ማኅበረሰቡ ለዘመናት ከአያት ቅድመ አያት የሚጠቀምባት ወንዝ ብትሆንም የማይሰራን ሕሊና ግን ረበሸች:: ሁኔታው መቀየር እንዳለበት አመነ:: ''እንዴት ሰውና ከብት በአንድ ወንዝ ውሃ ይጠጣል? እንዴትስ በዚያው ውሃ ገላውን ይታጠባል? ከዚህ በላይ የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ መሰቃየት የለበትም::'' በማለት በራሱ ላይ እርምጃ ወሰደ:: ከተማ ውስጥ በባትሪ የሚፈለገው ባለሙያ ከወንዙ ባሻገር ያለውን ግዙፍና ሰንሰለታማውን ተራራ በመሸንቆር ለአካባቢው ማኅበረሰብ የንጹሕ ውሃ አቅርቦት በየቤቱ እስኪያደርስ ተኝቶ ላለማደር ለራሱ ቃል ገባ::

ከከተማ ጄኔሬተር በማስገዛት ውሃውን ከተራራው ሥር ስቦ የማውጣት ሙከራውን አሳየ:: ጉዳዩ በቀላሉ የሚሰምር አልነበረም:: ይህ ሁሉ ልፋት ለማይሰራ ገንዘብ አያስገኝለትም:: ማንም አቅም ኖሮት የሚከፍለው የለም:: እሱም ከማንም ምንም አይፈልግም:: ሃሳቡን እውን በማድረግ ብቻ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ንጹሕ ውሃ ማጠጣት ነው ሕልሙ:: በሚሊዮን የሚቆጠር የከተማ ሃብቱን ማንቀሳቀሱን ትቶ

ነው ወደዚህ ሶልዲ ወደማያስገኝ በሺዎች የሚያስወጣ ሥራ ውስጥ የገባው::

ከተደጋጋሚ ሙከራና ልፋት በኋላ ሃሳቡ ሰመረ:: ትናንት ቅዠት ይመስል የነበር ሃሳቡ ዛሬ በርካታ ተከታዮችን አሰልፎ ሃሳቡ ከግብ ደረሰ:: ይህን ሃሳብ በወጠነ በሶስት ዓመቱ የአካባቢው ማኅበረሰብ የንጹሕ፣ ያውም በበርካታ ንጥረ ነገር የካበተ የማአድን ውሃ ተጠቃሚ ሆነ:: የዚህን የውሃ ምረቃ ተጋብገዬ ለመመልከት ችያለሁ:: ማይሰራ ግን በአካባቢው ቀርቶ በሃገሩም የለ:: በሰዎች በተቀነባበረ ሴራ በማይረባ ነገር እንዲታሰር ተደርጎ በወህኒ ይገኛል:: እቅድና ሕልሙን ሌሎች ቢረከቡትም የፍሬው ተቋዳሽ መሆን አልቻለም:: ማይሰራ ሥሙን መልዓክ ሳይሆን ሰዎች ያወጡለት ነው:: እምነት ኖሮት ተራራውን ወደ ወርቅነት ባይቀይረውም በጠንካራ የሥራና አርቆ የማሰብ ክህሎት ተራራውን በሺዎች ለሚቆጠሩ የሃገሬው ነዋሪዎች ከወርቅ በላይ የሆነውን ጤና እንዲያገኙ ረዳቸው::

በዓለም ላይ ከተፈጸሙ ታላላቅ ተግባራት መካከል አስደናቂ መስለው የሚታዩን አብዛኛዎቹ ጉዳዮች ትናንት የእብድ ሃሳብ የመሰሉና በማኅበረሰባቸው በተፌዘባቸው ግለሰቦች የታቀዱ ነበሩ:: ማኅብረሰብ ለየት ያለ አስተሳሰብ ያላቸውን ሰዎች ከማክበር ይልቅ ማጣጣልና ማክሰሙን ከጥንትም በታሪክ የምናገኘው እውነታ ነው:: ጉዱ ካሳን ከፊታውራሪና በዘመኑ ከነበረው ማኅበረሰብ ያጋጨው የነበረው ማኅበር ዕድሩ በሚፈልገው ቦይ መፍሰስ አለመፈለጉ ነበር:: 'ይሁን… ይሁን…' ብሎ ሹምን ፈርቶ አይሳሳትም:: ትክክል ያልሆነውን ሆድ አደሮች ስለተስማሙ አይስማማም:: ዛሬም እንደ ጉዱ ካሳ ዓይነት የተለየ አስተሳሰብ ያላቸውን ምጡቃን ሳይሆን የፊታውራሪን የትምክህት አመለካከት ያላቸውን ሰዎች የሚያጅብ ብዙሃን ነው የምናገኘው:: አሸንፎ ሥልጣንን የተቆናጠጠው ምናለ ተብሎ በሰበብ ባስባቡ ቢጨበጨብለትና ሙቀት ቢፈጠርለት እንጂ ጎጂና መርዛማ ሃሳቡ አይተችም፤ አይደፈርም::::

ብዙኃን የተፈጠሩት ''…ብዙኃን ይመዉሎ… ''ን ቃል እያስቀደሙ ለሚመጡ ጥቂቶች ፍላጎት አስፈጻሚነት ይመስል ሞጋችና ፈታኝ ሃሳቦች ሲሰነዘሩ ማጣጣል እንጂ ጆሮ አይሰጣቸውም:: ከልማድና ከዘይቤያዊ ድግግሞሽ ኑሮ የሚያናጥቁና ከእንቅልፍ የሚያባንኑ አዲስ ክስተቶች ሲፈጠሩ ለምን? እንዴት? እንዲህስ ቢሆን? የሚልን ደፋር ጠያቂና ቆም ብሎ የሚያሰላስልን ደጋፊና ተሟጋች ለማግኘት ብዙ ርቀት መሄድን የሚጠይቅበት ዘመን ላይ ያለን ይመስላል::

ማኅበሩን አለመምሰል ወይም ከቡድንና ከዕድር አለመቀላቀል ዋጋ ማስከፈሉ የማይቀር ነው:: ሶቅራጥስ ከዘመኑ ማኅበረሰብ ሃሳቡ በማፈንገጡ የመረረ ዋጋ አስከፍሎታል:: በርግጥ ሶቅራጥስ ሞቶ እንኳን አሁንም ሃሳቡ አፈንጋጭ ነው:: አሪስቶትል በኒኮማቺያን ኤቲክስ የተለየ ሃሳቡ ተቀባይነትን ሊያገኝ አልቻለም ነበር:: ኒቼ ከአፈንጋጮች አንዱ ነው:: ኦገስት ኮምቴ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ፈላስፋ ነው:: ሎጂክን በሳይንስ ለመተርጎም የሞከረ ሰው ነበር፤ እሱም ተቀባይነት ለማግኘት ዓመታትን ቆጥሯል:: ዴሪዳ እንዲሁ የዲኮኒስትራክሽን አስተሳሰብ አራማጅ ነው:: በማኅበረሰቡ የተዋቀረውን አስተሳሰብ ገልብጦ መመልከቱን ለተረዳ ለማሰብና ለማጠየቅ ሌሎች አያሌ መንገዶችን እንድናስብ ይመክረናል:: ከፊት ለፊት ብቻ ሳይሆን እስቲ ከኋላም እንየው፣ ገልብጠን እናስብ፣ ባልታየበት መንገድ እንይ:: ለምን ሽፍኑን ብቻ? ፈርሱንስ መመርመር ገደቡ ለምን ነው?

መዋቅሩን ማፍረስ:: ከብዙሃን በተለየ መንገድ ማሰብ:: ነብያትም ከዘመኑ አስተሳሰብ አፈንግጠው የመንጋውን አስተሳሰብ ሲቃወሙ በቀላሉ ተቀባይነት ሊያገኙ አልቻሉም:: ነብዩ ኢብራሂም/አብረሃም አንዱ ተጠቃሽ ነው:: አብረሃም አምላኩን በጸሐይ፣ በጨረቃ፣ በቀን፣ በሌሊት ውስጥ እንደሆነ አሰበ:: አምላኩን ፍለጋ ብዙ ሞከረ:: ጣዖት አምላኪያን የአብራሃምን ሃሳብ እንደ ድፍረት ነበር የቆጠሩት:: በዘመኑ ሊታሰብ የማይገባ አስተሳሰብ ሆኖባቸው ሳይሆን ከለመዱትና ከተዋሃዱት መላቀቅን ስለሚፈሩ አዲስነትን መቀበል አይሹም:: አባቱ አዛር ጭምር የአብራሃምን ሃሳብ ኮንኗል:: ጣዖታትን ሲያፈራርስም በሕይወቱ ዋጋ የሚያስከፍለው ውሳኔን ነበር ያራመደው:: በየዘመኑ የሚነሱ የተለዩ ሃሳቦች ብዙ መጥቀስ ይቻላል:: ከተከፈለባቸው መራር እና ሚዛን የለሽ ዋጋ ጭምር::

ተቃርኖ እስከሌለ እድገት አይኖርም:: እምዬ ምኒሊክ ለአዳዲስ ሃሳቦች ልባቸው ክፍት ነበር:: ሆኖም በጉልበታቸው እንጂ በማኅበረሰቡ ቅቡልነት አልነበረም ዘመናዊነት ሊያነግሱ የቻሉት:: ጥብቅ በሆነ ባሕል የተተበተበ ማኅበረሰብ ለአዳዲስ ሃሳቦች በሩን ክፍት አያደርግም::

በሌላ በኩል ምዕራባውያን ብቻ ትክክል ናቸው ማለት አንድ ዓይናነት ነው:: ጃፓን ባሕሏን ጠብቃ ያደገች አገር ነች:: ሳይንስና ባሕልን ያጣመረች፣ ከምዕራባውያን በተቃራኒ ያለች በእድገት ቁንጮ ላይ የተቀመጠች አገር ነች::

ፍራንሲስ ፉክያማ ‹‹ዘ ኢንድ ኦፍ ሂስትሪ ኤንድ ዘ ላስት ማን 1989›› በሚለው መጽሐፉ ከኋላ ጀምሮ ያሉትን የዓለም ታሪክንና አስተሳሰብ ካወሳ በኋላ ወደፊት የሚመጣው የሰው ልጅ ዲሞክራት ሳይሆን አንድ ዓይነት አመለካከት ያለው ቴክኖክራት ይሆናል ይለናል:: ተመሳሳይ ሃሳብ ያለው፣ ለሃሳብ ልዩነት የማይጓጓ፣ በቴክኖሎጂ የደነዘዘ እንደሚሆን ተንብዮ ነበር:: የሃሳብ ልዩነትን የሚገድል የቴክኖሎጂ ሰለባ የሆነ ማኅበረሰብ፣ ሰው ከተፈጥሮው ያፈነገጠ የሃሳብ ልዩነትን የማያስተናግድ የፋብሪካ ውጤት ዓይነት ይለዋል:: ይህ ሰው ከጊዜ በኋላ የሚመጣው ማኅበረሰብ ነው የታሰበው:: ዛሬ በሃገራችን ከፉክያማ ትንበያ የተለየ ሁኔታ አናይም:: ሰዎች ተቃራኒ ሃሳብን ለማስተናገድ ብዙም አይደፍሩም:: ሰውዬው በተለየ ሃሳቡ ለውግዘት ሲዳረግ እናያለን:: በመንጋ አንድን ነገር ተቀብሎ ከመሄድ የበለጠ ሞት የለም::

## የሃገራችን ምሁራን

ምሁራን ከማኅበረሰቡ የቀደሙ፣ ማኅበረሰቡን አንድ እርምጃ የሚቀድሙ፣ አስከታዮች፣ በአኗኗራቸውም ሆነ በአመለካከታቸው ተለይተው በራሳቸው መንገድ የሚራመዱ ተደርገው ነው የሚታሰቡት:: ከሚያነቡት መጻሕፍት አንጻር ብዙ ጉዳዮችን ያውቃሉና የሚያውቁትን ይተገብራሉ ተብሎ ይገመታል:: ሟቹ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትውልድ ቀራጭ ምሁራንን ሰብስበው ሲያነጋግሩ ጠንካራ አስተሳቦችና ተገዳዳሪ አመለካከቶች ይገጥማቸዋል የሚል ትንበያ ከብዙ ጋዜጠኞች ተጠብቆ ነበር:: የሆነው ግን፤ ስለ ሀገሩ አጠቃላይ ሁለንተናዊ ጉዳዮች ላይ የፖሊሲና የስትራቴጂ አቅጣጫዎችን በዕውቀት የሞገተ ሳይሆን የተሻለ የደሞዝ ጭማሪ፣ የመኪና እና የምቾት ዕቃዎችን ያለቀረጥ የማስገባት ፍቃድን ነበር:: ይብሱን በስብሰባው ማጠናቀቅያ ያሆነውን ውዳሴ ከንቱ አጀባና የፊርሚያ ግፊያ (ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለማስፈረም) ትከሻ ለትከሻ የተደረገውን ግፍያ ስናይ ሞጋች ሃሳብ ገደል ገባ ብለ ነበር:: ይሉኝታ ጠፍቶ፣ እውቀት አሸርግዶ፣ ሥልጣን ግዘፍ ነስቶ ሲታይ ‹‹እንዴት ይሆን በአሸርጋጅ በአድርባይ ምሁር ሀገር ወደፊት የምትራመደው? ብለን እስከመጠየቅም አድርሶናል::

ዛሬም የልዩነት ሃሳቦችን ለእውቀት ማበልጸጊያ ከማድረግ ይልቅ ተቧድኖ የመፈራረጅያ፣ ቂም የመያያዥያ መድረክ ማድረግ ተክነናል:: በአንድ ጉዳይ መለያየታችን ከሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ሥርዓትና ፍላጎት እንጂ ወዳጅነትን የሚያሻክር፣ ዝምድናችንን የሚቆርጥ መርዝ እየሆነ ነው:: የማያግባቡን ሃሳቦች ከጤነኝነት ይልቅ ክፉ ደዌን ጎትተው የሚያመጡ መዘዞች እየሆኑ ነው:: አንድን ጉዳይ ነጭም ጥቁርም አለማለት ዘር የሚያስቆጥር፣ ሃይማኖት የሚያስመረምር፣ ወገን የሚያስለይ ውግዘት አስከታይ እየሆነ ነው:: ነገሩ ግራጫ የመሆን እድል እንዲሰጠው አይፈለግም:: እኛ ነጭ ነው ብለናልና አንተ ማን ብትሆን ነው አይደለም የምትለው በሚል አግላይነት ይከሰታል:: ሻይ ቡና መጠጣጠት ያስቀራል፣ ከእድር ያሰርዛል፣ እቁብ ተራ ያሳልፋል፣ ጭቅጭና ያስከስታል::

ሁሉም ሰው ‹‹ኢትዮጵያ ትቅደም የማለት ግዴታ›› የለበትም:: ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑርም አማራጭ ነው:: ኢትዮጵያ ትባረክም ምኞት ነው:: ክፉ አይንካትም ምረቃ ነው:: የራሷ ጉዳይም መብት ነው:: ለምን እኔ ያልኩትን አላልክም አንተ አናርኪስት፣ ሌኒኒስት ብሎ ቡጢ መሰነዛዘር ወድቆ ከመሰባበር ከመሰባበር አያመልጥም::

በብዙ ጉዳዮቻችን ተወያይተን በስምምነትም ሆነ በልዩነት ተከባብሮ መኖር ያልተቻለ የምሁራን ክሽፈት እየመሰለ ነው:: የሃሳብ ልዩነት ከቃላት ጡጫ እስከ አካላዊ እርግጫ፣ የዘርና የሃይማኖት ጥላቻ ማመንጫ እስከመሆን ደርሷል:: ምናልባትም የማኅበራዊ መገናኛው መስመር ማንም የፈለገውን እንዲለጥፍ እድል መስጠቱ፤ ዶግዷጊውን ጸሐፊ ማሰኘቱ፤ ለሰው ክብር መንፈግን ደረጃን ማመሳሰልን ፣ በአካል የታጣውን በበይነ መረብ ማገናኘት እንዲደፋፈር አድርጎ ሊሆን ይችላል::

ኢትዮጵያ ባሳለፈችው የታሪክ እድሜ ሕዝቦችዋን የሚጎዳ የታሪክ አጋጣሚዎች ተከስተው፣ አልፈው ይሆናል:: በየዘመኑ የተነሱ ነገስታት ዘመናቸውን ያስተዳደሩበት የሥልጣን ማራዘሚያ ዘዴ አጠቃቀምም ሊኖር ይችላል:: ይህ ያለፈ ታሪክ ሁሉም ማኅበረሰብ በአንድ ዓይነት ጅምላ አረዳድ እንዲረዳ አይጠበቅም:: ለአንዱ መልካም መስሎ የታየው ለሌላው ሳይጣናዊ ሆኖ ሊሳልለት ይችል ይሆናል:: የታሪክ መምሕራን ታሪክን የሚያስተምሩበት የራሳቸው ሥልተ-ትምህርት መኖሩ ተማሪዎች በየተማሩበት መንገድ እውነት ያሉትን ታሪክ ተምረው ያድጋሉ:: በሂደት ነገሮች ሊለወጡም ይችላሉ:: የሰዎች ግንዛቤና የነገሮች አረዳድ እንደ የልዩነት ውበት እንጂ መነቋቆርያ ሊሆን አይገባውም::

ሰዎች የተረዱት በራሳቸው የመረዳት መንገድ ሆኖ ሳለ አንተ የገባህ እንዲህ ነው:: ‹‹እንዲህ ለማለት ፈልገህ ነው:: ሃሳብህ ገብቶኛል:: እንዴት እንዲህ ታስባለህ›› በሚል አታካራ መግጠም በአስተሳሰብ ነጻነት ላይ ጦር ከመምዘዝ አይተናነስም:: ….ብዙ ብዙ የምለው ነበረኝ:: ሞጋች ሳገኝ እገፋበታለሁ:: መልካሙን ሁሉ እመኝላችኋለሁ:: ቸር እንሰንብት::



# “የቤተክህነት ኃላፊዎች የሚያመልኩት ሥርዓቱን ነው”

**“በተጠና ሁኔታ የዘር ማጥፋት ዘመቻ እየተካሄደ ነው”**
**“ማኅተብ በጥሱ፤ የመነኩሴ ልብሳችሁን አውልቁ ተብለናል”**
**“ማንም ይንገስ ማንም ቤተክርስቲያን ላይ እጁን እንዲቀሥር አንፈቅድለትም”**
**“አሁንም ድንበር እየተገፋ መሬታችን ለሱዳን እየተሠጠ ነው”**

## *አባ ገብረየሱስ ኪዳነ ማሪያምና አባ ገብረስላሴ ወልደኃይማኖት*

*የዋልድባ መነኮሳቱ አባ ገብረየሱስ ኪዳነማሪያምና አባ ገብረስላሴ ወ/ኃይማኖት በባለፈው እትማችን ቆየት ያለውን የዋልደድባ ገዳምና የህወሃት ታጋዮችን ውዝግብ፤ ብሎም እስካሁን ድረስ የቆየውን የቦታውን ችግር በተመለከተ ሰፋ ያለ መረጃ ለአንባብያን አድርሰዋል።*

*አንድ አመት ከሶስት ወር የቆየው የእስር ህይወታቸው ያሳያቸውን የፍትህ እጦት፣ የዜጎች መንገላታትና ሌሎች አንገብጋቢ አገራዊ ችግሮችን በተመለከተ ዛሬም የሚነገሩን በርካታ ጉዳዮች አሉ። በተለይም ቤተ ክርስትያንና ቤተክህነትን በተመለከተ ጠለቅ ያለ መረጃ አድርሰውናል። መነኮሳቱን ከእስር እንደተፈቱ ያነጋገሯቸው የግዮን ጋዜጠኞች ፍቃዱ ማ/ወርቅና ሮቤል ምትኩ ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል በዚህ መልኩ አቅርበውታል።*

**ግዮን፡- በእስር ላይ እያላችሁ አዲስ ጠቅላይ ሚንስትር ተሹሟል:: የዋልድባን ጉዳይ በተመለከተ ከጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐብይ አህመድ ለማነጋገር አስባችኋል?**

**አባ ገብረ ኢየሱስ**፡- ጠቅላይ ሚንስትሩን ለማነጋገር አስበናል:: እንደውም በቅርቡ እንገባለን ብለን ነበር፤ ነገር ግን መቀሌ በሄዱበት ሠዓት ያልሆነ ንግግር ሲናገሩ ቅሬታ ተሠማን:: በተለይ ስለ ፈላስፋው ዘርአያዕቆብ የተናገሩትን በደንብ ሠምተነዋል:: "የዘርአያዕቆብ አገር" ማለታቸው ትንሽ ተሠምቶናል:: ያልሆነ ታሪክ በአደባባይ መናገር፣ የሌላ የሆነን ታሪክ አሳልፎ ለሌላ መስጠት ወንጀል ነው:: ዘርአያዕቆብ ዘእንፍራንዝ መጠቀስ ያለበት ኢትዮጵያዊ መሆኑ እንጂ ትግራይ መሆኑ አይደለም:: በዚህ ደግሞ ልንሞግታቸው ስለምንችልና መረጃው ስላለን ነው፤ ይሄ ትንሽ ቅር አሰኝቶን ነበር::

እኛ ከህወሓት ጋር የመጀመሪያው ፀባችንና ልዩነታችን የዋልድባ ገዳም ነው:: ሁለተኛው የድኅ ምስክር፣ የቤተልሔምን ምስክር የመሠሉ ወደ ትግራይ የመውሠድ ጥረት ነው:: የራስ ዳሽን ተራራን የተነጠቅን ሰዎች ዛሬ እንዴት የቤተልሔም ምስክር፤ የማኅበረ ሥላሴ ገዳም፤ የጎንደር መሬት ለሱዳን ተላልፎ መስጠት፤ የራስ ዳሽንን ወደ ትግራይ መከለል አግባብ አይደለም እያልኩ ነው:: ይሄ የእምነት ጉዳይ ነው:: ዝም ተብሎ የሚታለፍ አይደለም:: ደብረ ቢዘንን የመሠለ ገዳማችንና ቅርሳችንን አሳልፈን ሰጠን:: አሁን ሌሎችን አሳልፈን ልንሰጥ እየተዘጋጀን ነው:: ምንም ያልመሰላቸው ሰዎች ዝም ይበሉ፣ እኔ ግን እናገራለሁ:: የታሪክ ዝርፊያ አስፈላጊ አይደለም:: ታሪኩን ላባለ ታሪኩ ነው መተው ያለበት:: የእኔ ያልሆነውን ታሪክ ተቀብዬ አስተናግዳለሁ ብል ታሪኩ ራሱ አይቀበለኝም::

በቅርብ ጊዜ የተዘጋጀ የመስቀል በዓል አለ፤ ትግራይ ላይ፣ የታሪኩ ባለቤት ማን ሆነና ነው ፓትርያርኩ አዲግራት ድረስ ተጉዘው መስቀልን እናክብር ለማለት የተፈለገበት ምክንያት ምንድነው? የመስቀሉ ባለቤት ወይም ባለታሪኩ ማን ሆነና ነው እዛ አካባቢ እንደዛ መጮሁ? ይሄ ነገር ወደ ነገ ሲሄድ ታሪኩ አቅጣጫውን የሳተ መንገድ ይከተላል ማለት ነው::

የዛሬ ሦስት ሺህ ዓመት ላስታና ሠቆጣ ላይ የነበረው የአሸንዳ ታሪክ ትናንት ትግራይ ላይ መከበር ስለተጀመረ ዓለም ዓቀፍ ዕውቅና እንዲያገኝ ተደርጓል:: እንዲህ ያለውን ታሪክ አሳልፈን የምንሰጥበት ምክንያት ምንድነው? ያልሆነ ታሪክ ለሌላ አካል እንዴት ተላልፎ ይሰጣል? እኛኮ ይሄን መሠሉን ትውልድ የሚበርዝና የሚያበላሽ ነገር ነው የምንቃወመው:: ስለዚህ ታሪኩን ለባለታሪኩ መተው ይገባል:: የሌለን ታሪክ ለራሳችን ብንወስደው ሽክም ካልሆነ በቀር አይዋሃደንም:: ብሔር፣ ክልል የሚባለውን ነገር እኔ አልቀበልም፤ አላምንበትምም:: ግን የትኛውም ታሪክ ለሌላ ተላልፎ መሠጠት የለበትም::

ለምሣሌ፤ የጎንደርን ታሪከ ለራሱ ለጎንደር ስንሰጠው ይዋሃዳል፤ የትግራይን ታሪክ ለትግራይ ስንሰጠው ይጣጣማል፤ የሸዋውንም፣ የሀረሩንም እንደዛው ነው ማድረግ ያለብን:: አሳልፈህ ባለቤቱ ላልሆነ ስትሰጥ ግን ታሪክ ይበላሻል:: ማኅበረ ሥላሴ በጎንደር ክልል ተከልሎ ግን ወደ ሱዳን ሊሄድ በዝግጅት ላይ ነው:: ገዳሙ ይሄን መሠሉ አደጋ ከፊት ለፊቱ ተጋርጦበታል:: በምን መስፈርት ይህ ቦታ ለሱዳኖች ታሪክ ይሆናቸዋል? የላስታን ታሪክ ለላስታ ስትሰጠው መጽሐፉ ላይም ስታነበው ከትውልድ ወደ ትውልድ ላስታ እያለ ይሄዳል:: የጎንደርን የቤተልሔም ድኅ ታሪክ አምጥተህ ጎንደር ከተማ ላይ ብታስቀምጠው አይዋሃድልህም:: ቤተልሔሞች ጋይንቶች ግን ይጠቀሙበታል:: ሌላውም ህዝብ የራሱን ታሪክ ይዞ ይሄዳል ማለት ነው:: እኔ በኢትዮጵያዊነቴ የማምን የዓባይ ዳር የግዮን ፍሬ ነኝ:: አንዱን ከሌላው ለይቼ ልመለከት አልችልም:: ግን ታሪክ እንዲበረዝ ደግሞ አልሻም::

ወደ ጠቅላይ ሚንስትሩ ጉዳይ ስንመጣ፤ እሳቸው ጋር የዋልድባ ገዳም ጉዳይን በተመለከተ መግባታችን አይቀርም፤ በቅርብ ቀጠሮ እናስይዛለን:: ትግራይ ላይ ያደረጉት ንግግር ቅር ስላሰኘን በተለይ የወልቃይትን ጉዳይ አስመልክተው የተናገሩት ጥሩ ስሜት ስላልያዘ የእኛም መልስ በቂና ጥሩ አይሆንም በሚል አቁመነው ነበር:: አሁን በቅርቡ ጎንደርና ባህር ዳር ላይ ባደረጉት ንግግራቸው ደግሞ የተወሠነ መልክ ቀየር ብሎ መጥቷል:: ጎንደር ስንደርስ ከጎንደር ህዝብና ከተለያዩ የአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተነጋግረን ወደ ጠቅላይ ሚንስትሩ የምንመጣበት ጊዜ ይኖረናል:: ያ በዕቅድና ፕሮግራም የሚሆን ነገር ነው::

**ቤተ ክርስትያን የፍቅር፣ የሠላምና የአንድነት ተምሳሌት እንደ መሆኗ ችግሩ ሲፈጠር "ተው" ማለት ይገባታል እንጂ ከገዳዩ ጋር አብራ መቆም የለባትም::**
**አቡነ ማቲያስ እኮ በአደባባይ "ወላጆች ልጆቻችሁን ከልክሉ" አይደል እንዴ ያሉት? ተው እረፍ መባል ያለበት ጥይት የሚተኩሰው ነው? ወይስ መብቱን የሚጠይቀው? እንዲህ ዓይነት ነገር መቅረት አለበት፤ ይሄንን ከህሊናቸው ማውጣት አለባቸው**

አባ ገብረ ሥላሴ፡- ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐብይ አህመድን እኔና አባ ገብረ ኢየሱስ ስለ ገዳሙ ጉዳይ ልናነጋግራቸው ተዘጋጅተን ነበር:: ቀደም ሲል እንደተገለፀው ትግራይ ላይ የተናገሩት ነገር ለእኛም በቂ መልስ አያስገኝልንም በሚል ልባችንን አሻክሮት ነበር:: ግን ላመሰግናቸው የሚገባ ነገር አለ:: ጎንደር ላይ ሄደው ይቅርታ የጠየቁበት መንገድ ሁላችንንም ልባችንን ሰብሯል:: ትህትና በጣም ብዙ ሰውን ይገነባል:: ሰው ማለት፣ ኢትዮጵያዊነት ማለት እንደዚህ ነው:: ይቅርታ ስለጠየቁ እኛም ደስ ብሎናል:: ወደ ፊት ያለውን ባናውቅም::

ጠቅላይ ሚንስትሩ አፍ አውጥተው በልበ ሙሉነት እንዲናገሩና ወደ መንበረ ሥልጣኑ እንዲመጡ ያደረጋቸው፤ እንዲሁም እነ አቶ ገዱ አንዳርጋቸውና አቶ ለማ መገርሳ በድፍረት ነገሮችን እንዲጋፈጡ ያደረጋቸው የህዝብ ጩኸት ነው:: ህዝቡ፤ ተሠቃይተናል፣ እየሞትን ነው፣ እስከመቼ ድረስ እንዲህ እንዝለቃለን ብሎ መትረየስ ያጠመደ ወታደርን ያለ ፍርሃት ሲጋፈጥ ሲያዩት፤ ‹‹ይሄ ህዝብ እየሞተ እየተፈናቀለ የእኛ ሥልጣን ላይ መቆየት ምኑ ላይ ነው?›› በማለት ለማ መገርሳ እስከ መናገር የደረሰው የህዝብ ጩኸት ተሰምቶት ነው:: የተወሠኑ ባለሥልጣናትም በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ከህዝብ ጎን በመቆማቸው በጣም ደስ ብሎናል::

አሁን ባለው ሁኔታ ጠቅላይ ሚንስትሩ ጋ ስንገባ ፍትህ ይሠጡናል ብለን እናምናለን:: ምክንያቱም አሁን አገራችን ትልቅ ውድቀት ላይ ነው ያለችው:: ታሪኳ እየተዘረፈ እየተሸጠ ነው:: ለምሣሌ "ነፍስ ገበያ" የምትባል በመተማ መስመር የምትገኘው ቦታ የሠፈረባት ማነው? ‹‹ተዋበች››፤ ‹‹መድህን›› የሚባሉት ሱዳን ውስጥ ያሉ ቦታዎች የእኛ ነው የነበሩት:: አሁንም ድንበር እየተገፋ ነው:: ማሕበረ ሥላሴም ወደዚያው እየሄደ ነው:: ብዙ ቦታዎች እየተቆራረሱ ነው:: ኢትዮጵያ ማንነቷን ልታጣ ትንሽ ነው የቀራት:: ነገስታት ሁሉ እያከበሩት፣ መባ፣ አምሀ እየሰጡት የመጣው ታላቁን የዋልድባ ገዳምንም ሆነ ሌሎች ጥያቄዎችን በተመለከተ አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር መልስ ይሠጡናል ብለን እናስባለን::

**ግዮን፡- ስትያዙ በለበሳችሁት የመነኩሴ ልብስ አንድ ዓመት እንድትቆዩ ተገዳችኋል፣ በእስር ላይ በነበራችሁበት ወቅት ፀሎት በአግባቡ ታካሂዱ ነበረ? የፀሎት መጻሕፍት እንድታነቡስ ተፈቅዶላችኋል?**

**አባ ገብረ ሥላሴ**፡- ሌላ ተለዋጭ የመነኩሴ ልብስ እንዳይገባ ስለከለከሉን እኔም ሆንኩ አባ ገብረ ኢየሱስ መጀመሪያ ስንገባ የነበርንበትን ልብስ እስር ቤት ውስጥ አንድ ዓመት ከሶስት ወር ሙሉ ለብሰነዋል:: መጀመሪያ ቀን ሲይዙን እየደበደቡን ቀደውት ነበር:: ያንን የተቀደደውን እየሰፋን፣ ስንታጠብም እዛው እያጠብን ነው አንድ ልብስ ይህን ያህል ጊዜ የለበስነው:: ይህች ልብስ አሁንም አለች፣ ለታሪክ ተቀምጣለች:: የእኛ ሁኔታ ያሳሰባቸው ወገኖቻችን ልብስ ይዘውልን ሲመጡ ፖሊሶቹ እየደበደቡ፣ ምራቅ እየተፉ፣ እያንጓጠጡ ነበር የሚያባርሯቸው:: እዛ ውስጥ የሚሰሩት ሰዎች የተማሩት ሥነ-ምግባር አይደለም:: ስድብ፣ ዱላና ሌሎች መጥፎ ነገሮችን ነው የሚያውቁት:: ከማዕከላዊ ጀምሮ እስከ ቂሊንጦ ድረስ ያሉት ሰዎች በጠቅላላ ስድብና ሰውን ማዋረድ ነው ዕውቀታቸው::

ስለ ፀሎቱ ጉዳይ ካነሳን ማዕከላዊ እያለን ኪዳን እናደርስ ነበር:: ስብከተ ወንጌል እንሰብክ ነበር:: ምህላ እናደርግ ነበር:: ይሄን እነሱ ፈቅደውልን ሳይሆን የሚመጣውን ቅጣት እየተቀበልን በገዛ ጉልበታችን ነበር የምናደርገው:: ሰው ይሰበሰባል ፀሎት እንጀምራለን፣ ያኔ ፖሊሶች ዱላ ይዘው ይገባሉ:: ችግር ሊፈጠር ሲል ጥለው ይወጣሉ:: የፀሎት →

መጽሐፍ ግን የለንም፤ አላስገቡልንም::

**አባ ገብረ ኢየሱስ፡-** ፀሎቱ ተፈቅዶ አይደለም:: ማዕከላዊ እያለን ሳይቤሪያ የሚባለው የምርመራ ክፍል ቀኑን ሙሉ በሩ ስለሚዘጋ በተዘጋበት ፀሎትህን ታደርሳለህ:: እነሱ ሲመጡ ፀሎቱን አቁሙ ይላሉ፤ እኛ ደግሞ ሰብሰብ ብለን የመጣው ይምጣ በሚል እንቀጥላለን:: ግማሹ ሲፀልይ፣ ግማሹ ይከላከላል እንጂ እነሱ ፈቅደውልን አይደለም የምናካሂደው:: ይሄ በዋናነት ምርመራ የጨረሱ ሰዎች የሚገቡበት ሸራተን የተባለው ቦታ ላይ ነው::

ሳይቤሪያ 8ተኛ ቤት የሚባል አራት ክፍል ያላት ጨለማ ቤት አለች:: እያንዳንዱ ክፍል ብቻህን ነው የምትገባው:: ጠባብና መቆሚያ የሌላት፣ ለስምንት ወይም ለአስር ደቂቃ ፀሐይ አይተህ እንድትመለስ ነው የሚደረገው፤ ይሄ ዋነኛ ማሰቃያ ቦታ ነው:: በር አከፋፈታቸውና ካቴና አስተሳሰራቸው ራሱ ይመጣብሃል::

ማዕከላዊ ድሮ ሮማውያን ሲያደርጉት የነበረው የማሰቃያ ስልት የሚተገበርበት ቦታ ነው:: ብዙ ግፍና በደል ይፈፀማል:: በሰው ገላ መጫወት ምን ያደርጋል? ወንድምህን ለማጥቃት እንዴት ትመኛለህ? ቢያንስ በተጠና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ፣ ባህላዊ በሆነ መልኩ ጥፋተኛ ነው የምትለውን ሰው መመርመርና ማጣራት ሲገባህ በዱላ እንዴት ሰውን ልታሳምን ትሞክራለህ? ሰው በመስቀል፣ በመደብደብ፣ ብልት በማኮላሸት እንዴት ምርመራ ታካሂዳለህ? ይሄ ብልት ማኮላሸት የሚባለው ነገር ለምን አስፈለገ? ሌላ አካል አይደበደብም ወይ? ጣልያኖች እኮ መጀመሪያ በቀጥታ ያደርጉት የነበረው ብልት መቁረጥ ወይም መስለብ ነበር:: ህወሓትም ይሄን ነው እያደረገ ያለው፤ ሌላ አይደለም:: በጣም የሚገርምህ ደግሞ ዘር ለይቶ አማራና ኦሮሞ ተወላጅ በሆኑት ላይ ነው ይሄን የሚያደርገው:: በተጠና ሁኔታ ዘር የማጥፋት ዘመቻ እኮ ነው እያካሄዱ ያለው::

ይሄ ችግር ሲፈፀም የነበረበት ማዕከላዊ አሁን ተዘግቷል እያሉ ነው ግን አይመስለኝም:: እናንተ ብትፈልጉ ይሄን ቢሮ ዘግታችሁ ትሄዳላችሁ፤ በቀጣይ ሌላ ቢሮ ትከራያላችሁ የማዕከላዊ መዘጋትም ከዚህ የተለየ አይመስለኝም:: የቤትና የቦታ ለውጥ ልክ እንደ ትልቅ ነገር በቴሌቭዥን መስኮት ብቅ ብሎ "ማዕከላዊ ተዘጋ፣ ሊዘጋ ነው" ማለት ዋጋ የለውም:: ቤቱ ምን አደረገ? መማርና መለወጥ ያለባቸው እዛ ያሉት ሰዎች ናቸው:: እነሱን በስነ-ምግባር ማነፅ፣ መልካምነት ምን ያህል ጥቅም እንዳለው እንዲያወቁ ማድረግ ነው የሚያስፈልገው:: እኔ አሁን ክፉ ከሆንኩ ይሄን ቤት ዘግቼው ብሄድ ምን ትርጉም አለው? የምሄድበት ቦታ ዓመልና ድርጊቴ አብሮኝ ስለሚኖር:: የማዕከላዊ መዘጋት ‹‹ይሄን ሰው አውቆብኛልና ሌላ መግረፊያ ማሰቃያ ቦታ አሉኝ፤ ወይም ልክፈት ነው›› አካሄዱ:: አዲስ አበባ ውስጥ ወገኖቻችን እያለቁ ያሉበት ብዙ የማሰቃያና የመግረፊያ ቦታዎች እንዳሉ በእስር ቆይታችን ተረድተነዋል:: በእነዚህ ድብቅ ማሰቃያ ስፍራዎች ስንት ወገኖቻችን አልቀዋል? ስንት መነኮሳትና ባህታውያን ሞተዋል? በእነዚህ ስለአገራቸው ስለኃይማኖታቸው የሞቱ ሰዎች ደም ላይ ነው ቁጭ ብለን ያለነው::

**ግዮን፡- ይሄን ሁሉ መስዋዕትነት የከፈላችሁት ለዕምነታችሁ፣ ለቤተክርስትያን ክብር ነው:: ጉዳዩ የሚመለከታት ቤተ ክህነት እንደ ተራ ዱርዬ ስትገረፉና ስትጣሉ ዝምታን ነው የመረጠችው:: የታሠሩብኝ መነኮሳት አሉ፣ የቤተ ክርስትያን ክብርና ሞገስ ተገፏል፤ መንግሥት በኃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እየገባ ነው በማለት ቤተክርስትያን ለገዥው አካልም ሆነ ለህዝብ ጥሪ ያላስተላለፈችበት፤ መግለጫ ያልሰጠችበትም ሆነ ድምጽዋን ያላሰማችበት ጉዳይ ህዝበ ክርስትያኑን በእጅጉ ያሳዘነ ነበር:: እናንተስ በዚህ ጉዳይ ምን ተሰማችሁ?**

**አባ ገብረ ኢየሱስ፡-** እኛ የቤተርክርስትያን ልጆች ነን:: ይህ ሁሉ መከራ ቢደርስብንም አሁንም ወደፊትም ከእሷ ህግና ደንብ አንወጣም::

ስለ ዕምነት፣ ስለ አገር፣ ስለ ነፃነት ለመናገር ዶክተር ወይም ሊቀ ጳጳስ መሆን አያስፈልግም:: ሁሉም ስለ ነፃነቱ ስለአገሩ መናገር ግዴታው ነው:: እኛ በዚህ መካከል ያለን ሰዎች እስከሆንን ድረስ ስለ መብታችን እንናገራለን:: በቂሊንጦ፣ በቃሊቲ፣ በማዕከላዊ መሠል ቦታዎች ያሉ ሰዎች እኮ፤ ነፃነት ያጣሁት እኔ ወንድማቸው ነፃነት አግኝቼ በአገሬ ላይ እንድኖር ስለተናገሩ፣ ስለፃፉ ነው እስር ቤት እየገቡ እየሞቱ ያሉት:: ብዙ ጋዜጠኞችና የነፃነት ታጋዮች በዚህ መንገድ ስለተጓዙ ነው የታሠሩት:: እኔም እናንተም በአገራችን ላይ የዜግነት መብታችን ተከብሮ በነፃነት እንድንኖር ነው የታገሉት::

በሌላ በኩል እኛ ደግሞ "ቤተ ክርስትያኗ እየጠፋች ነው፤ ቅርስ እየወደመ ነው" ነው ያልነው:: ይሄ ሁኔታ ደግሞ ቤተ ክርስትያኗን እናስተዳድራለን ለሚሉት ሰዎች አይዋጥላቸውም:: በመንበረ ፓትሪያርክ ጽ/ቤት ያሉ ሰዎች፣ በጠቅላይ ቤተ ክህነትና በየሀገረ ስብከቱ ያሉት አብዛኛው ሰዎች በሙስናና በዘረኝነት ታጭቀው የተቀመጡ ሰዎች ናቸው:: በጥቅም የታወሩት እነዚህ ሰዎች የሚያወሩት ስለፖለቲካ ነው እንጂ ስለ ቤተ ክርስትያን አይደለም:: ቤተ ክርስቲያናችን በእነዚህ ሰዎች ተተብትባለች ማለት ነው::

እስቲ ለዚህ አባባል በቂ መረጃ እንዲሆነን ነገሮችን ወደ ኋላ መለስ ብለን እናስታውስ:: ሲኖዶስ ተሰብስቦ አንድ ቀን ስለ ቤተክርስትያን ችግርና ጥፋት፣ ስለአገር ጥቃት ተነጋግሮ ያወጣው መግለጫ አለ ወይ? የለም:: ምክንያቱም የሚሰበሰቡት ደመወዛቸው ላይ ስንት ይጨመር፤ በጀታችን በምን ያህል ይደግ የሚል ካልሆነ በቀር በኃይማኖት ጉዳይ መንግስት ችግር እየፈጠረ ስለሆነ ይሄን ጉዳይ በተቃውሞ መልክ አውጥተን መንገዱ ስህተት መሆኑን ማሳየት አለብን፤ ጉዳዩን ህዝበ ክርስትያኑ እንዲረዳው ማድረግ አለብን ብለው አያውቁም:: ..እነሱ አቶ እገሌ እንዲህ ዓይነት መመሪያ አስተላልፏልና ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ መግለጫ እንስጥ የሚል ካልሆነ በስተቀር በትክክለኛው መንገድ ተጉዘው አያውቁም::

እኛ ከእነሱ የጥቅም መንገድ ወጥተን ለየት ባለ መንገድ ነው የመጣነው:: ስለዚህ እኛን ከማጥላላት፣ ጥቁር ነጥብ ከመጣል ውጭ አጋዥ ሆነውን አይቀርቡም:: ምክንያቱም ቤተ ክርስትያኒቱን እናስተዳድራለን የሚሉት ሰዎች ሌላ፣ እኛ ሌላ ሰዎች ነን:: ልክ እንደ ፖለቲካ ፓርቲና የመንግስት መ/ቤት ቤተ ክርስትያን ውስጥ ተሰግስጎ ያለው ህወሓት ነው:: ግልፅ ሌብነትና ዘረኝነት የተንሠራፋበት ቦታ ነው:: የሳህሊተ ምህረት ሀና ማሪያም ቤተ ክርስትያን ጉዳይ እስካሁን ድረስ ሳይፈታ መቆየት ነበረበት? የጣና ገዳማት ለዝርፊያ ሲዘጋጁ ለምን የሚል የቤተ ክህነት ሰው ነበር?.. ቤተ ክርስትያኖች ሲቃጠሉ ለምን አይሉም? ቢያንስ ቢያንስ ማነው ያቃጠለው? ብሎ እንኳ ጥናት ማድረግ አይሹም፤ ለምን ስራቸውን ስለሚያውቁ::

ለምሳሌ የእንጦጦ ማሪያም ቅርስ ሲዘረፍ ዘራፊዎቹ እነማን ናቸው? በዚህ ጉዳይ ላይስ የቤተ ክህነት ሰዎች ይገቡበታል? ለህዝብ ያሳውቃሉ? ፈፅሞ አይገቡበትም፤ ህዝቡምን የቤተ ክርስትያን አካል አያደርጉትም:: የእነሱ ኃይልና መሳሪያ ህወሓት ነው፤ አምላካቸውም ሥርዓቱ ነው:: እነዚህ ሰዎች እየኖሩ ያሉት በህዝቡ ሐብትና ንብረት ነው::

እኛን በተመለከተ "የቤተ ክርስትያን ልጆች፣ የዋልድባ መነኮሳት ታስረዋል" ብሎ ህዝብ ሲያወራ፣ መላው ሚዲያ ከአገር ባሻገር በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ሲያወጣና እነሱም ሲወቀሱ ነበር:: እውነተኞች ወይም ሐሰተኞች መሆናችንን መጥተው እናንተ እነማን ናችሁ? ብለው ለምን አልጠየቁንም:: በታሰርንበት ቦታ ቢጠይቁን እኛም መልስ ለመስጠት ዝግጁ ነበርን:: ከፓትሪያርኩ ጽ/ቤት ይሁን ከጠቅላይ



ንግስት ይርጋ የዋልድባ መነኮሳት ዮናታን ተስፋዮ እና እስክንድር

ቤተክህነት ወኪላቸውን ልከው ‹‹እናንተ ከየት ቦታ ነው የመጣችሁት? ማንስ አመነኮሳችሁ? ለምንስ ታሰራችሁ?›› ተብለን መጠየቅ ነበረብን:: እነዚህ ሰዎች የእኛ አይደሉም ብለው ለመመለስ እንኳን መጥተው መጠየቅ ነበረባቸው:: ለኢትዮጵያ ህዝብም በተለይም ለምዕመኑ በጉዳዩ በቂ መልስ መስጠት ነበረበት:: እነሱ ግን ዝምታን ነው የመረጡት:: ለምን ቢባል የሥርዐቱ አገልጋይ ስለሆኑ ሥራቸው ያሳፍራቸዋል:: እኛን "የቤተክርስትያን ልጆች አይደሉም" እንዳይሉ በደንብ እንተዋወቃለን፤ ማንነታችንን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ማስረጃም ስላለን:: ለምሳሌ እኔ የሰሜን ጎንደር አገረ ስብከት የገዳም ክፍል ሃላፊ ነበርኩ፤ ይሄንን መጥቀስ አልፈልግም ነበር:: በዛ ዘመን በፔሮል ላይ ፊርሜ ደመወዝ የምቀበል ሰው ነበርኩ፤ በተለያዩ ጊዜያት በሲኖዶስ ስብሰባ ላይ ስሳተፍ የነበርኩ ሰው ነኝ፤ እንዴት ብለው አላወቅንህም ይበሉ? አላውቅህም ቢሉ ደስ ይለኝ ነበር፤ በቂ መረጃ ስላለኝ::

መላው ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ክርስትያን ሳይል ከዳር ዳር በእኛ ጉዳይ ሲንጫጫና መንግስት ላይ ግፊት ሲያደርጉ፤ የቤተ ክርስትያኒቱ አስተዳዳሪ ነን ባዮች ዝምታን የመረጡት አዕምሮአቸው በንዋየ ዓለም ስለተጠመቀ ነው:: አሁን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን "ሰው አላት" ብለን አፋችንን ሞልተን መናገር አንችልም:: እንደውም የሚሠሩ አካላትን ላለማሠራት ችግር የሚፈጥሩ ሰዎች ናቸው ያሉን:: አሁንም እኛ ትግላችን ከእነሱ ጋር ነው:: ቤተ ክርስቲያን ክብሯ ሲገፈፍ፣ እንድትጠፋ ሙከራ ሲደረግባት መቼም ዝም ብለን አናይም::

**አባ ገብረ ሥላሴ፡-** አባቴ አባ ገብረ ኢየሱስ የተናገሩት ላይ ለመጨመር ያህል፤ እነዚህ በቤተ ክርስትያን ዙሪያ የተሠገሠጉ ሰዎች መሰብሰብያ አድራሻቸው ውሸት ነው እያፈለቀ ያለው:: የእግዚአብሔር ቃል እንዳይነገርበት፣ ዕውነት እንዳይሰበክበት ከፓትሪያርኩ ጽ/ቤት ጀምሮ እስከ ገጠሯ ቤተክርስትያን ድረስ የራሳቸውን ሰው በማስቀመጥ፤ ህዝበ ክርስትያኑ ጠዋት ለመሳለም፣ ፀሎት ለማድረግ ሲመጣ የሚነገረው ስለ ፖለቲካና ስብስባ እንጂ የእግዚአብሄር ቃል አይደለም::

እንግዲህ እኛ ከተያዝንበት ቀን ጀምሮ አንድ ጳጳስ ወይም ኃላፊ ከአገረ ሥብከት ወይም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የተናገረ፣ ድርጊቱን ያወገዘ ሰው የለም:: "ይሄ ገዳም እየፈረሠ ነው፤ ይሄ ገዳም እየታረሠ ነው፤ እነዚህ መነኮሳት እውነታቸውን ነው" ያለ አካል የለም:: እኛንም ማብራሪያ የጠየቀን አካል የለም:: ሙት ወቃሽ አያድርገኝና ያኔ ገና ነገሩ ሲጀመር ገዳሙን በተመለከተ የትግራይ ክልል ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ሰው "ገዳሙ ልማት ላይ ቢውል ምን ችግር አለው? እናንተ የልማት ፀር ናችሁ" ነበር ያሉን:: እኛ በዓላማችን ፀንተን ታስረን፣ ተገርፈን ወጥተናል:: እሳቸው ግን ወደማይቀረው ዓለም በፍጥነት ሄደዋል::

በቤተ ክህነት ውስጥ ያሉት ሰዎች ዋልድባ ገዳም ቢታረስ፣ አፅመ ቅዱሳኑ ወጥቶ ቢጣል የሚያሳስባቸው አይደሉም:: አባቶች መጀመሪያውኑ በመፈንስ ቅዱስ የተቃኙ፤ ሥልጣንና ኃላፊነቱን በመንፈስ ቅዱስ የተቀበሉ ቢሆኑ ኖሮ ይሄ ሊሆን አይችልም ነበር:: በእኛ ጉዳይ ከህዝቡ ተነጥለው ዝም ያሉትም ለእዚህ ነው:: አንድ ሰው በሚያገባው ነገር ላይ አውቆ ዝም ካለ ችግር አለ ማለት ነው:: ቤተ ክርስትያን ከፖለቲካ ነፃ መሆን አለባት! ከህወሓት ነፃ መውጣት የሚገባቸው ብዙ ሰዎች አሉ:: በድርጅት የተቃኘ ሰው ቤተ ክርስትያንን ሊመራ ሊያስተዳድር አይችልም::

መንግስት ነኝ ብሎ የተቀመጠው አካል ህዝቡን ሲያስር፣ ሲያሰቃይና ሲገድል ቤተ ክርስትያን የራሷ ሥርዓት አላት፤ የራሷ ህግ አላትና "አቁም" ልትልና ህዝቡን ልትታደግ መጣር ይገባት ነበር:: ቤተ ክርስትያን የፍቅር፣ የሠላምና የአንድነት ተምሳሌት እንደ መሆኗ ችግሩ ሲፈጠር "ተው" ማለት ይገባታል እንጂ ከገዳዩ ጋር አብራ መቆም የለባትም::

አቡነ ማቲያስ እኮ በአደባባይ "ወላጆች ልጆቻችሁን ከልክሉ" አይደል እንዴ ያሉት? ተው እረፍ መባል ያለበት ጥይት የሚተኩሰው ነው? ወይስ መብቱን የሚጠይቀው? እንዲህ ዓይነት ነገር መቅረት አለበት፤ ይሄንን ከህሊናቸው ማውጣት አለባቸው::

**ግዮን፡- ከብዙ መከራና እንግልት በኋላ ክሳችሁ ተቋርጧል፤ ውጡ ስትባሉ ምን ተሰማችሁ?**

**አባ ገብረ ሥላሴ፡-** እኛ በግርፋት ብዛት ሰውነታችን ለአስቀያሚ ሽታ ከተዳረገበት ማዕከላዊ ጀምሮ እግዚአብሔር በራሱ ሠዓት ያወጣናል እንጂ ሕወሓት ይፈታናል የሚል ተስፋ አልነበረንም:: አድርገንም አናውቅም:: ህግም፣ ፍትህም ስለሌለ ተስፋችን ቸሩ መድኃኒዓለም ብቻ ነበር:: በነገራችን ላይ ክሳችን በመቋረጡና በመፈታታችን ደስተኛ አይደለንም፤ የተደሰትነው በህዝባችን ብቻ ነው:: ህዝባችን ዕውነታውን ስለሚፈልግ፣ ለዕውነት የቆመ መሆኑን ማወቃችን አስደስቶናል:: ከዛ ውጭ

> **ታሪኳ እየተዘረፈ እየተሸጠ ነው:: ለምሣሌ "ነፍስ ገበያ" የምትባል በመተማ መስመር የምትገኘው ቦታ የሠፈረባት ማነው? ‹‹ተዋበች››፤ ‹‹መድህን›› የሚባሉት ሱዳን ውስጥ ያሉ ቦታዎች የእኛ ነው የነበሩት:: አሁንም ድንበር እየተገፋ ነው:: ማሕበረ ሥላሴም ወደዚያው እየሄደ ነው:: ብዙ ቦታዎች እየተቆራረሱ ነው:: ኢትዮጵያ ማንነቷን ልታጣ ትንሽ ነው የቀራት**

መፈታታችን ትርጉም የለውም:: ብንቆይም ሊያደርጉ የሚችሉትን በሙሉ አድርገውብናል:: የቀራቸው መግደል ብቻ ስለነበር አዲስ ነገር አይጠበቅብንም:: ሁሉንም ከፈጣሪ ጋር ችለናል፣ ተወጥተነዋል:: እኛን ያስፈታን የኢትዮጵያ ሕዝብ ታስሮ፣ ተደብድቦ፣ ሞቶ ነው ያስፈታን:: ታስረን በነበረበት ጊዜ እንኳ ፍርድ ቤት ሰው እንዲጠይቀን ሲፈቀድ በፖሊስ እየተገፈተረ፣ እየተወረወረ ፀሐይና ብርዱን ተቋቁሞ ነበር የሚጠይቀን:: ሙስሊሞች ሁሉ "አይዟችሁ" እያሉ አበረታተውናል:: ያሠረን ህወሓት ቢሆንም መግለፅ በሚያቅት ሁኔታ መስዋዕትነት ከፍሎ ያስፈታን የኢትዮጵያ ህዝብ ነው::

የእዚህች አገር ፈላጭ ቆራጭ የሆነው ህወሓት እኛን እንደዛ ባለ ሁኔታ ሲያሰቃየን የቤተ ክርስትያኒቱ ኃላፊዎች "ለምን?" ማለት ይችሉ ነበር:: ግን እነሱ ደጋፊ ናቸው፣ የሚያስጨንቃቸው የራሳቸው ጥቅም ብቻ ነው:: ስለቤተክርስትያኑ የሚከፈል መስዋዕትነት፤ ለዕምነት የሚደረግ ትግል አይገባቸውም:: እንደውም ህዝቡ ቀድሟቸዋል:: በስራቸው ቢያዝንም ለእኛ ግን ጊዜውን አካሉን፣ ሕይወቱን ሰጥቶልናል::

አሁንም በጣም ብዙና የተለያዩ ሰዎች ፍትህ አጥተው በቂሊንጦ የተቀመጡ አሉ:: ለምሳሌ አስቻለው ደሴ የሚባል ልጅ ብልቱን አኮላሽተውት እየተሰቃየ ነው:: እነ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጠኝ፣ እነ አሸናፊ አካሉ፣ እነ ጌታ አስራደን የመሳሰሉ በእስር ቤት ውስጥ በፍትህ እጦት ላይ ነው ያሉት:: አጋየ አድማሱ፣ አበባው ሰጠኝን የመሰሉ በርካታ የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች ለአገር መስራትና ማገልገል እየቻሉ በእስር ላይ ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ፍትህ አልባ ናቸው:: እኛ የዘር ጉዳይ ውስጥ የለንበትም:: ሰውን ሰው በመሆኑ ብቻ በእኩል ዓይን የምናይ ነን:: የመጣንበትም ሁኔታ ፍቅርና የሰው ልጅ እኩልነትን የሚሰብክ ነው:: ግን ያየነውን መናገር ካለብን ሰዎች የሚደበደቡትም የሚታሰሩትም ሆነ የሚሰቃዩት ኦሮሞና አማራ በመሆናቸው ብቻ ነው::

አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ የሚባል የዘረኝነት ጉዳይ መቅረት አለበት:: አምላክ የሰውን ልጅ እኩል አድርጎ ነው የፈጠረው:: ይሄ ነገር መቅረት አለበት:: የኃይማኖት አባቶችም ይሄንን ጉዳይ ለምን ዝም ብለው እንደሚመለከቱት ግራ ነው የሚገባኝ:: ህዝቡ ሲደበደብና ህዝቡ ሲገደል፤ ህዝብ በዘረኝነት ሲከፋፈል እና ሲጎዳዳ ዝም ብለው ለምን ያያሉ? እነዚህ ሰዎች በምድር ህግም ሆነ በሠማያዊ ንጉስ ተጠያቂ ናቸው:: እኛ ግን ኃላፊነታችንን እየተወጣን ነው:: ከመናገር ወደኋላ ብለን አናውቅም:: የትኛውንም እግዚአብሄር ከመፍጠር ያልናቀውን ፍጡር ልናከብረው ይገባናል:: ሊገደልም ሊሰቃይም አይገባም:: እኛ ክሳችን ተቋርጦ ብንለቀቅም አሁንም እስር ላይ ነን:: ለበርካታ ዓመታት ታስሮ ያለውን ህዝብ ነው የተቀላቀልነው::

**አባ ገብረ ኢየሱስ፡-** በኢትዮጵያ ለተፈፀመው ጥፋት ተጠያቂው በአሁኑ ሠዓት ከሥርዓቱ ጋ ሆነው ከጀርባ እያስተባበሩ ያሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን አባቶች ነን ያሉ ሰዎች ናቸው:: በታሪክም በህዝብም ይጠየቃሉ:: የሰው ልጅ ደም ሲፈስ እያዩ ለምን? ካላሉ የእነሱ አባትነት ምኑ ላይ ነው? አባትነታቸው የሚለካው ከህገ ዕምነት ባልወጣ መልኩ ስለ ሰው ልጅ መብት፣ ነፃነት ሲናገሩ ነው:: የኃይማኖት፣ የሀገርና የህዝብ

ቀሪውን ቃለ-ምልልስ በገጽ 30 ይመልከቱ

ምልከታ

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፋሽስት ለተፈጸመባት ግፍና ጭፍጨፋ ፤

## የጣሊያን መንግሥት ይቅርታ ሊጠይቅና ካሣ ሊክስ ይገባዋል!



ተረፈ ወርቁ

እንደሚታወሰው ባሳለፍነው ሳምንት ቅዳሜ ሚያዚያ ፳፯ቀን ጀግኖች፣ አርበኞች አባቶቻችንና እናቶቻችን ወራሪውን የፋሽሽት ጦር ያሸነፉበትን ፸፯ኛ ዓመት ‹የድል መታሰቢያ በዓል›ን አክብረናል፡፡ ይህ ለአፍሪካ፣ ለአፍሪካ አሜሪካውያን፣ ለመላው ጥቁር ሕዝቦችና በአጠቃላይም ነጻነታቸውን ለሚያፈቅሩ የሰው ልጆች ሁሉ ብሔራዊ የኲራት ምንጭ፣ ለበርካታ ጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ተጋድሎ እንቅስቃሴ የወኔ ስንቅ የሆነና ዳግመኛ አውሮፓውያንን ሃፍረት እንዲከናነቡ በማድረግ፤ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በዓለም መድረክ ከፍ ያደረገ፣ ያስከበረ አንጸባራቂ ድላችን ነው፡፡

ይህ ድል ጀግኖች አርበኞቻችን ለአምስት ዓመታት በሀገራችን ተራሮችና በበረሃ፣ በዱርና በገደል፣ በሸንተረር ባደረጉት እልህ አስጨራሽ የአርበኝነት ተጋድሎና እንዲሁም ኢትዮጵያውያንና በርካታ የኢትዮጵያ ወዳጆች በዓለም አቀፍ መድረክ ባደረጉት ያላሰለሰ የዲፕሎማሲ ትግል ጭምር የተገኘ ድል መሆኑንም መዘንጋት የለብንም፡፡

በዚህ በዛሬው ጽሑፌ በድል በዓላችን ማግሥት፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፋሽስት ስለደረሰባት ግፍና መከራ፣ በአገልጋዮቿና በመእምናኖቿ ላይ ስለደረሰው አሰቃቂ ጭፍጨፋና እልቂት በተመለከተና ለዚህም ደግሞ የኢጣሊያን መንግሥት ቤተክርስትያኒቷን ይቅርታ በመጠየቅ ተገቢውን ካሣ እንዲከፈላት ጥያቄ መቅረብ እንዳለበት እንድንነጋገር በማሰብ ነው፡፡

የዓለማችን የታሪክ እምብርትና የሥልጣኔ ቁንጮ የሆነችው ታላቂቷን ሮማንና መላውን የአውሮፓውያኑን የቅኝ ገዢ ኃይሎች ቅስም የሰበረውንና አሳፍሮ የመለሰውን የ፲፰፻፹፰ቱን የዐድዋውን ሽንፈት ለመበቀል ነበር ከዐርባ ዓመት በኋላ በፋሽስቱ መሪ በቤኒቶ ሞሶሎኒ ሮም ልጆቿን እስከ አፍንጫቸው አስታጥቃ ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ጦሯን ያዘመተችው፡፡ ሮማንና ሕዝቦቿን እንዲሁም መላውን አውሮፓ አንገት ካስደፋው ከዚህ የታሪክ ቅሌትና የሞራል ስብራት ሮማን ለመታደግ እኔ ጀግናዋ አለሁ በማለት ነበር የፋሽስቱ መሪ ቤኒቶ ሞሶሎኒ ለራሱና ለሕዝቡ ቃል የገባው፡፡

ሞሶሎኒ ኢጣሊያንና መላውን አውሮፓን ሳይወዱ በግድ የሽንፈት ጽዋ እንዲጋቱ ያደረገችውን ኢትዮጵያን ለመበቀል ሰዓቱ አሁን እንደሆነ በሮም አደባባይ ለተሰበሰበው ሕዝብ አስረግጦ ተናገረ፡፡ የፋሽስቱ ቀንደኛ መሪ በሮም አደባባይ ባደረገው ንግግሩም እንዲህ ነበር ያለው፡-

‹‹ኢትዮጵያን አምላኬ የምትለው እግዚአብሔር ከኃያሉ መዳፌ ሊያድናት የሚችል ከሆነ የእኔንም እግዚአብሔር ልጨምርላት እችላለሁ!›› በተመሳሳይም የምሥራቅ አፍሪካ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ሹም ጄኔራል ግራዚያኒ ለአለቃው ለሞሶሎኒ የገባለት ቃልም፡- ‹‹ኢትዮጵያን ከሕዝቦቿ ጋር ካልሆነም ኢትዮጵያን ገጸ በረከት አድርጌ አቀርብልሃለሁ፡፡›› በማለት ነበር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን እንደ ሽቀጥ ለገጸ-በረከትነት ለማቅረብ ሮማውያኑ ፋሽስቶች በአደባባይ የተደራደሩባት፡፡

ፋሽስት በዓለም ሁሉ ፊት ሮማ የደረሰባትን ታላቅ እፍረትና ሽንፈት ለመበቀል እስከ አፍንጫው የታጠቀ ዘመናዊ ጦሯን በቫቲካን ጳጳሳት አስባርካ ወደ ኢትዮጵያ የላከችው፡፡ የሞሶሊኒ ወደ ኢትዮጵያ የላከው ኃይል በጦር መሣሪያ ብዛትም ሆነ ዘመናዊነት በቂ ወታደራዊ ሥልጠና ከሌለው ከአገራችን የጦር ሰራዊት ጋር ፈጽሞ የማይወዳደር እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡ የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት እስከ አፍንጫው ከታጠቀው ዘመናዊ የጦር መሣሪያ በተጨማሪም የኢትዮጵያን ሰማይ እየሰነጠቁ ሞትን የሚተፉ የመርዝ ጭስ አረሮችን የተሸከሙ የጦር አውሮፕላኖችን ጭምር የታጠቀ ነበር፡፡

በእነዚህ በሰማይ ላይ በሚምዘገዘጉና በሚበሩ የፋሽስት ኢጣሊያ አውሮፕላኖች እንግዳ የኾነው የኢትዮጵያ ሕዝብም ‹‹ምን ዓይነት ጉድ መጣብን!›› በሚል በእጅጉ ተደናግጦ ነበር፡፡ በእነዚህ ሰውነትን አሳብጠውና ብጥስጥስ አድርገው በሚገድሉ፣ የሞት ላንቃቸውን በአናታቸው ላይ በሚተፉት፣ የእሳት አሎሎን በሚያዘንቡ እሳታውያን፣ የሰማዩ ላይ በራሪ አካላት ባደረሱት እልቂት እጅጉን ግራ የተጋቡ የአገሬ መነኮሳት በወቅቱ ‹‹ይህ ምን ዓይነት መዓት፣ ምን ዓይነት ጉድ ነው!›› በሚል እንዲህ መቀኘታቸውንና ፈጣሪን፣ አምላክን መሞገታቸውን የታሪክ ድርሳናት ይጠቁማሉ፡-

*ከኢትዮጵያ ጸሎት ጣሊያኖች በለጡ፣*
*በዐርባ ዘመናቸው ክንፍ አውጥተው መጡ፣*
*ፈጣሪ ተጠንቀቅ ወደ አንተም እንዳይመጡ፡፡*

ይህች ቅኔያዊ ግጥም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ በቅዱስነታቸው፣ በተጋድሎአቸውና በወንጌል ገበሬነታቸው የሚታወቁት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለሰባት ዓመታት ያህል በአንድ እግራቸው ቆመው ባደረጉት ጸሎትና መንፈሳዊ ተጋድሎ እግራቸውን ቢያጡም ከአምላካቸው ዘንድ ስድስት ክንፍ እንደተሰጣቸው የሚያትተውን ገድላቸውን የሚያስታውስ ሆኖ፤ በእንዲህ ዓይነቱ ጸሎታቸው፣ መንፈሳዊ ተጋድሎአቸውና ትሩፋታቸው ከሚታወቁ ኢትዮጵያውያን ይልቅ ሮማውያን ልቀው ተገኝተው በዐርባ ዘመናቸው ክንፍ አውጥተው የመጡበትን ጥበባቸውን የሚያደንቅና ፈጣሪያቸውን የሚሞግት ቅኔ ነው፡፡

ይህን በአሰቃቂ ኹኔታ ሰውነትን በጣጥሶ የሚገድለውን የመርዝ ጭስ ፋሽስት ኢጣሊያ ለመጠቀም የፈለገው የኢትዮጵያውያንን የውጊያ፣ የመከላከል ሞራልና ቅስም በመስበር ቅኝ ተገዢ ለማድረግ ኾን ብሎ አስቦና አልሞ እንደነበር ታሪክ ድርሳናት ይጠቁማሉ፡፡ በወቅቱ ፋሽስት ኢጣሊያ በኢትዮጵያውያን ላይ መጠቀም ስለሚገባው የመሣርያ ዓይነት በምስጢር አስተላልፎት የነበረውን መልእክት የአሜሪካው ላይብረሪ ኦፍ ኮንግረስ የሚገኝ ወታደራዊ፣ ምሥጢራዊ ሰነድ እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡

‹‹ተልእኳችን እንዲሳካ ከተፈለገ በጠላት ላይ እጅግ ከፍተኛ ውድመት ከዚህም በላይ የሞራል ስብራት የሚያስከትለውን ልዩ የሆነ ፈሳሽ ቦምብና መርዝ ሼል እንደፈለጉ በስፋት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡››

ፋሽስት በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ዳግመኛ ወረራው በበቂ ኹኔታ ተዘጋጅቶና የዐድዋውን ሽንፈት በሚገባ ለመበቀል የመርዝ ጋስ ጭስ ሣይቀር ታጥቆ ነበር የመጣው፡፡ በተጨማሪም ፋሽስት ሕዝቡን በዘር፣ በጎሳና በቋንቋ በመከፋፈል በአንድነቱ እንዳይቆምና እንዲሁም ስለ አንድነቱና ነጻነቱ የሚያስተምሩና በጽናት እንዲቆሙ የሚመክሩ እንደ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ያሉትን የሃይማኖት ተቋማት ለማዳከምና ለማፍረስ ከተቻለም በሮም ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ ለማድረግም ከፍተኛ የሆነ ዘመቻን ከፍቶ ነበር፡፡

ፋሽስት በዚህ ዘመቻው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ዋንኛ ዒላማው አድርጓት ነበር፡፡ የሰማዕታቱ የአቡነ ጴጥሮስና የአቡነ ሚካኤል የግፍ ግድያ፣ የበርካታ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት መቃጠል፣ መዘረፍና መውደም እንዲሁም ደግሞ የበርካታ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች የኾኑ ካህናት፣ መነኮሳት፣ መናኒያን፣ ዲያቆናትና ምእመናን ጭፍጨፋም የዚሁ የኢጣሊያ ፋሽስት መንግሥት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያራምድ የነበረው የከፋና እኩይ አቋሙ ማሣያዎች ናቸው፡፡

ፋሽስቱ ቤኒቶ ሞሶሊኒ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ንቀትና ጥላቻ ያሳየበትና ቢቻለውም ቤተ ክርስቲያኒቱን በፋሽስት ወይም በሮማ አስተዳደር ሥር እንድትሆን የነበረውን ሕልም የሚያጋልጠው እ.ኤ.አ. ታኅሣሥ 16/1935 በአስመራ ለሚገኘው ለጦር አዝማቹ ለማርሻል ባዶሊዮ ያስተላለፈው ጥብቅ ምሥጢራዊ ቴሌግራም እንዲህ ይነበባል፡-

‹‹በቁጥር 421M እና በቁጥር 426 ዳግም ያስተላለፍክልኝን የምስጢር ቴሌግራም ደርሶኝ በሚገባ አይቼዋለሁ፡፡ የአክሱም ገዳም የተቀደሰ ሥፍራ እንደመሆኑና ካለውም ጥንታዊ ታሪክና ቅርስ አኳያ በጦር መሣሪያም ሆነ በማናቸውም ዓይነት ወረራ እንዳይነካና ኢትዮጵያዊነቱን እንደያዘ መቆየት አለበት የሚለውን የውጭ መንግሥታት አሳብ ከምንም አልቆጥረውም ማለትህና ወደፊትም ይህን አሳብ የምቀበል ሰው አይደለሁኝም ማለትህ ትክክለኛ ነህ፤ ጥሩም አድርገኻል፡፡ አሁን የቀረህ ደግሞ የአክሱምን ገዳም ካህናትና መነኮሳት ብዛታቸውንና ማዕረጋቸውን ጠይቀህ ካወቅህ በኋላ በገናናዋ በሮምና በሞሶሎኒ ዙፋን ሥር እንተዳደራለን የሚሉ እንደሆነም በውል አጽፈህና እያንዳንዳቸውን አስፈርመህ ቃል የገቡበትን ሰነድ ወደ እኔ እንድትልክልኝ ነው፡፡››

ፋሽስት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያደረሰው ግፍና መከራ እንዲህ በቀላሉ ተዘርዝሮ የሚያበቃ አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ እጅግ አሳዛኙ ነገር የቫቲካን ሃይማኖት አባቶች ለሞሶሎኒ የግፍ ወረራ ድጋፍ ማድረጋቸውና ጦሩንም ባርከው መላካቸው በታሪክ የተመዘገበ የቫቲካን

ካቶሊካውያን የሃይማኖት መሪዎች ትልቅ እፍረትና ቅሌት የመሆኑ ጉዳይ ነው:: የእነኚህን የቫቲካን የሃይማኖት መንፈሳዊ መሪዎችንና አባቶችን ቅሌት በወቅቱ የታዘበ ኤሊክ ሲንድሩም የተባለ ስዊድናዊ ጋዜጠኛ ለሮማው ፖፕ በጻፈው ደብዳቤው እንዲህ ሲል ነበር ኀዘኔታውን የገለጸው፡-

‹‹… ቅዱስ ሆይ እኔ በሰሜን አገር የተወለድሁ አንድ ፕሮቴስታንት ስዊድናዊ ነኝ:: … እርስዎ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ዋና ነዎት:: ካቶሊክ ማለት ደግሞ የሁሉም ማለት ናት:: ዛሬ እንግዲህ የእርስዎ ቤተ ክርስቲያን በእውነት የሁሉም ናት‍ን?! እርስዎ ከሞሶሎኒ ጋር ሆነው ከሌላው ዓለም ጋር በጠብ አሉ:: እርስዎ የሚመሯቸው ጳጳሳት ኢትዮጵያ ለኢጣሊያን ቅኝ አገር እንድትሆን የሚገባ ነው ብለው ተናገሩ:: ዘመቻውንም የተቀደሰ ዘመቻ ነው በማለት ለዘመቻ የተዘጋጁትን ታንክና ጦር መሳሪያዎች ባረኩ ….::

እርስዎ እንደሚሉት የኢትዮጵያ ሰዎች አገራቸውን ለመጠበቅ ሲሰበሰቡ የኢጣሊያ የአይሮፕላን ቦምብ ጥርግ አድርጎ ቢያጠፋቸው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ነው ብለው ያስባሉን!? ሴቶችንና ሕፃናትን በመርዝ ጭስ ሲፈጅ እግዚአብሔርን ያገለግላሉ ብለው ያስባሉን!? እርስዎ የዓለም ሁሉ አባት ነኝ ሲሉ ሳለ የሞሶሎኒ ባሪያ ሆነዋል:: ኢትዮጵያ እርስዎ ለሚያመልኩት አምላክ ጸሎት ልታሳርግ አትችልም:: ሌላው ዓለም እንደዚሁ ወደ እርስዎ አምላክ ሊጸልይ አይችልም::

እርስዎ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰውዬው ለሞሶሊኒ የሚታዘዙ ሆነዋልና:: እርስዎ መናገር በተገባዎ ጊዜ ዝም አሉ:: አሁንም በቅርብ የገና በዓል ነው:: ለግፍ ጦርነት ወርቃቸውን የሰጡ ጳጳሳትም እንግዲህ ‹‹ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፣ በምድር ላይ ሰላም ይሁን፣ ለሰውም በጎ ፈቃድ ይሁን!›› ብለው ሊዘምሩ ነው:: ይኽንንም መዝሙር ሲያዜሙ በደረታቸው ላይ የወርቅ መስቀል ሳያደርጉ አይቀርም፣ ነገር ግን በጀርባቸው ላይ የእንጨት መስቀል ቢሸከሙ በተሻላቸው ነበር …::

የኢትዮጵያ ታላቅ ባለውለታ የነበሩትና የኢጣሊያን ፋሽስት ጭካኔና ግፍ ለዓለም ሁሉ በማጋለጥ ከኢትዮጵያውያን ጎን የቆሙት ሲልቪያ ፓንክረስት የፋሽስቱ መሪ ቤኒቶ ሞሶሊኒ በሃይማኖት አባቶች ላይ እየተወሰደ ያለው ዕርምጃ ሌሎች ኢትዮጵያውያንን ሊያሸማቅቅ እንደሚችልና ጭፍጨፋውም ውጤታማ እንደሆነ በወቅቱ ለምስራቅ አፍሪካ ለቅኝ ግዛት ሚ/ሩ ለግራዚያኒ ያስተላለፈውን ምስጢራዊ የቴሌግራም መልእክት ‹Ethiopia and Eritrea› በሚለው መጽሐፋቸው እንዲህ ጠቅሰውታል፡-

… The execution of Abune Petros, one of the four Ethiopian bishops, has terrified the leaders and the public. The work of repression against armed groups dispersed in the forest continues. All prisoners have been shot. Inexorable reprisals have been effected against the populations guilty, if not complicity, at least of lack of favorable attitude. A telegram of March 1, 1937.

ትርጉም፡- ‹‹በአቡነ ጴጥሮስ ላይ የተወሰደው የግድያ ዕርምጃ ብዙዎችን እንዲፈሩና እንዲሸማቀቁ አድርጓል፤ ይህ ዓይነቱ እርምጃ ለኢጣሊያን እንዳይገዛ ሕዝቡን በሚያነሣሡና በዱር በገደል በአርበኝነት በተሰማሩት ፋኖዎችም ላይ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል . . . ::››

በተመሳሳይም የፋሽስት ጦር በደብረ ሊባኖስ ገዳም ባሉ መነኮሳት አባቶችና አገልጋዮች ላይ ርምጃ እንዲወስድ ያስተላለፉት ትእዛዝ በተመለከተ በወቅቱ የፋሽስት አዛገሮች የተለዋወጡት ደብዳቤ እንዲህ ይነበባል፡-

*ለኢጣሊያ ምሥራቅ አፍሪካ ጠቅላይ ግዛት*
*የፕሮቶኮል መዝገብ ቁጥር 9325*
*አዲስ አበባ ግንቦት 24/1937 ዓ.ም.*

*ጥብቅ ምስጢር፡- ለጄኔራል ማሌቲ- ደብረ ብርሃን፣*
*ለክቡር ምክትል ገዥ ኤታማጆር- አዲስ አበባ፣*
*ለፖለቲካ ጉዳይ ዋና አዛዥ- አዲስ አበባ፣*
*ለጦር ፍርድ ቤት- አዲስ አበባ፣*
*ለካራቢኜራዎች ዋና አዛዥ- አዲስ አበባ::*

ቁጥር 26609- የደብረ ሊባኖስ ጉዳይ ሙሉ ሓላፊነቱ የእርስዎ እንደሆነ አረጋግጬያለሁ:: የደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኮሳትና ዲያቆናት ሁሉም አንድ ሣይቀር በጥይት እንድትፈጇቸው አዝዣለሁ:: ትእዛዝህን በአስቸኳይ አስፈጽሜያለሁ በሚል ቃል እንድታረጋግጥልኝ ይሁን!

ማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒ::

በወቅቱ በግራዚያኒ ላይ ለተደረገው የግድያ ሙከራ የደብረ ሊባኖስ መነኮሳት እጃቸው አለበት በሚል በገዳሙ መነኮሳትና አገልጋዮች ላይ የተወሰደውን የግድያ እርምጃ ኢጣሊያዊው የታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰር አልቤርቶ ሰባኪ Ethiopia Under Mussolini: Fascism and the Colonial Experience በሚለው መጽሐፋቸው፡-

‹‹… የገዳሙ መነኮሳት በሙሉ፣ የገዳሙ አለቃ አባ ገ/ማርያም ወ/ጊዮርጊስ ጭምር እንዲገደሉ አዘዘ:: ግንቦት 21 ቀን 1937 ጄኔራል ፒየትሮ ማሌቲ በትዕዛዙ መሠረት 297 መነኮሳትን አስረሸነ:: ወደ 153 የሚጠጉ መምህራን፣ ዲያቆናትና ተማሪዎች ወደ ደብረ ብርሃን ከተጋዙ በኋላ የሴራው ተባባሪ ናቸው ተብለው ግንቦት 26 ቀን እንዲረሸኑ ተደረገ …::›› በማለት ገልጸውታል::

ፋሽስት የደብረ ሊባኖሱ ግድያና ጭፍጨፋ የአቡነ ተ/ሃይማኖት ዓመታዊ በዓል በሚከበርበት ግንቦት ፲፪ ቀን ነበር እንዲሆን ያዘዘው:: ከበዓሉ ዋዜማ፣ በበዓሉና ከበዓሉ በኋላም በገዳሙ የተገኙ መነኮሳት፣ ካህናት፣ ዲያቆናትና ከገዳሙ አቅራቢያና ከሩቅ አካባቢ በዓሉን ለማክብር የመጡ አገልጋዮችና ምእመናን ሣይቀሩ የዚህ ጭፍጨፋ ሰለባ ኾነዋል:: ፕ/ር ኢያን ካምፔል ፋሽስት በደብረ ሊባኖስ ያደረሰውን ጭፍጨፋ በገለጹበት፤ ‹‹The Massacre at Debre Libanos Ethiopia 1937:- The Story of One of Fascism’s Most Shocking Atrocities›› በሚለው መጽሐፋቸው፡-

‹‹በግንቦት ፲፬ ቀን የፊንጫ ወንዝ ወደ ደም ጅረትነት ተቀይሮ እንደነበርና የፋሽስት ወታደሮችም በግፍ የገደሏቸውን ሰዎች በላያቸው ላይ አፈር ብቻ በመበተን ለአውሬና ለጅብ ራት እንዲሆኑ በየሜዳውና በየዱሩ ጥለዋቸው እንደነበር::›› ጽፈዋል::

በወቅቱም የኢጣሊያን የጦር አዘገሮች ከግድያውና ከጭፈጨፋው ባሻገርም የገዳሙን ቁልፍ ተርከበው በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ የከበሩ ንዋያተ ቅድሳትን፣ የብራና መጻሕፍትን፣ በተለይም ደግሞ በ፲፮ኛው መቶ ክ/ዘመን በዐፄ ገላውዴዎስ ለገዳሙ በስጦታ የተበረከተውን በወርቅ የተለበጠና በዐራት ሰው ትክሻ የሚነሳውን ትልቅ የብራና ወንጌል ከሌሎች መጻሕፍት ጋር ሰርቀው እንደወሰዱት የታሪክ ድርሳናት ይጠቁማሉ:: በተጨማሪም በገዳሙ ያገኙት ብዙ ሀብትና ቅርስ ያስገረማቸውና ዝርፊያው የጣማቸው የኢጣሊያ ወታደሮች የተደበቀ ወርቅና ብር እናገኛለን በሚል ተስፋ ፈጽሞ ሰብአዊነት በጎደለው ኹናቴ የገዳሙን መካነ መቃብሮች እንኳን ሣይቀር ቆፍረውትና ንደውት ነበር::

በደብረ ሊባኖስ ገዳም በግፍ ስላለቁት፣ ወደ ሶማሊያ ተግዘው በዳናኔ ወኅኒ ቤት ስለሞቱት የገዳሙ ተማሪዎችና በገዳሙ ላይ ስደረሰው አሰቃቂ እልቂትና ዝርፊያ በ፪ሺሕ ፫ ዓ.ም. ነሐሴ ወር ላይ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ያወጣው ‹‹ዜና አብዮሙ ለሰማዕታት ዘ ደብረ ሊባኖስ ደቂቁ ለተክለ ሃይማኖት›› በሚል ርእስ የታተመው አነስተኛ መጽሔት በፋሽስት ኢጣሊያ በገዳሙ የተገደሉትን ሰዎች ቁጥር ወደ ሁለት ሺ ገደማ ያደርሰዋል:: በእርግጥ በፋሽስት ወረራው ወቅት ከደብረ ሊባኖስና ከሌሎች የአገሪቱ ገዳማትና ቅዱሳን መካናት በግፍ የተገደሉ፣ የተጨፈጨፉ፣ የተጋዙ በርካታዎች ናቸው:: ከእነዚህ ገዳማትና ቅዱሳት መካናት የተዘረፉ ቅርሶችና ንዋይተ ቅድሳትም እጅግ የበዙ ናቸው::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ሉዑላዊነትና በሕዝቦቿ ነጻነት ላይ ያላትን የማያወላውል ጽኑ አቋም በሚገባ የሚያውቁ አውሮጳውያን ቅኝ ገዢዎች፣ ወራሪዎችና ተስፋፊዎችም በተለያዩ ዘመናት ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማፍረስና ቢቻላቸውም በራሳቸው ግዛትና ቁጥጥር ሥር ለማድረግ ያልቆፈሩት ጉድጓድ፣ ያልወጡት ተራራ የለም ማለት ይቀላል:: አልተሳካላቸውም እንጂ፤ ይህ ሙከራቸው ደግሞ መልኩንና ይዘቱን ቀይሮ እስካሁንም ድረስ የዘለቀ ነው ማለትም ይቻላል::

የኢትዮጵያ ቤ/ን በውጭ አገራት ወራሪዎችና ቅኝ ገዢዎች ዘንድ ጥርሳቸው እንዲነኩስባትና በተለያዩ ዘመናት ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ያጋጠማቸውን ወረራ፣ የቅኝ ግዛት መስፋፋት በማውገዝና በመቋቋም ረገድ ያደረገችውን ተጋድሎና የከፈለችውን ክቡር መሥዋዕትነት የታሪክ ድርሳናት የሚመሰክሩት ነው:: ቤተክርስቲያኒቱ ለሰው ልጆች ኹሉ ከፈጣሪ በተሰጠ ነጻነት፣ በእውነት፣ በፍትሕ ላይ ያላት ጽኑ የሆነ አቋም ስለ ነጻነታቸው፣ ስለ ፍትሕና ስለ ሰው ልጆች እኩልነት በሚታገሉና በሚጋደሉ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ዘንድ የተሰማ፣ ትልቅ ክብርና ዝና ያለው ነው::

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በሀገራችን በኢትዮጵያ፣ በአፍሪካ፣ በመላው ጥቁር ሕዝቦችና በአጠቃላይም ነጻነታቸውን በሚያፈቅሩና በሚያከብሩ የሰው ልጆች መካከል ያላት አኩሪ ታሪክ፣ ገድልና መልካም የሆነ ምስክርነት በኋላ ዘመን አፍሪካን እንደ ቅርጫ ሥጋ ለመቀራመት ለመጡ አውሮጳውያን እንደ እግር እሳት ነበር ያንገበገባቸው:: እናም ይህን ለጥቁር ሕዝቦችና አፍሪካውያን መመኪያ የሆነ ታሪክ በማጠልሸት፣ የኢትዮጵያንና የሕዝቦቿን ቅርስና ታሪካቸውን ከመሠረቱ ለመናድ፣ በሃይማኖቱ ጽኑ የሆነውንና ለነጻነቱ ቀናዒ የሆነውን ሕዝብ ለመበቀል ሲል ፋሽስት የበቀል በትሩን ዘግናኝና አረመኔዊ በሆነ መልኩ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ አንስቷል::

ስለሆነም የፋሽስት መንግሥት ለሰው ልጆች ሁሉ ነጻነት፣ ለፍትሕ፣ ለፍቅርና ለሰላም በቆመችው በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ለፈጸመው ግፍ፣ ጭፈጨፋና ኢሰብአዊ ድርጊት ይቅርታ ሊጠይቅና ካሣ ሊከፍል ይገባዋል:: ይህን ጥያቄም ቅዱስ ሲኖዶስና የቤተክርስቲያኒቱ ልጆች በአንድነት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሊያሰሙ ይገባል:: ለአብነትም ‹ኒውዮርክ ታይምስ› ከሁለት ዓመት በፊት የአርመን ኦርቶዶክስ ቤ/ክ ከመቶ ዓመት በፊት ቱርካውያን በአርመን ክርስቲያኖችና አብያተ ክርስቲናት ላይ ላደረሱት ጭፍጨፋ፣ ግፍና መከራ የአርመን ቤ/ን መሪና መንፈሳዊ አባት የሆኑት አቡነ አራህም l/አንደኛ የቱርክ መንግሥት ለቤተ ክርስቲያኒቱ ተገቢውን ካሣ እንዲከፍል የጠየቁበትንና ያሳሰቡበትን ሰበር ዜና አስነብቦን ነበር:: የኢትዮጵያ የቤተክርስቲያንም በተመሳሳይ ‹የይቅርታና የካሣ› ጥያቄዋን ለኢጣሊያ መንግሥትና ሕዝብ ማቅረብ ይኖርባታል::

ሰላም!

**የአማራ...** *ከገጽ 11 የዞረ*

በተለይም የወጣቱን ሃይልና የምሁሩን ክፍል የማያወላውል ድጋፍ ማግኘት የግድ ነው:: እንዳያማህ ጥራው አይነት ሳይሆን ፣ በክልሉ ጉዳይ ያገባናል ከሚሉ ሃይሎች ጋር በጋራ ለመስራት በቅንነት በሩን ክፍት ማድረግ አለበት:: ስልጣንን ለህዝብ ለመመለስ እርምጃ መጀመር አለበት:: ነገር ግን በተለመደው አፋኝነት ፣ ብልጣብልጥነትና አግላይነት እቀጥላለሁ ፤ የክልሉን ውስብስብ ችግሮች በትህነግ/ወያኔ መፍትሄዎች እመልሳለሁ ካለ መጀመሪያ የአሾክሻኪነቱን በትር መቅመሱ አይቀርም::

## ሐ. የአማራ ብሄርተኝነትና የምሁራን ሚና

ትእግስቱና ሆደ ሰፊነቱ ለመገፋት የዳረገው የአማራ ህዝብ ብሄርተኝነት መንፈስ እንደ ቋያ እሳት እየተንቀለቀለ መሆኑ ዓይን ላለው ሁሉ በግልፅ ይታያል:: ይህ ስሜት በጉባኤውም ላይ በጉልህ ተንፀባርቋል:: በሌላ በኩል አማራና ብሄርተኝነት የሚሉት ቃላት አብረው መታየታቸው ፣ ገና ከወዲሁ ከየአቅጣጫው ጩኸት አስነቷል:: አንዳንድ ሚርተኞችና ፀረ-አማራ ጉጅሌዎች ‹‹የአማራ ምሁራን የጦርነት ነገሪት እየጎሰሙ ነው›› ብለው ማራገብ የጀመሩት ገና ጉባኤው ሳይጋመስ ነበር:: እነዚህ በጎሰኝነት የሰከሩ ቡድኖች በአማራው ላይ ይህ ሁሉ ግፍ ሲወርድበት ትንፍሽ ያላሉ ናቸው:: ዛሬ እንዲህ ምን አንዳንገበገባቸው

በነገራችን ላይ ጠቅላይ ሚ/ር አብይ በሁለተኛው ቀን ከቀትር በኋላ በድንገት በአዳራሹ ውስጥ ሲገኙ ታዳሚው በግርምትና በጭብጨባ ነበር የተቀበላቸው:: በግል እንደታዘብኩት እኝህ ሰው ከህዝብ መደባለቅ የማይቸግራቸው ፣ ማራኪ ስብዕና ያላቸውና የአድማጫቸውን ቀልብ በቀላሉ መግዛት የሚችሉ ናቸው:: ያለአንዳች የአግቱልኝና ጋርዱልኝ ጋጋታ ወደ መድረኩ በመውጣት ስጋታቸውን ሲገልፁ ፣ ‹‹በአገሪቱ ተዘዋውሬ ያየሁትና የሰማሁት ችግርና ምሬት ደረጃ አስደንግጦኛል:: ከፊታችን የተደቀነውን ታላቅ ብሄራዊ አደጋ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር ተሰባስበን ካልሆነ በጭራሽ አንፈታውም›› ብለዋል::

በአገራችን መጨረሻው ያልለየለት ቀውስ መስፈኑ እውነት ነው:: በአንድ በኩል ማህበረሰቦች ከጨቋኝ ፣ ዘረኛ ፣ ሌባና አረመኔ መንግሥታቸው ጋር ተፋጥጠዋል:: ቁጭት ፣ ጥቃትና ቁጣ የቀሰቀሰው ህዝባዊ ማዕበል አስፈሪነቱ ታይቷል:: በሌላ በኩል ስርዓቱ የፈለፈላቸው የጎሳ ነጋዴዎች ፣ የራሳቸውን ሥልጣንና ጥቅሙን ለማዳን ማህበረሰቦች በጥርጣሬና በጥላቻ ለደም መፋሰስ እንዲሰለፉ ደፋ ቀና ይላሉ:: እምቢተኝነት ፣ አድማ ፣ ግርግር ፣ አመፅ ፣ ግጭት ፣ መፈናቀል ፣ የንብረት ውድመት ፣ የህይወት መጥፋት የዕለት ተዕለት ክስተቶች ከሆኑ ከራርመዋል::

ስጋት አይሆንም::

ብሄርተኝነት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ልያዘው ወይስ ልተወው እያሉ በአመክንዮ የሚወስኑት ምርጫ አይደለም:: በ‹‹ዘር›› የሚተላለፍም ደመነፍሳዊ ባህሪ አይደለም:: ማህበረሰቦች ካለፈ ታሪካቸውና ተመክሮአቸው ተነስተው ወደፊት የተደቀነባቸውን የህልውና ስጋት ለመቅረፍ የሚከተሉት የትግል ስልት ነው:: መንግሥት ለማህበረሰቦች ዘላቂ ዋስትና መስጠት ካቃተው ፣ ተጠቂዎች ህልውናቸውን ለማስጠበቅ ብሄርተኛ መንገዶችን ይከተላሉ:: የአማራም ብሄርተኝነት በዚሁ ዓይነት ሂደት የተፈጠረ በመሆኑ ፣ ሊያስገርመን የሚገባው እስከዛሬ ተዳፍኖ መክረሙ ነው::

የአማራ ብሄርተኝነት ለሌሎች ኢትዮጵያውያን ስጋት የማይሆንበት ተጨማሪ ምክንያት የብሄረሰቡ ትክለ ስብዕና ነው:: አማራ የጥበብ መሃንዲስ ፣ ታሪክ ሰሪ ፣ ድንበር አስከባሪ ፣ አስተዋይ መሪ ነው:: ለአከርካሪው ሲቃጡት አናት የሚያፈርስ የጀግኖች አውራ ነው:: እንደ ኢትዮጵያ ቤተሰብነቱ አማራ የእግዜር የበኩር ልጅ ነው:: በሃይማኖቱ ፣ በቁርጠኝነቱ ፣ በደግነቱና በትዕግስቱ ያሰበበት ደራሽ ነው::

አማራው በታሪኩ ዘውግ ተኮር ጥቃት ሲደርስበት የመጀመሪያው አይደለም:: ቢያንስ የቅርቡን የፋሽስት ጣልያንን ዘመነ አፀባ ማስታወስ ይቻላል:: ነገር ግን ይህ ሆደ ሰፊና አስተዋይ ህዝብ አገሩን ከራሱ በማስቀደም ለባንዶችም ፣ ለፊርማቶሪዎችም ፣ ለአስካሪዎችም ፣ ለልጆቻቸው ለገንጣይ አስገንጣዮችም የሰላም እጁን ዘርግቶ ከማቀፍ ውጭ የበቀል በትር ሰንዝሮ አያውቅም:: አማራ በኩሩና ታላቅ ስብዕናው የተነሳ ብሄርተኝነቱ ከበታችነት መርዝ የፀዳ ነው:: ስለዚህ ለማንም ወገን ስጋት አይደቅንም::

## ታዲያ ምን ይደረግ ?

የአማራው ብሄርተኝነት ንቅናቄ ገዥ መንፈስ ብሄራዊ እኩልነትና ፍትህ ነው:: አማራው አንገቱን ቀና አድርጎ በእኩልነት የሚኖርባት አገር በመጠየቁ ሊያፍርበት አይገባም:: እስካሁንም ከትዕግስትና ከፀሎት ባለፈ ፣ ችግሩ በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝለት አቤት ሲል ኖራል:: ፕሮፌሰር አስራትና አጋሮቻቸው በዚያች ቀውጢ ቀን የመላው አማራን ድርጅት በመመስረት ድምፃቸውን ለማሰማት ሞክረዋል:: በርካቶችም የንብረት ፣ የአካልና የህይወት መስዋዕትነት ከፍለውበታል:: እነዚህን ፋና ወጊዎች ታሪክ ሲዘክራቸው ይኖራል::

ዛሬም የአማራ ህዝብ የተጋረጡበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መፍታት የሚችለው በሰላማዊ ትግል በየደረጃው ነው:: በውይይቱ እንደተሰመረበት የአማራው ብሄርተኝነት እርምጃ የሚጀምረው በኢትዮጵያዊነቱና በአማራነቱ መካከል የተፈጠረበትን ብዥታ በማጥራት ነው:: ታሪክ እንደሚነግረን ከራሱ ከአማራው ገዥ መደቦች ጭምር ፣ በየጊዜው የሚነሱ ባዕዳንና አገር በቀል ጠላቶቹ የአማራውን የብሄር ንቃተ ህሊና ክፉኛ ይፈሩታል:: ስለዚህም በኢትዮጵያዊነቱና በአውራጃዊነቱ መካከል ያለውን ብሄረሰባዊ ማንነቱን ለማደብዘዝ ይተጋሉ:: የዘመናችንም አንዳንድ የዋህ ሊቃውንት እንደሚመኙት ፣ አማራው ብሄርተኝነት የህልውና አልፋና ኦሜጋ በሆነበት ሥርዓት ውስጥ ማንነቱን ችላ ብሎ ወይም ነገሮች በተዓምር እስኪቀየሩ እጁን አጣጥፎ መቀመጥ አይችልም::

**የአማራ ብሄርተኝነት ለሌሎች ኢትዮጵያውያን ስጋት የማይሆንበት ተጨማሪ ምክንያት የብሄረሰቡ ትክለ ስብዕና ነው:: አማራ የጥበብ መሃንዲስ ፣ ታሪክ ሰሪ ፣ ድንበር አስከባሪ ፣ አስተዋይ መሪ ነው:: ለአከርካሪው ሲቃጡት አናት የሚያፈርስ የጀግኖች አውራ ነው:: እንደ ኢትዮጵያ ቤተሰብነቱ አማራ የእግዜር የበኩር ልጅ ነው:: በሃይማኖቱ ፣ በቁርጠኝነቱ ፣ በደግነቱና በትዕግስቱ ያሰበበት ደራሽ ነው**

እናውቃለን:: ሌሎች ደግሞ የበግ ለምድ ለብሰው ‹‹ኢትዮጵያ አለቀላት›› ፣ ‹‹ወያኔ በፈለገው መስመር ገባንለት›› የሚል ሙሾ ያወርዳሉ:: ለነዚህም ሰዎች 27 ዓመት ሙሉ ከማለቃቀስ የተሻለ መፍትሄ አላመጣችሁም እንላቸዋለን::

ነገር ግን በቅን ልቡና ፅንፈኛ ብሄርተኝነት አገራችንን ይዞአት የገባበትን መቀመቅ በማየት የአማራ ብሄርተኛ መነሳሳት ያሰጋቸው አሉ:: ከነዚህ አንደኛው ጠቅላይ ሚኒስትሩ አብይ ናቸው:: ዶ/ር አብይ ከጎንደርና ባህር ዳር ህዝብ ጋር ባደረጓቸው ውይይቶች የክልሉን በቁጭትና ቁጣ የነደደ ስሜት በትክክል ተገንዝበዋል:: ስለዚህም ለምሁራኑ ባደረጉት አጭር ንግግር ኦህዴዶች ‹‹ለከት በሌለው ብሄርተኝነት ትልቁን የኦሮሞን ህዝብ አውርደን መንደር ውስጥ መክተታችን ስህተት ነበር:: እናንተም በስሜት የአማራን ትልቅ ህዝብ በዚያ መንገድ እንዳትነዱት:: ለብሄርተኝነታችሁ ገደብ ማበጀት እንዳትዘነጉ ፣ በጥናትና ምርምር ደግፉት›› ሲሉ አደራ ብለዋል::

ገና አሁንም ማህበራዊ ሰላም ፣ ብሄራዊ ሰላም የለም::

## መ. የአማራ ብሄርተኝነት ስጋት የማይሆነው ለምንድነው?

እነዚህ ከየፋካቸው ለሚንጫጩ ወገኖች ፣ ‹‹አይዟችሁ አትስጉ›› ማለት ብቻ በቂ አይደለም:: የአማራ ብሄርተኝነት ለሌሎች ኢትዮጵያዊን ወንድሞቹ ስጋት የማይሆንባቸው ነባራዊና ታሪካዊ ምክንያቶች አሉ:: በእኔ አመለካከት አንደኛው ምክንያት የአማራ ብሄርተኝነት ሞልቶ ከፈሰሰ በደልና ከተጨባጭ የህልውና አደጋ መነሳቱ ነው:: በጥላቻ የሚነዳ ጎሰኝነት ሳይሆን በአማራ ህዝብ ላይ የተንሰራፋበት ጭቆና ፣ ኢፍትሃዊነት ፣ ማናለብኝነት ፣ ዝርፊያና ዘረኝነት ውጤት ነው:: እውነተኛ የነፃነት ፣ እኩልነት ፣ ፍትህ ፣ ወንድማማችነት ፣ ተስፋ ፣ ክብርና ማንነት ጥያቄ ነው:: ስለዚህም ከሥርዓቱ አቀንቃኞችና ጋሻ ጃግሬዎች ውጭ ለማንም



ስለዚህ አማራው በመጀመሪያ ራሱን እያለ እንደሌለ ከመቁጠርና ከምስለኔ ግዞት አላቅቆ በሁለት እግሩ መቆም አለበት:: አማራው ለህልውናው ሲል አኩሪ ማንነቱን ማስጨበጥና በራሱ መተማመኑን መመለስ ይደር የማይባል ተግባር ነው:: በፌዴራላዊው ሥርዓት ውስጥ በእኩልነት የመደራደር አቅም መፍጠር አለበት:: ይህ ከሆነ እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሥርዓቱ የፈጠራቸው የጋራ ጉዳዮች በብሄራዊ መድረክ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይፈታል:: ነገር ግን ከላይ እንደተገለፀው አማራውን ለይተው ኢላማ ያደረጉትን አደገኛ ተግዳሮቶች በገዛ ራሱ ብሄርተኝነት ስር ተሰልፎ መፍትሄ መፈለግ ግዴታው ነው::

የአማራው ብሄርተኝነት ገና በቅጡ ጥርት ብሎ አልተቀመረ ይሆናል:: ነገር ግን ጥያቄውን ፣ ጠላቱን ፣ ፍላጎቱንና ግቡን በውል ለይቷል:: በማህበረሰቡ ውስጥ የተሰራበትን ትልቅ የመከፋፈል ፣ የማዋከብና ተስፋ የማስቆረጥ ገደል ተራምዷል:: ከሁሉም በላይ አንድ ልብና መንፈስ ሆኗል:: በዚህ ላይ አማራው የታጠቀ ፣ የተደራጀና ሥርዓት ገብ ማህበረሰብ በመሆኑ ፣ ርዕዮቱን በወጉ የሚያስጨብጠውና የሚመራው ካገኘ ለመከተል ዝግጁ ነው::

የአማራ ልሂቃን ይህንን ሰፊ ህዝባዊ መናበብና መነሳሳት በጥበብና በአስተዋይነት ወደ ጠንካራ ንቅናቄ መቀየርና ከዳር ማድረስ ታሪካዊ አደራ አለባቸው:: የህዝባቸውን ውስጣዊ ጥንካሬውንና ተግዳሮቱን ፤ ውጫዊ የሃይል አሰላለፍን በማጤን መሬት የያዘ የትግል ስልት መንደፍ አለባቸው:: ለዚህ ደግሞ የብሄርተኝነት አንቀሳቃሽና መሪ የሆነው ልሂቃዊ መደብ አይነ ጥላውን ገፍፎ መነሳቱ ፣ በተለይ በወጣቱ ምሁር ውስጥ የሚታየው የቁርጠኝነት መንፈስ እጅግ ተስፋ ሰጭ ነው:: መንገዱ አልጋ ባልጋ ነው ማለት ግን አይደለም::

የአማራው ትግል ሊገጥሙት ከሚችሉ ፈተናዎች መካከል ቀንደኛው መንግሥታዊ ሥርዓቱ ነው:: በጣምራ የችግሩ ምንጮች የሆኑት ክልላዊና ፌዴራላዊ አገዛዞች ለአማራው ጥያቄ የሚሰጡት ምላሽ የአማራ ብሄርተኝነትን ባህሪና አቅጣጫ በከፊል ይወስነዋል:: በምክክሩ ወቅት ከጠቅላይ ሚ/ሩም ሆነ ከክልሉ ባለሥልጣናት አዎንታዊ ለውጦች እንደሚከተሉ ፍንጭ ታይቷል:: እንዲያውም የምክክሩ መድረክ ከክልሉ መስተዳድር ጋር በጋራ ለመስራት የሚችልበትን ስልት የሚተልም አንድ ጊዜያዊ ቡድን ሁሉ መስርቷል::

እነዚህ መንግሥታዊ አካላት የህዝቡን ብሶት በቅጡ አዳምጠው በአፋጣኝና በቅንነት የሚመልሱ ከሆነ ፣ ምናልባት የራቃቸውን ህዝብ በሂደት ሊያቀርቡ የሚችሉበት እድል ይኖራል:: ይህም እንኳን ቢሆን የአማራ ብሄርተኝነት እንደ ጉም ተኖ ይጠፋል ማለት አይደለም:: የፖለቲካ ሥርዓቱ እስካለ ድረስ ለአማራው ጥቅምና ልዕልና በሥልጣን ላይ የሚወጣውን አገዛዝ የሚፎካከሩና የሚያተጉ ቡድኖች ያስፈልጋሉ:: አማራው ከእንግዲህም ታሪኩን ፣ ባህሉን ፣ ቋንቋውንና ማንነቱን እንዳይረሳ እንዳመችነቱ መስራት ያስፈልጋል::

ነገር ግን በሥልጣን ላይ ካሉት ከብአዴንም ሆነ ከራሱ ከኢህአዴግ ታሪክ ከተነሳን መሰረታዊ ለውጥ መጠበቅ የዋህነት ይመስለኛል:: ገና ከወዲሁ እንደተለመደው ብሄረሰቡን የማዋከብ ፣ የመከፋፈል ፣ ከሌሎች ወንድሞቹ ለመነጠል ግጭትና አመፅን የማራገብ ምልክቶች እያየን ነው:: የፌዴራሉና የክልሉ መንግሥታት በአፋኝነት ፣ በብልጣብልጥነትና አግላይነት እንቀጥላለን ፤ የአማራውን ፅኑና ውስብስብ ችግሮች እንደተለመደው በትዕዛዝ መፍትሄዎች እንመልሳለን ብለው መግደርደራቸው የማይቀር ይመስላል:: በአጭሩ ኢህአዴግ ባለበት አቋሙ የችግሩ እንጂ የመፍትሄው አካል መሆን አይችልም:: ስለዚህም የአማራ ብሄርተኝነት ቀበቶውን ሳያላላ የችግሮቹ ዋና ምንጭ የሆነውን ሥርዓት ማድረቅን የመጨረሻው ግብ ማድረግ አለበት::

በዚህም የአማራው ትግል አንድ ጎዳና ብቻ ሊከተል አይችልም:: ከአማራው ተፈጥሮ ጋር የሚስማማው ፣ ብዝሃነትን ጥንካሬ የማድረግ ስልት ይመስለኛል:: አሁን እንደሚታየው በግልፅ የአማራ ፓርቲ በማቋቋም ወይም በብዝሃዊ ድርጅቶች ስር ተሰልፎ መታገል ይችላል:: መንግሥታዊ ባልሆኑ የተፅእኖ ቡድኖች ፣ በባህላዊ የአደረጃጀት ሥርዓቶችና ተቋማት አማካኝነትም ትግሉ መፋፋም አለበት:: በውጭ አገር እንደ አሸን የፈሉት የአማራ ድርጅቶችም የብሄረሰቡ አውራጃዊ የታሪክ ቅርስ ነጸብራቆች በመሆናቸው ሊያስደንቅና እንደ ድክመት ሊታይ አይገባም:: የትግሉ ሂደትም እነዚህን ብዝሃነቶች ወደ አንድ ድርጅት በመጨፍለቅ አይጀምርም:: ለአሁኑ ወሳኙ ነገር በጋራ ህዝባዊ ዓላማ ስር መተማመንና መተባበር የሚፈጠርበትንና የሚጎለብትበትን መንገዶች መፈለግ ነው::

ታሪኩን ለማሳጠር የአማራው ተግዳሮቶች እጅግ ሥር ሰደዶች ስለሆኑ ድል በቀላል ዋጋ ሊገኝ አይችልም:: የጊዜ ፣ ጉልበት ፣ አእምሮ ፣ ሀብትና ህይወትንም መስዋእትነቶችን ያስከፍላል:: ለሁሉም በሁሉም ነገር መዘጋጀት ያስፈልጋል:: ካለፉት 27 ዓመታት ተመክሮ መዘንጋት የማይገባው ቁምነገር ፣ ያንድ ወገን ፍላጎትና ድል ዘላቂ ሰላም አለማስገኘቱ ነው:: ስለዚህም የአማራው ብሄርተኝነት ለአፍታም ቢሆን ትልቁን አገራዊ ስዕል ኢትዮጵያዊነቱን ከማየት ሊዘናጋ አይገባም:: ይህ ደግሞ አማራው በመላ ታሪኩ የኖረለትም የሞተለትም ጉዳይ ስለሆነ አዲስ እንግዳ አይሆንበትም::

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !

# ከ82 ዓመት በፊት የኢጣሊያ ወረራ ዋዜማ ጃፓን እንደ ምክንያት



ብሩክ መኮንን



ባለፈው ቅዳሜ ሚያዝያ 27 ቀን ከሰባ ሠባት ዓመት በፊት የፋሺስት ኢጣልያ ጦር ድል ተደርጎ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ጀግኖች አርበኞች በድል አድራጊነት ወደ አዲስ አበባ የገቡበት 77ኛው የድል በዓል በመላው ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ተከብሯል::

ኢትዮጵያዊያን አባት እናት አያት ቅድመ አያቶቻችን ለነፃነታቸው፤ ለአገራቸው ሉዓላዊነትና ክብር የከፈሉትን መስዋዕትነት፤ ደማቸውን አፍስሰው፤ አጥንታቸውን ከስክሰው የሰጡንን ድልና ነፃነት ምን ያህል ዋጋ እንደተከፈለበት ለቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍበትን መንገድ የማመቻቸት ኃላፊነትና ግዴታ አለብን::

ከዛሬ 77 ዓመት በፊት ድል የተነሳው የኢጣልያ ጦር ወልወልን እንደ ጦርነቱ መነሻ ምክንያት በማድረግ ከአርባ ዓመት በፊት በአድዋ ተራሮች ላይ የደረሠበትን ሽንፈት ለመበቀል ወረራ እንደፈጸሙብን የሚያወሱ ታሪካዊ መዛግብትና መጽሐፍት አንብበናል::

በተለያዩ ጊዜያት የኢትዮ-ጣልያን ሁለተኛው ጦርነትን በተመለከተ የሚወጡ የምርምርና የጥናት ጽሑፎች የተለያዩ ምክንያቶችን ለጦርነቱ መንስኤ ናቸው ሲሉ ያቀርባሉ:: ከዛሬ 82 ዓመት በፊት የጃፓን ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ በብዛት መጉረፍና በሁለቱ መንግሥታት መካከል የተጀመረው የተጠናከረ ወዳጅነት አስግቶት ነው የሚለው እንደ ምክንያት ይጠቀሳል::

ከ82 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አገራቸውን ወደ ዘመኑ የስልጣኔ ጎዳና እንድትበቃ የሚያግዝና አገራቸውን ዙሪያዋን ከከበቡ ቅኝ ገዥ የአውሮፓ መንግሥታት ተፅዕኖ ለመቋቋም ሁነኛ ወዳጅና አጋር ፍለጋ ላይ ነበሩ::

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፍለጋቸውን በጥንቃቄ እያካሄዱ እያለ የጃፓን መንግሥት የሥልጣኔ ታሪክ ቀልባቸውን የገዛው የውጪ ጉዳይ ሚንስትራቸው ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት አጋር ጃፓን እንደሆነች ንጉሱንና ሌሎች ባለሥልጣናት ማሳመን ቻሉ::

በርግጥም ኢትዮጵያዊያን ጃፓኖችን እንደ ወዳጅና እንደ አጋር ለመቀበል አላመነቱም:: ይህንን ተከትሎ በርካታ የጃፓን የንግድ ኩባንያዎች ተወካዮች ለሸቀጦቻቸው ገበያ አፈላላጊ ጃፓናዊያን ነጋዴዎች፣ የጃፓን መንግሥት ልዑካን ከኢትዮጵያ ጋራ በንግድና በፖለቲካ ግኑኝነታቸውን ለማጠናከር ወደ ኢትዮጵየ በብዛት ይመጡ ጀመር::

በተለይ ደግሞ "ካታጋዋ ናካሽያ" የተባለ ነጋዴና ደላላ ባልደረቦቹ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣቱ በአዲስ አበባ ደማቅ አቀባበል ተደረገላቸው:: የናጋሳኪ አሶስየሽን ፎር ኢኮኖሚክ ኢንቨስትጌሽን ኦፍ ኢትዮጵያ የተባለ በ1932 ዓ.ም. በናጋሳኪ የተመሠረተው በአስመጪና ላኪነት ሥራ የተሠማራ (ኒኪኪሻ) የተባለ ኩባንያ ተወካይ ነኝ ሲል ካታጋዋና ካሺያ ከኢትዮጵያ ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ተገናኝቶ ስለሁለቱ አገሮች ግንኙነት ሠፊ ውይይት አደረገ::

ጃፓናዊው ነጋዴ ካታጋዋ ናካሽያ ከውጪ ጉዳይ ሚነስትሩ ጋራ ከተወያዩ በኂላ ለናጋሳኪ የንግድ ምክር ቤት በላከው ቴሌግራም 12,300,000 ሄክታር የሚጠጋ የእርሻ መሬትን ለጥጥ እርሻ፣ ለትንባሆ ማልሚያ፣ ለሻይ ቅጠል ልማት፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ እርሻ በተለይ ደግሞ 1,500,000 ሄክታሩን ለመድሐኒት መሥሪያ ግብዓት የሚሆን፤ እንዲሁም ኦፕየም የተባለውን አደንዛዥ ዕፅ ለማልማት የሚያሥችል የመሬት ሊዝ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ሥምምነት መድረሱን አሳወቀ::

ይሄ ጃፓናዊ ነጋዴ ለዚህ ግዙፍ የእርሻ ልማት ላይ ለማሠማራት 650 ሺህ ጃፓናውያን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲስፋፉ ከመንግሥት ጋር ከስምምነት ላይ መድረሱንም ለጃፓን የንግድ ማህበረሠብ አሳወቀ::

ይህ የቴሌግራም መልዕክት ቶኪዮ የውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤት ባለስልጣናት ዘንድ ሳይደርስ የተለያዩ የጃፓን ጋዜጦች እጅ ገባ:: ይህንኑ በተመለከተ ኦሳካ አሳሂ የተባለ የጃፓን ጋዜጣ ዘገባውን አተመ:: ከዚያ በኂላ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ የጣልያን ታዋቂ ጋዜጦች ዘገባውን እያጋነኑ እየጨማመሩ በማተም መላው አውሮፓ ጉዳዩን በትኩረት እንዲከታተል አደረጉት:: አውሮፓውያን ጃፓን በኢኮኖሚና በፖለቲካ ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ልትቆጣጠር ትችላለች የሚል ስጋት አደረባቸው:: እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ኢጣልያ እያንዳንዱን የጃፓኖች እንቅስቃሴ መከታተል ግድ አላቸው::

ከወራት በኂላ በኢትዮጵያ መንፈቅ ያህል ከርሞ የነበረው ካታጋዋ ናካሺያ ወደ ሀገሩ ተመለሰ:: ወደ ሀገሩ ያደረሠችው መርከብ መልሕቅዋን በጣለችበት ፖርት ሞጂ 130 ጃፓናውያን ባለኢንዱስትሪዎች እንዲሁም የናጋሳኪ የንግድና የኢንዱስትሪ ምክር ቤት አባላት ደማቅ አቀባበል አደረጉለት::

በአቀባበል ሥነሥርዓቱ ላይ ለተገኙት ጋዜጠኞች መግለጫ የሰጠው ካታጋዋና ካሺያ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ የደረሰው የንግድ የልማት ሥምምነት መጭው ጊዜ ለጃፓን አምራቾች ሠፊ ገበያ ካላት ኢትዮጵያ ጋራ የሚሰሩበት ይሆናል ሲል ተናገረ::

የካታጋዋ ናካሺያን ወደ ሀገሩ መመለስና የሰጠውን መግለጫ እንዲሁም በተከታታይ የሚወጡ የጃፓን ጋዜጦች ዘገባን የሚከታተለው የኢጣልያ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለብሪታኒያ እና ለፈረንሣይ ዲፕሎማቶች ጉዳዩን በትኩረት ይከታተሉ ዘንድ መወትወቱን አላቆመም ነበር::

የኢጣልያ መገናኛ ብዙኃን ኢትዮጵያ ከሶስቱ የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት ዕውቅና ውጭ አውሮፕላኖችን መድፎችን የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችን ለመግዛት ወደ ጀርመን ከፍተኛ ልዑካን ቡድን መላኳን፤ ኢትዮጵያ ይህንን

ዕርምጃ ስትወስድ የኢጣልያን አውሮፕላን አምራች ኩባንያዎችን የመሸጫ ዋጋ እንኳን ለማወቅ ፍላጎት አለማሳየትዋን እና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ጃፓንን በአጋርነት ከመያዙ በተጨማሪ ወደ ጀርመን ማድላቱ የያዘውን ፀረ አውሮፓዊ አቋም ያሳያል ሲሉ ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ማካሄዳቸውን ቀጠሉ::

የጃፓን መንግስት የካታጋዋ ናካሺያና ሽሪኮቹ በኢትዮጵያ ጀመርነው ያሉትን እንቅስቃሴ በቅርበት ሲከታተል ቆይቶ የኢትዮጵያ መንግስት ለጃፓናዊያኑ 2,500 ሄክታር የሚሆን መሬት በአዲስ አበባ ዙሪያ በኪራይ መስጠቱን ማረጋገጡን ይህም ሥምምነት የዓለም ዓቀፍ ህግ መሠረት እንዲሆን ውሉን የማዘጋጀት ሥራን የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነት መውሠዱን የሚያወሡ ዘገባዎች የታወቁ የጃፓን ጋዜጦች አትመው አስነበቡ:: እነዚህ ዘገባዎች ደግሞ በውጥረቱ ላይ ቤንዚን እንደማርከፍከፍ ያህል አስተዋፅኦ አደረጉ:: የፋሺስት ርዕዮተ ዓለም አቀንቃኝ የሆነው እንደ "አዛኒዬኮሉኒያሎ" ያሉ የኢጣልያን ጋዜጦች በምሥራቅ አፍሪካ የጃፓኖች ወዳጅነት ቀጣይ እንቅስቃሴ በዝምታ የሚታየው እስከመቼ ነው ሲሉ ጠየቁ::

ከወራት በኂላም ማርች 18 ቀን 1934 (እ.ኤ.አ) ቤኒቶ ሞሶሎኒ በሮም ኦፔራ ሐውስ ደጋፊዎቹን ሰብስቦ ባደረገው ንግግር "…አገራችን ኢጣልያ ልትፈፅመው የሚገባ ሁለት ታሪካዊ ግዴታዎች አሉ:: እነዚህን በሥራ ላይ የማዋል ኃላፊነት ደግሞ የእኛ የልጆችዋ ነው:: አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ አገራችን ግዛትዋን ወደ ሰሜንም ሆነ ወደ ምዕራብ የማስፋፋት ዕድል የላትም:: የግዛት ማስፋፋትን በሥራ ላይ ለማዋል የምትችለው ወደ አፍሪካና ወደ እስያ ነው::

…እኛ ኢጣልያናዉያን ወደ ሩቅ ምስራቅም ሆነ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አፍሪካ የምናደርገው መስፋፋት በዚያ ላሉ ህዝቦች ብልፅግናና ሥልጣኔን ይዘን ነው:: ይህንን እንቅስቃሴያችን ለማስቆም ማንም ሊሞክር አይገባውም:: እንቅስቃሴያችን፤ የሞኖፖሊ ሠፋፊ እርሻ መሬቶችን ለማግኘትና ማዕድን ለማውጣት፣ ውል ለመዋዋልና ለምርቶቻችን ገበያ ፍለጋ አይደለም :: በዚህ መሰሉ ተግባር የተሰማሩ ወገኖችን ላስጠነቅቅ እወዳለሁ::

ኢጣልያ፤ በቅርቡ ጃፖን የኢትዮጵያን ጦር ኃይል በዘመናዊ የጦር አውሮፕላኖች፣ ታንኮችና መድፎች፤ እንዲሁም የተለያዩ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን በማሥታጠቅ ላይ እንደምትገኝ አረጋግጣለች:: ስለዚህም ኢጣልያ በአፍሪካ ቀንድ ባሏት ቅኝ ግዛቶች፤ ኤርትራና የጣልያን ሱማሌ ላንድ ያለውን የጦር ኃይል ማንኛውንም ጥቃት እንዲመክት የሚያስችል አቅም እንዲኖረው እናደርጋለን::" አለ::

ይህንን የቤኔቶ ሞሶሎኒን ንግግር ተከትሎም በኢጣልያ ፓርላማ የኢጣልያን ቅኝ ግዛቶች አሥተዳደር ኃላፊ አሌክሳንደሮ ሎስፓ ጃፓን በኢትዮጵያ እያደረገች ያለው መጠነ ሠፊ እንቅስቃሴ አደገኛ መሆኑን በመግለፅ ማስጠንቀቂያ አዘል ማሳሰቢያ በመስጠት በአፍሪካ ቀንድ ያለውን የኢጣልያ ጦር በተጠንቀቅ እንዲቆም መንግሥቱ መወሰኑን ኔፕልስ ላይ ለመገናኛ ብዙኃን ይፋ አደረገ::

ይህንን መሰሉ የኢጣልያ መንግሥት አቋም፤ እንዲሁም በአውሮፓ የሚታተሙ ታዋቂ ጋዜጦች "…ጃፓን በኢትዮጵያ የሚውል ነዋየ ፍሠት ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ላቀ ደረጃ ተሸጋግሯል::…" የሚለው ዘገባ እውነት መሆኑን እንዲመረምር የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ የአሜሪካ መንግስት ወኪል የሆነውን ኤዲሰን ሳውትሃርድን አዘዘ::

አሜሪካዊው ዲፕሎማት በጃፓን እና በኢትዮጵያ መካከል ተደረጉ የተባሉ የተለያዩ ሥምምነቶችንና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ ይዘግቡ የነበሩት የአውሮፓ አገራት ጋዜጦች መሆናቸውን አረጋገጠ :: ከዚህም በተጨማሪ ጃፓኖች በብዙ መቶ ሺህ ሔክታር በኢትዮጵያ ሊያለሙ አቅደዋል የተባለው የጥጥ እርሻንም በተመለከተ ቀደም ብሎ ፈረንሳዊያን፣ ጀርመናውያንና የቤልጅየም ዜጎች ሞክረው መክሠራቸው እየታወቀ ጃፓኖች ደፍረው በመሥኩ መዋዕለ ነዋይ ለማፍሰስ ወስነዋል የተባለውም ምንም ማረጋገጫ እንዳላገኘለት ለስቴት ዲፓርትመንት ሪል ስቴት ዲፓርትመንት አሳወቀ::

አሜሪካዊው ዲፕሎማት በወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ በሺዎች የሚቆጠሩ ጃፓናውያን በመግባት በተለያዩ ሥራዎች ላይ ተሠማርተዋል የሚለውን ወሬ ለማረጋገጥ ተንቀሳቀሰ:: በ1931 ዓ.ም የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ጃፓንን ሲጎበኙ በአገራቸው መዋዕለ ነዋይ ለማፍሰስ የሚፈልጉ ጃፓናዊያንን ወደ ኢትዮጵያ ቢመጡ የሚያገኙት ርካሽ የሠው ጉልበት፤ ለም የሆነ ጠፍ የእርሻ መሬት እና ሌሎችም በአጭር ጊዜ ውስጥ አትራፊ ያደርጋችኂልና ኑ! ሲሉ የቀሰቀሱትን የሚል ማግባባት ሠምተው የመጡ አንዳንድ ጃፓናዊያን እንኳን በኢትዮጵያ የነበራቸው ቆይታ ፈታኝ አክሣሪ ሆኖ ወደ ሀገራቸው መመለሻ ገንዘብ ማጣት ድረስ እንደተሰቃዩ ማረጋገጡን የሚያሳይ መረጃ ወደ ዋሽንግተን በመላክ የኢጣልያ መንግስት እንዲሁም የአውሮፓ ጋዜጦች የሚዘግቡት ዘገባ መሠረተ ቢስ ነው ሲል አስተባበለ::

የአሜሪካ መንግሥት ኢጣልያ በምስራቅ አፍሪካ ያለ ጥቅምዋን ወደ ኢትዮጵያ መዋዕለ ነዋይ ለማፍሰስ በሚጎርፉ ጃፓናዊያን ምክንያት ላጣ እችላለሁ ከሚል ሆን ተብሎ የተፈበረከ ፍርሐትና ሥጋትን በማመካኘት የጦር ኃይሏንም ወደ ምሥራቅ አፍሪካ የቅኝ ግዛቶችዋ በገፍ ለመላክና ለማደራጀት የተጠቀመችበት ስልታዊ ዘዴ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ደረሰ::

የኢጣልያ ጋዜጦችና የፋሺስት ዲፕሎማቶች በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ጃፓን ወደ ኢትዮጵያ በብዙ ሺህ የሚጠጉ ጃፓናውያንን በመላክ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በመመደብ በአፍሪካ የመሥፋፋት እንቅስቃሴን ቀጥላለች እያሉ መወንጀላቸውን አላቆሙም::

በኢጣልያ እና በኢትዮጵያ መካከል ወልወል ላይ የተከሰተውን የድንበር ግጭት ተከትሎ ሙሉ ለሙሉ ወደ ጦርነት ከመገባቱ ከወራት በፊት በታተመ አንድ መጽሐፍ፤ "…ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ ጃፓኖች ከአባይ ሸለቆን ከሚዋሰኑት የኢትዮጵያ ከፍተኛ ተራሮች መልካ ምድር አንስቶ እስከ ቀይ ባህር መዳረሻ፤ ብሎም እስከ ህንድ ውቅያኖስ አቅራቢያ ያለ፤ ለጥጥ እርሻ ምቹ ለም የሆነ 750 ሺህ ሔክታር መሬትን ለጃፓናዊያን አከራይታለች::

ይህንን ሰፊ መሬት ለማልማት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጃፓናዊያን ወጣቶች ወደ ኢትዮጵያ አምርተው በዚያ ሰፍረዋል:: ጃፓናዊያኑ ወጣቶች ሚስቶቻቸውን ይዘው አልሄዱም:: ምክንያቱም ኢትዮጵያዊያን ሴቶችን አግብተው ወልደውና በዝተው በዘላቂነት እዚያ እንዲኖሩ የተወጠነ ውጥንን በስራ ለይ ለማዋል እንዲመች የተዘጋጀ እቅድ ነው::…" ሲል ደራሲው ሁኔታውን ገልጾ ነበር::

የኢጣልያን ፕሮፖጋንዲስቶችና ፖለቲከኞች ይህንን መሰል ዘገባዎችን እንደ መረጃ በመጥቀስ ኢትዮጵያን ለመውረር የሚያደርጉትን ዝግጅት ፍትሐዊ ለማሳመሰል ከመጠቀማቸው በተጨማሪ በኢትዮጵያ ላይ ሌሎችም፤ እንግሊዝና ፈረንሳይ መንግስታት የተዛባና በጥርጣሬ የተሞላ አቋም እንዲኖራቸው አድርጓል::

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ "ህይወቴና የኢትዮጵናያ እርምጃ" በተባለ መጽሐፋቸውም "…ኢጣልያውያን ያለማቋረጥ በሚነዙት ሃሰተኛ ወሬ የፈረንሳይ መንግሥት እና የእንግሊዝ ንጉሠ ነገሥታት በዙሪያቸው ባሉ ቅኝ ግዛቶቻቸው ያላቸውን ጥቅም ሊያሳጣን ይችላል ብለው ሰግተው ነበር::

መንግስታችን ከሌላ መንግስት ጋራ ምንም አይነት ሚስጥራዊ ውልም ሆነ የሞኖፖሊ ኮኔክሽን ውል አልፈረመም ብለን ለማስረዳት ብንሞክርም ፓሪስ እና ለንደን ሊቀበሉንና ሊያምኑን ተቸግረው ነበር::

…ሌላው ይቅር የሶቪየት ራሽያ እንኳን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ርዕዮት እያራመደች፤ ጃፓን ኢትዮጵያን ትረዳለች የሚለውን የኢጣልያኖች በሬ ወለደ ክስ መረጃ ተቀብለው ኢትዮጵያን ከመደገፍ ይልቅ ለኢጣልያ ወግነው የኢጣልያን አቋም ደግፈው ነበር::…" ብለዋል::

ኢጣልያኖች:- ጃፓኖች በኢትዮጵያ ሰፊ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስና በሺዎች የሚቆጠሩ ጃፖናዊያንን ኢትዮጵያ ውስጥ እያሰፈሩ ነው በሚል ውንጀላና ክስ መላውን የአለም ማህበረሰብ ኢጣልያ በ1934—1935 እ.ኤ.አ ኢትዮጵያን ለመወረር ሲያደርገው የነበረውን ዝግጅት አይቶ እንዳላየ እንዲሆን ማድረግ ችለው ነበር:: ከዚህ በተጨማሪ፤ ወረራውን በተመለከተም ኢትዮጵያ ወደ ሊግ ኦፍ ኔሽን ያቀረበችው አቤቱታ ፍርደ ገምድላዊ ውሳኔ እንዲወሰንበት አድርጓል ብለው የሚያመኑ የታሪክ ተመራማሪዎች አሉ::

ያም ሆነ ይህ ከ82 አመታት በፊት ኢጣልያ፤ አገራችንን በግፍ ለመውረር ጃፓንን እንደ ምክንያት ተጠቅማ እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል:: አያት ቅድመ አያቶቻችን ለአምስት አመታት በዱር በገደሉ በጀግንነት ከወራሪው ጋር ተፋለመው በደማቸው አመሐ የደመቀውን የነፃነት ሰንደቅ ከፍ አድርገው በማውለብለብ ወራሪውን የጣልያን ጦር እንደ ጃፓን ስኒ ሰባብረው ድል ተቀዳጅተዋል::

ባሳለፍነው ሳምንት 77ኛውን የድል በዓል ስናከብር፤ ሁላችንም፤ ኢትዮጵያ! ነፃነትዋ ተጠብቆ፣ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም እንድትኖር ቃል መግባት ብቻ ሳይሆን መጪው ተረካቢና ተተኪ ትውልድ በታሪኩ ደምቆና ኮርቶ አገሩንና ማንነቱን ጠብቆ እንዲኖር ዘላለማዊዉን ታሪክ ሳይበረዝና ሳይከለስ በማውረስ ጭምር ሊሆን ይገባዋል::

***:- ይህንን ፅሁፍ ለማዘጋጀት A JAPANESE SCOUNDREL'S SKIN GAME እና ሌሎች መዛግብትን ፀሐፊው በግብአትነት ተጠቅመዋል::***

# “ሕዝባዊ ሲኖዶስ ሊቋቋም ይገባል”



ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

ቅዱስ ሲኖዶስ ማለት የተቀደሰ ጉባኤ ማለት ነው፤ በፍትሐ- ነገሥቱ እንደተደነገገው ሲኖዶስ ማለት ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም የጳጳሳትና የሊቃውንት ማኅበር ወይንም ሸንጎ ወይንም ስብሰባ አልያም ጉባኤ ማለት ነው:: በዓመት ሁለት ጊዜ የሚካሄደው የጳጳሳት ጉባኤ መጠርያም ይሆናል:: ይህ ጉባኤ ታሪካዊ አመጣጡ ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ ያለ ሲሆን ከጥንት ጀምሮ ቅዱስ ሲኖዶስ እንከን የለሽ ውሳኔ የሚተላለፍበት፤ ሁሉን በእኩልነት የሚያይ ጉባኤ ነው፤ ነገር ግን በቅዱስ ሲኖዶስ ስም እንደ ዓለማውያኑ ሸንጎ የሐሰትና የቡድን ውሳኔ የሚተላለፍበት መንፈስ ቅዱስ የሚመራው ሳይሆን የግለሰቦች ፍላጎትና ጥቅም የሚዘውረው ሲኖዶስ ከሆነ እግዚአብሔር ስለማይደሰትበት የሲኖዶሱ ልዕልናና ቅድስና አጠያያቂ ይሆናል::

በትንቢተ አሞጽ መጽሐፍ ላይ እንደተጠቀሰው እሥራኤላውያን እንደዚህ ዓይነት ቅዱስ ጉባኤ በመረጡት ቀን ያደርጉና እግዚአብሔር ተናገረ፤ ፍርድንም ሰጠ ብለው ያውጁ ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር በመንፈሳዊ አቋማቸውና በቅዱስ ሲኖዶሳቸው ስም የሚያካሂዱት ሃይማኖታዊ ያሉትን ተግባራትና ውሳኔአቸውን ተቃውሟቸዋል:: ይልቁንም በእግዚአብሔር ቀን የእግዚአብሔር ፍርድ እያሉ የሚመኩበትን ቅዱስ ጉባኤን በተመለከተ የተቀደሰው ጉባኤአችሁ ደስ አያሰኘኝም በማለት ቃል በቃል ገስጾአቸዋል፤ የጉባኤያቸውንም ውሳኔ እስከነ ድርጊቱ ነቅፎታል፤ ይልቁንም ፍትሕን እስካላመጡና የተበደለን እስካልካሱ ድረስ መስዋዕታቸውን፤ ዝማሬአቸውንና ቁርባናቸውን እንደማይቀበለው አስታውቋቸዋል::

ይህ አይነቱን ሲኖዶሳዊ አሠራር እግዚአብሔር አይደሰትበትም፤ በእንደዚህ ዓይነቱ ቅዱስ በተባለው ጉባኤ ጉቡዓን የሃይማኖት መሪዎች ቢባርኩ ቡራኬያቸውን ወደ እርግማን እግዚአብሔር ይቀይረዋል፤ ቅዳሴያቸውን እግዚአብሔር አይቀበለውም፤ ወንጌል እናስተምር ቢሉ አእምሮውን ጥበቡን ይነሣቸዋል፤ እንዘምር፤ ማኅሌት እንቁም ቢሉ ይጮኻሉ፣ ይጮኻሉ እንዳልጮኹ ኾነው እግዚአብሔር የማይሰማቸው ይኾናሉ::

ዛሬ በብሔር ማንነቱ፤ በትውልድ ስፍራው በጎሳ መሠረቱ ምክንያት በሰው ላይ ጭፍን ጥላቻ የሚያንጸባርቁና በማን አለብኝነት ከሕግ አግባብ ውጭ የሆኑ የሃይማኖት መሪዎችና የሲኖዶስ አባላት የሆኑትን እነ አቡኑን የዚህ ጉባኤ አባል ኾነው ማየት ብርቃችን አይደለም:: በየፍርድ ቤቱ ፍትሕ ፈልገው የሚመላለሱት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ገንዘብና ዘመድ የሌላቸው ካህናት ከሌላው የተለየ በደል ሰርተውም አይደለም፤ በየሰብአዊ መብት ድርጅቶች የሚመላለሱበት ምክንያታቸው የፓትርያርኩን አስተዳደር ጠልተውም አልነበረም፤ እንደ ሃይማኖታቸውም የጳጳሳቱን አባትነትና ቡራኬ ሳይፈልጉት ቀርተው አይደለም:: ነገር ግን ከጎሳና ከጥቅማ ጥቅም በጸዳ መልኩ ፍትሕ የሚሰጣቸው አባት ወይም የበላይ ሲኖዶሳዊ አካል ስላጡ ብቻ ነው::

ይኸውም ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ኾነ በእግዚአብሔር ጉባኤ ውስጥ ተሰብስበው በዋጋ በሚሠሩ በሃይማኖት መሪዎቻችን ምክንያት የምዕመናን መጠጊያ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በኑፋቄ በሙስና እና በዘረኝነት እንደ እርሻ መታረሷን በእየሩሳሌም አምሳል የምትታወቀው የእግዚአብሔር ሀገር ኢትዮጵያም የድንጋይ ክምር ልትሆን እንደምትችል በትንቢተ ሚክያስ ተጽፏል:: ይህም የትንቢት ፍጻሜ እየሆነ ያለው እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፤ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል የሚለውን የሐዋርያትን የጉባኤ ቃል ለይምሰል እየጠቀሱ ነገር ግን ማንነታቸውን ለዋጋ የሰጡ በጉቦ የሚፈርዱ በዋጋ የሚያስተምሩ የሃይማኖት አባቶችን መመልከታችን የትንቢቱ ፍጻሜ ላይ መድረሳችንን ያረጋግጣል::

ምንግዜም ጸላኤ ሠናይ ውክልናውን የሚያሳየው ገንዘብ በሚወዱ ሰዎች ነው:: ገንዘብን መውደድ ደግሞ የጥፋት ሁሉ መሠረት ነው:: ዛሬ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር የጥፋት መሠረት ሆኖ የሚያተራምሰው የገንዘብ መውደድ ነው፤ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተሰየሙ ሰዎች የአስተዳደር ማጠንጠኛቸው የገንዘቡ መጠን እስከሆነ ድረስ ደግሞ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ ማኅበረ ምዕመናንን ለመበታተን አባቶች በጨረታው የሚገደዱ ኾነው አላገኘናቸውም:: እንደ ፍትሐ ነገሥት ገለጻ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የሚያመለክተው የምዕመናንን ኅብረት እስከሆነ ድረስ ጳጳሱ የቤተ ክርስቲያኑን ትምህርትና አስተዳደሩን እንዳያጣ በተሾመባቸው ምእመናን ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ፍትሐ ነገሥት ያስጠነቅቃል:: የፍትሕ መንፈሳዊ ሥርዐት ይህ በሆነበት ሁኔታ ጳጳሳት ግን የቤተ ክርስቲያን መገለጫ ከሆኑ ከማኅበረ ምእመናኑ ይልቅ በጣት የሚቆጠሩ ነገረ ሠሪዎችን የመረጡበት ምክንያት በፍትሐ ነገሥቱ ለተዘረዘሩት ለገንዘብ መውደድ ሐሜት እየዳረጋቸው ይገኛል::

በአዲስ አድማስ ጋዜጣ የዜና ሽፋን ሆኖ እንዳነበብነው “የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ለሰራተኛ ቅጥር 100 ሺሕ ብር ጉቦ መቀበሉ ታወቀ” ሲባል አባ ሆይ ሰውየውን በአንድ ደብዳቤ ያሰናብቱታል ወይም አግደው ጉዳዩን ያጣሩታል ብለን ገምተን ነበር፤ ሰውየው ጎይትኦም እንጂ ዘሪሁን ባለመሆኑ ግምታችን ሳይሳካ ቀርቷል፤ ሥራ አስኪያጁ የተዘገበበትን ጥፋት የፈጸመው ግለሰብ የእነ እገሌ ወይም የእነ እንትና ብሔር ቢሆን ኖሮ እንኳን ታውቆበት ዜና ሆኖ በተዘገበ ጉዳይ ቀርቶ በፎርጅድ ጉዳይ ከሥራህም ከደመወዝህም ትሰናበታለህ፤ ይህ ከማንነትህ ጋር ተያይዞ የሚመጣብህ እዳ ነው፤ እንደ ሥራ አስኪያጁ ዓይነት ስምና ማንነት ሲኖርህ ግን በአባ ሆይ ችሎት ዘንድ ያለመከሰስ ፀጋ እንዳለህ ያመላክታል:: እርሳቸውም ስላንተ ይከራከራሉ መብትህንም ያስከብራሉ::

ሐሜት እንዳይመስልብኝ በእኔ የደረሰውን እንደማሳያ ላቅርብ:: አባ ሆይ ባላወቁት ጉዳይ በ2008ዓ.ም ከሥራዬ እንድሰናበት ሸኚ ደብዳቤ ጽፈው ስለነበር በነበረኝ የሥራ ክርክር ባላጋራዎቼም የፓትርያርኩ ደብዳቤ አልታየልንም ብለው ይግባኝ ስለጠየቁ፤ አባታችን ስማቸው በፍርድ ቤት በከንቱ እንዳይነሳ በማሰቤ በብዙ ደጅ ጥናት አናግሬአቸው አውቃለሁ፤ እርሳቸው ግን ስለ ስማቸውም ስለመንበረ ክብራቸውም አልተጨነቁም፤ ከዚህም የተነሣ በምታሸንፍበት መንገድ ሄደህ ልታሸንፍ ትችላለህ ብለው አሰናበቱኝ:: ፍትሐ ነገሥቱ እንደሚለው ፓትርያርኩ በራሱ ፍርድ ቤት ያስወስን የሚለው አንቀጽ የቤት ልጆችን የሚመለከት እንጂ እንደእኔ አይነቱን በእርሳቸው ዘንድ መጻተኛ የሆንኩትን የማይመለከት መሆኑ የገባኝ ያኔ በተለይ አሁን ነው፤ አሁንም እንደ እንጀራ ልጆች የሚቆጠሩ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በቤተክርስቲያን ሥርዐት ፍትሕ የሚሰጣቸው አባት፤ የበላይ አካል የሆነ ይግባኝ ሰሚ ሲያጡ ጉዳያቸው በዓለማዊ ፍርድ ቤት እየተያዘ እስከ ሰበር ፍርድ ቤቶች ድረስ መዝለቃቸውና መብታቸውን ማስከበራቸው አይቀሬ ነው::

በዓለማዊ ፍርድ ቤትና ገዢዎች ዘንድ የአብያተ ክርስቲያናት ጉዳይ እንዲያዝ ማድረግ ማለት ከጳጳሳቱ ጉባኤ ከቅዱስ ሲኖዶስ ልዕልና ይጠበቃልን? ወይስ ብፁዕ ቅዱስ ከሚባል መንበር ወይም መንፈሳዊ ልዕልና ላይ አለ የሚባል የሃይማኖት መሪም እንዲህ ማድረግ ይገባዋልን? የቤተ ክርስቲያን መገለጫ የሆኑት ማኅበረ ምዕመናን መብታቸውን የሚጠይቁት በመንፈሳዊው ልዕልና መንገድ እንዲመለስላቸው በአክብሮት እንጂ በአለማዊ ፍርድ ቤቶች ፍትሕ እንደሚያገኙ እነሱም ቢሆን ሕገ መንግስታዊ መብታቸው መሆኑን መንገዱ ጠፍቷቸው አይደለም፤ ከዚያ ይልቅ ግን ብፁዕ ቅዱስ የሚለው አገላለጽ ለሲኖዶሳዊ መንፈሳዊነት ልዕልናና ለተቋማዊነቱ የተሰጠ በመሆኑንም ቤተ ክርስቲያን ስለ ሁሉም ነገር የፍትሕ ሥርዐት አላት ብለው ስለሚያምኑ ነው::

የሲኖዶሳዊ ሉዓላዊ አሠራር እየቀረ የአብያተ ክርስቲያናትን ጉዳይ ወደ አለማዊ አገዛዝ ፍርድ ቤቶች መምራት ማለት የሃይማኖት

መሪውን ተቋማዊነት አውርዶ ወደ ግለሰባዊነት ማምጣት ማለት መኾኑን የገባን ስንቶቻችን ነን ? በዚህ መንገድ የሃይማኖት መሪዎችም በአለማዊ አገዛዝ ፍርድ ቤት ከስሰን ማስቀጣት እንደምንችል የምናውቅ ስንቶቻችን ነን? መልካም !!! ይህም ቅዱስ ሲኖዶስ ለግፉዓን ፍትሕ አለመስጠቱ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ላይ እየመጣ ያለውን ተቋማዊ ክስረት ማሳያ መሆኑን ልንረዳው ይገባል!! እናም ታላቁ መጽሐፍ በመላእክት ላይ እንኳን የመፍረድ ስልጣን አላችሁ ያለው ከቶ ለማን ነው? ለጳጳሳት፤ ለካህናት ፤ ለፓትርያርኩ አይደለምን? በዚህ ዓለም ጉዳይ በሥርዐታችሁ በአግባቡ መፍረድ ካልቻላችሁ ከዓለማውያን መሪዎች በምን ልትለዩ ትችላላችሁ? ለምእመናንን ጥያቄ መፍትሔ እንድታበጁ፣ መናፍቃንን ለይታችሁ እንድታወግዙ ሽማግሌሊሆንየሚችልአንድአስተዋ ይሰውበእናንተዘንድሊኖር ይገባል::

እንደ መንፈሳዊ መሪነታችሁ በሃይማኖት ጉዳይ የሚተራመሰውን መንፈሳዊ ኮሌጅ ማጥራት ሲገባችሁ ዝምታን መምረጣችሁ ለምን ይኾን? አሁንም ለአብነት ያህል በመንፈሳዊ ኮሌጆቻችን ከገቡ መምህራን መካከል የአንዱን ቀሳጢ መምህር መጽሐፍ ልጥቀስ::ይህ ሰው በ2010 ዓ/ም መልሕቅ ክፍል ሁለት (አሌትያ) በሚል መጽሐፉ በገጽ 188 ላይክርስቶስን አማላጅ ነው ለማለት ሮሜ 8፤ 34 ላይ ያለውን የሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምይፈርዳል የሚለውን ንባብ ሲተች "… ከአተረጓጎም ስልት የራቀ ነው በማለትና ይማልዳል የሚለውን ቁልፍ ሥነ መለኮታዊ ቃል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መተርጉማን ይፈርዳል ብለው መቀየር የለባቸውም፤ ተገቢም አይደለም…" በማለት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከ2000 ዓመታት በኋላ ቃሉን ሆን ብላ የቀየረች አድርጎ መጻፉና እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስን አማላጅ ነው ማለቱ የሚያስወግዘው አይደለምን? እንደዚህ ዓይነት የሀሰት ትምህርት የሚያስተምር አስተማሪን በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መቀጠሩን እያወቃችሁ ዝም ማለታችሁ ለምን ይመስላችኋል ? መጽሐፉን አላነበብነውም፣ ስለጉዳዩም አናውቅም እንዳትሉ ብቻ!!! እናንተማ!!! "ስማችሁ የለም" የሚለውን የወንድማችንን መጽሐፍ እኛን ለመንካት ነው ብላችሁ ለግል ክብራችሁ ተጨንቃችሁ እንዳቂማችሁበትና እንደተፈራረማችሁበት ይታወቃል ፤ በአንፃሩ ግን ለጌታ ክብር ግድ ሳይሰጣችሁ የኮሌጁን መምህር መጽሐፈ ኑፋቄ ለማውገዝ ምነው ዝም አላችሁ?!

አባቶቼ !!! ይህም አካሄዳችሁ ምን ያህል ከሲኖዶሳዊነታችሁ ይልቅ ግለሰባዊነታችሁ ላይ ያተኮረ መሆኑን ያንጸባርቃል :: ስለ ዝናና ክብር የምትጨነቁ ከሆነ ከዓለማውያን በምን ተለያችሁ? በዓለማዊ ባለሥልጣናትና በአባቶች ሥልጣን መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፤ የአባቶች ሥልጣን ባለቤቱና ሰጪው ነሺውም መንፈስ ቅዱስ ነው:: የዓለማዊ ባለሥልጣን ግን በምድራዊ ሥርዐት በፉክክር የሚመጣ ነው::በዓለማዊ ተቋማት ያለው ፉክክር የደመወዝ፤ የሥልጣን፤ የምቾትና የይገባኛል ነው፤ ዓለማውያን ለሥልጣን ማግኘት የሚያደርጉት ፉክክር የሚያስነቅፋቸው አይደለም፤ ነገር ግን በመንፈሳዊ መሪዎች መካከል ያለው የሥልጣን ፉክክር ያስነቅፋል ፤ ወይም ስለተሾሙለት ሕዝብ ሳይሆን ባሕር ማዶ ተሻግሮ ገንዘብ ለመሰብሰብ የሚደረገው የምረጡኝ ዘመቻ አሁን ባለንበት በጳጳሳቱ ጉባኤ የተሰማ አይደለምን? ከዚህ የበለጠስ መንፈሳዊ ክስረት ምን አለ ? እነ አቡነ ደርበውስ የተፈጠሩት አሁን ባለንበት የጳጳሳት አስተዳደር አይደለምን? ደርበው ማለቴ የሀገሩን ውስጥ ሰርተው ሳይጨርሱ ለበጀቱና ማለትም ሁለት ሦስት ደመወዝ ለማግኘት ሲሉ ብቻ በፍቅረ ሲመት ተጠምደው ቃል ኪዳን የተቀበሉበትን፤ ሀገረ ስብከትና ሕዝብ እየተዉ ሌላ ሀገረ ስብከት የሚደርቡ፤ የእገሌ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊ፤ የእገሌ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ፤ የእገሌ ተቋም ቦርድ ሰብሳቢ፤ የእገሌ ቤተ ክርስቲያን አሳራጊ የሚባሉ ደራቢና ተደራራቢ ጳጳሳትን ነው:: የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በበጀት እጥረት ሰበብ አንድ ሥራ አጥተው እየተራቡ ሁለት ሦስት ደመወዝ የሚያገኙ፤ የቤት ኪራይ የሌለባቸው፣ የኑሮ ውድነት የማያስጨንቃቸው፣ ሁሉን ትተው ጌታቸውን የተከተሉ ጳጳሳት ሁለት ሦስት ደመወዝ መውሰዳቸው የጽድቅ ነው ትላላችሁ?

ሲኖዶሱ ጣልቃ እንዳይገባብኝ እያሉ የሀገረ ስብከቱ ጳጳሳት ሁሉ የምዕመናን አቤቱታ እንዳይሰማ የሚያደርጉበት ዘመን አሁን አይደለምን ? ይህ የአባ እገሌ ልዩ ሀገረ ስብከት ነው ሲኖዶሱ አይመለከተውም እየተባለ ሀገረ ስብከቶች ከሲኖዶስ አሠራር ውጭ ሆነው በጳጳሳቱ ይሁንታ ብቻ የሚተዳደሩበት የፍትሐ ነገሥት አንቀጽ አለን? ሕገ ቤተ ክርስቲያኑስ ቢሆን ከመደበኛው ከፍትሐ ነገሥቱ የህግ ትርጉም ጋር ሊጋጭ ይገባዋልን ? ሕገ ቤተ ክርስቲያኑ ሊሻሻል የሚችል ሲሆን ፍትሐ ነገሥቱ ግን ቀዋሚ ሕግ አይደለምን ? እውነታው ይህ ከሆነ



አባቶቼ ሲኖዶሳችሁ በሲኖዶሳዊ ጉባኤ ፍትሕ የተጓደለበትን ሁኔታ ሁሉ እየመረመረ ፍትሕ የምትሰጡበት ቅዱስ ጉባኤ መሆን ይገባዋል ::

ከዓመት እስከ ዓመት ያለው ቋሚ ሲኖዶስ መርምሮ ያላየውን ጉዳይ ምእመናን ለምልዐተ ጉባኤ አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ ‹‹አይ ይሄንን በቋሚ ሲኖዶስ እናየዋለን›› እየተባለ ከአመት እስከ አመት የሚንከባለሉ ችግሮችን ማየታችን ሲኖዶሱ ፍትሕን ለመስጠት ያለውን ልዕልና በግለሰቦች ፍላጎት ስር እንዳዋለው መረዳት እንችላለን :: ወይም የአብያተ ክርስቲያናትን ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት እንዲያመራ ማድረጉ ነገ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ የተስተዋለ አይመስልም፤ ቤተ ክርስቲያን በዓለማዊ አገዛዝ ፍርድ ቤት መዳኘት ስትጀምር ጅብ በቀደደው ውሻ ይገባል እንደሚባለው ማኅበረ ምእመናን እየተፈራረሙ በዓለማዊ አገዛዝ ፍርድ ቤት እያስወሰኑ በቦርድ የሚመራ ቤተ ክርስቲያን የሚያቋቁሙበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም:: ይህ በሆነ ጊዜ እገሌን ልሹምብህ እገሌን ልደርብብህ ማለት ይቀራል:: ያን ጊዜ የሚጮኸው ጩኸት የማይጠቅም ጩኸት ይኾናል፤

አባቶቼ !!! መንፈሳዊ የኾነ የሃይማኖት መሪ መገለጫው ትሕትናና ጥበብ እንጂ አምባገነንነትና አልሸነፍ ባይነት ሊሆን አይገባውም::

በኣለማዊ ባለሥልጣናትና በመንፈሳዊ መሪዎች መካከል ያለው ልዩነት የቅድስና ሊሆን ይገባል እንጂ የአልባሳት ልዩነት ብቻ ሊሆን ባልተገባው ነበር፤ ዓለማዊው ባለ ሥልጣን በቪኤት የሚሄድ ከሆነ መንፈሳዊው የሃይማኖት መሪ ደመና ጠቅሶ እንደሐዋርያት መንቀሳቀስ ነበረበት፤ ዓለማዊው መሪ በሱፍ በከረባት ሲያሸበርቅ፤ መንፈሳዊ የሃይማኖት መሪዎቻችን ደግሞ ባሸበረቁበት ልብሳቸው ድውያንን በፈወሱ ነበር፤ ይህንንም በዘመናችን አላየንም:: በዘመናችን ያየነው እነ አቡኑ አለባበሳቸውን የመደብ ልዩነት ሲያደርጉት እንጂ ልብሳቸው የቅድስና መለያ ሆኖ እንደእነ ጳውሎስ ሕሙማንን ሲፈውሱበት፤ እንደ እነ ኤልሳዕ ባሕር ሲከፍሉበት አልተመለከትንም::

አባቶቼ ነገሩ እንዲህ ከሆነ ከዓለማዊ ባለ ሥልጣናት በምን ተለያችሁ? በቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ችግሮች ተወያይታችሁ ደብዳቤ ከመለዋወጥ ባለፈ ውሳኔ የማትሰጡ ከሆነ እናንተ እነማን ናችሁ? አንዳንዶቻችሁ ፓትርያርክ መሆን ሳይቻላችሁ ሲቀር ለፓትርያርኩ እንደራሴ ልንሾምላቸው ይገባል የምትሉ ለሥልጣን የምትፎካከሩ እናንተ እነማን ናችሁ? ፓትርያርኩስ ቢሆኑ ከእናንተ እንደ አንዱ አይደሉምን? ሁላችሁም እንደራሴ ያስፈልጋችኋል!!!

አባቶቼጳጳሳት የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የማያሳስባችሁ ከሆነና ከማኅበረ ምዕመናን ጋር የምትገናኙበት መንገድ እየተቋረጠ ከሄደ ከዚህ በኋላ እርስ በራሳችሁ የምትመራረጡበት የእስከዛሬው አካሄድንበማስቀረት ማኅበረ ምዕመናኑ ያመኑበት፤ በዓይናቸው የሚያውቁት፤ በእጃቸው የዳሰሱት በትምህርቱ የተማረኩበት፤ የሕዝብ ይሁንታና ተመጣጣኝ የሕዝብ ውክልና የተሰጣቸው ሊቃውንትና ምሁራን አባቶች ተመልምለው የሚሳተፉበት ሕዝባዊ ሲኖዶስ ሊቋቋም ይገባል :: አዎ እደግመዋለሁ "የተቀደሰው" ጉባኤያችሁ ደስ አያሰኝምና ስለ ቤተክርስቲያን፣ ስለ ሀገር አንድነት ሲባል ሕዝባዊ ሲኖዶስ ሊቋቋም ይገባል!!! ይቆየን……….

"…ኩሉ አመክሩ ወዘሰናየ አጽንዑ…"

ገለቶማ !!!

ይቀጥላል…

# “አሸባሪ አላየሁም፤ ወደ ሽብር የሚገፉ መከራዎች ግን ብዙ ናቸው”

## ዘላለም ወርቅአገኘሁ

*የኢህአዴግ መንግሥት በዜጎች ላይ የሚፈፅመው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰትና የዴሞክራሲ ዕጦት ገፍቷቸው ወደ ሠላማዊ የፖለቲካ ትግል ከገቡ ወጣት አክቲቪስቶች መሐል አንዱ ነው፤ ዘላለም ወርቅአገኘሁ::*

*ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪውን የያዘው ይህ ወጣት የሁለተኛ ዲግሪውን በፖሊሲ ሣይንስ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እየሠራ በነበረበት 2006 ዓ.ም መጨረሻ ዓመት የትምህርት ፕሮግራሙ ላይ የመመረቂያ ጽሁፉን እያዘጋጀ ነበር ለእሥር የተዳረገው::*

*በአገሪቱ ከፍተኛ የፖለቲካ ሰዎች በተካተቱበት መዝገብ ውስጥ ክሥ የተመሠረተበት ዘላለም ወርቅአገኘሁ፤ አምሥት ዓመት ከአራት ወር እሥር ተፈርዶበት የእሥር ጊዜውን አጠናቆ ከወጣ ጥቂት ወራት ተቆጥረዋል::*

*ለመሆኑ ዘላለም ማነው? የታሠረበት ምክንያትና ያሣለፋቸው የትግል ጊዜያቶችስ ምን ዓይነት ገፅታ ነበራቸው? ለሚሉ እና ሌሎች ጥያቄዎች በቂ ምላሽ ይሆን ዘንድ የግዮን ባልደረባ ወጣቱን ፖለቲከኛ እንዲህ ባለ መልኩ አነጋግሮታል::*

---

**ግዮን፦ ከመታሰርህ በፊት የነበረው የፖለቲካ ሕይወትህ ምን ይመስላል?**


ዘላለም፦ ለእሥር ከመዳረጌ በፊት ይህን ያህል የጎላ እንቅሥቃሴ ነበረኝ ማለት አልችልም:: በ1997 ዓ.ም በነበረው የምርጫ ሂደት በፖለቲካ ውስጥ ያልተሳተፈ አልነበረም፤ እኔም ያኔ በካምፓስ ሕይወት እያለሁ ጓደኞቼ ጋ በመሆን ለቅንጅት ድጋፍ ሰጥተናል::

ከ2003 ዓ.ም በኋላ ግን የአገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ በንቃት ከመከታተል ወደ ማጋለጥ ተሸጋገርኩ :: የነበሩኝን መረጃዎች ለአንዳንድ የሚዲያ አካላት በማቀበል፣ አርቲክሎችን (ጽሑፎችን) በማደራጀት፣ በማዘጋጀት እንቅስቃሴ ውስጥ እስክያዝ ድረስ ቆይቻለሁ:: የሰብዓዊ መብት ጥሠት ሲካሄድ ወይም የሆነ ቦታ ላይ የተደበቀ ነገር ሲኖር ያንን የማጋለጥና ህዝቡ መረጃ እንዲያገኝ የማድረግ ሥራ ነው ሳከናውን የቆየሁት::

ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ሥራዎች የምሥራው “ደብረሃን” በሚባል ዌብሳይት ላይ ነበር:: በዚህ መንገድ ውጭ ከሚገኙ ዌብሳይቶች ጋር ፍሪላንሰር ሆኜ ነው መረጃዎች ሳቀብል የቆየሁት:: በኋላ ለእሥር ምክንያት የሆነኝም ይህ ሥራዬ ነው:: የሚገርመው ነገር ያን ያህል ጊዜ ስሰራ አብዛኛዎቹን ሥራዎች ራሴን አጋልጬ “ዘላለም” በሚል ሥምና ፎቶዬ አልነበረም:: በብዛት የፃፍኳቸው ጽሑፎች በብዕር ሥም የተፃፉ ሥራዎች ናቸው::

**ግዮን፦ ታዲያ በብዕር ሥም እየተጠቀምክ አንተ መሆንህን እንዴት ደረሱበት?**

ዘላለም፦ ተደብቆ መሥራቱ ወይም የብዕር ሥም መጠቀሙ ብዙ መሥራት ያስችላል የሚል ዕምነት ሥለነበረኝ ነው ይሄንን መንገድ የተጠቀምኩበት:: ይፋ ሆነህ በግልፅ መሥራቱ ወዲያው ስለሚያሲዝህና ያሰብከውን ነገር ሳታደርግ ስለምትቆም፤ ትንሽ ለመሠንበትም ቢሆን በብዕር ሥም መጠቀሙን ነው የመረጥኩት:: ለተወሠኑ ዓመታትም ቢሆን ይሄ ምርጫዬ ጠቅሞኛል:: ምናልባት እኔ ይፋ ወጣሁ ብዬ የማምንባቸው ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ሠማያዊና አንድነት ፓርቲ በጠሯቸው ሠልፎች ላይ ብቻ ነው:: ምናልባት እነዛ ሠልፎች እኔ



ላይ ክትትል እንዲደረግ መነሻ ይሁኑ አላውቅም ወይም ከተያዝኩ በኋላ ፍ/ቤት ይቀርቡ የነበሩ አካዳሚከ ጽሑፎች ላይ ምርመራ ሲያደርጉ ይድረሱበት ብቻ በማላውቀው መንገድ ሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም በፖሊሥ ቁጥጥር ሥር ዋልኩኝ::

**ግዮን፦ የት ቦታና በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር የያዙህ?**

ዘላለም፦ በዘመቻ መልኩ ነው የተያዝነው:: ከአንድ ቀን በፊት በተሠጠ መግለጫ እኔ፣ ሀብታሙ አያሌው፣ የሠማያዊ ፓርቲ አመራሮች እነ የሺዋስ አሠፋ፤ የአረና ፓርቲ አመራር አብርሃ ደስታ በተመሳሳይ ሠዓት ጠዋት ላይ ነው ሁላችንም የተያዝነው:: ባህሩ ደጉና ዮናታን ወልዴ የሚባሉ ሁለት ጓደኞቼ የሚዲያ ሥልጠና ልንወስድ ተነጋግረን በጊዜው ከእኔ ጋ ስለነበሩ ምንም በማያውቁት ነገር በዘመቻ መልክ አብረውን ታሥረዋል:: የያዙኝ ከቤቴ ሲሆን ፈፅሞ ያልጠበቅኩት ትልቅ ኃይል ነው የመጣው:: እኔ አንድ ሲቪል ሰው ነኝ ግን እኔን ለመውሠድ አንድ መኪና ሙሉ የካሜራ ክሩው (አባላት)፣ በሌሎች መኪና የታጠቁ ወታደሮች ተሠብስበው ስታይ ትደነግጣለህ::

በዚህ አስደንጋጭ ሁኔታ ሲወስዱኝ እናቴ ስላልነበረችና እንድታየኝም ስላልፈለኩ “ልትወስዱኝ አይደለ የመጣችሁት ይኸው ይዛችሁኝ ሂዱ” ስላቸው “አይ ቤትህን መፈተሽ አለብን” አሉ፤ ፍተሻው ተጀመረ፤ በዛ መሃል እናቴ ተመልሳ መጣች:: እንዴት እንደደነገጠች ልነግርህ አልችልም:: አራት ሠዓት የፈጀ ጠንካራ ፍተሻ አደረጉ፤ ግን ምንም አላገኙም:: በኋላ ወረቀት፣ ሞባይል፣ ሁለት ላፕቶፖችና አንድ ዲሥክ ቶፕ ኮምፒዮተር ይዘው ሄዱ:: የሚገርምህ ከታሠርኩ በኋላ እነሱ ከፈለጉት ጋር የሚገናኝ አንድም ነገር ባለማግኘታቸው መውሰድ ትችላለህ በሚል መልሠውልኛል::

በኋላ በአገራዊ ጉዳዮች ዙሪይ ከአንዳንድ ግለሠቦች ጋር የተወያየሁባቸውና የፃፍኳቸው ጽሑፍች ከኢሜሌና ፌሥቡኬ ወጥተው 250 ገፅ የሚሆን ዝርዝር የደህንነት ማኅተም ተመቶባቸው ማስረጃ ቀርበውብኛል:: ያው እንደምታውቀው የፀረ ሽብር ሕጉ ደህንነቱ የሐሠት መረጃዎችን እየፈበረኩ እንዲያቀርቡ ዕድል የሚሠጥ ነው::

**ግዮን፦ ተይዘህ ማዕከላዊ ከገባህ በኋላ የገጠመህ ነገር ምንድነው? በተለይ ከሰብዓዊ መብት ጥሠት አኳያ?**

ዘላለም፦ ከቤቴ ስወሠድ እንደምታሠር ስለማውቅ ጫማዬን አውልቄ በነጠላ ጫማ ነው የወጣሁት፤ ቀበቶዬንም ቤት ነው ያስቀመጥኩት:: ማዕከላዊ እንደ ደረስኩ ሳይቤሪያ የሚባል ቦታ አምስት ቁጥር ውሥጥ ነው ያስገቡኝ:: እዛ በብዛት በኦሮሚያ ማሥተር ፕላን ኬዝ የታሠሩ ልጆች ተቀበሉኝ:: አብዛኛዎቹ ኦሮሞዎች ናቸው:: እውነትም እሥር ቤት የኦሮሞ ልጆች መታጎሪያ ነው እንዴ? የሚለው ነገር ነው ወዲያው የገባኝ::

በተያዝኩ በሦስተኛው ቀኔ ከነበርኩበት ክፍል አስወጡና ሳይቤሪያ 8 ቁጥር የሚባል ቦታ አሠሩኝ፤ ሁለት ቀን ምንም ሳይጠሩኝ ጨለማ ቤት አስቀመጡኝ:: ልክ ሐምሌ አምሥት ማታ ምርመራ ጀመሩ:: ከማዕከላዊ እስከ ወጣሁበት ነሐሴ 13 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ አርባ አንድ ቀን ሙሉ ማታ እየተወሠድኩ ሌሊቱን ሙሉ ምርመራ ይደረግብኛል:: አሁን አልፎ ስታወራው ነገሮች ይገርማሉ:: በ41 ቀን ውስጥ ሦስት ቀን ብቻ ነው የውጪውን ብርሃን ያየሁት:: ሌላውን ጊዜ በሙሉ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ስለማሳልፍ መምሸትና ቀን መሆኑን የምለየው ማታ ሊወሥዱኝ ሲመጡ ብቻ ነበር::

በማዕከላዊ የሚደርስብህን ነገር እንዲህ ነው እያልኩ በመግለፅ ሌላውን ወጣት ማስፈራራት አልፈልግም:: ፍርድ ቤትም ይሄን ነገር ተናግሬዋለሁ:: ስትያዝ የሚደርስብህን አሰቃቂ

ነገር በይፋ በመግለፅ ሌሎች የህብረተሠብ ክፍሎችን ከድርጊታቸው እንዲቆሙ ማስፈራሪያ ይሆናል የሚል አቋም ስላለኝ የተሠቃየሁትን ነገር መዘርዘሩ ተገቢ ነው ብዬ አላምንም:: ሥርዓቱን ‹‹ተው›› እያሉ ያሉ፣ እየተጋፈጡት ያሉ ብዙ ወጣቶች በዚህ ዘመን ተፈጥረዋል:: እኛን ለእነሱ እንደማስፈራሪያ እየተጠቀሙብን ነው ያሉት ብዬ አስባለሁ::

መግለፅ ካለብኝ፤ ማዕከላዊ የሰው ልጅ በዛ ዓይነት ሰቅጣጭ ሁኔታ ውስጥ መመርመር አይገባውም የሚያሥብል አሠቃቂና ዘግናኝ ነገር የሚፈፀምበት ቦታ ነው:: አንድ ዓይነት አስተሳሰብ አንድ አይነት ሥሜት ያላቸው፤ ሥርዓቱን እንደፈጣሪ የሚያመልኩ ሰዎች የተከማቹበት ሥፍራ ነው :: ምን ኀድሎብህ፤ ምንህ ተነክቶ ነው የምትፅፈው፣ የምትቃወመው? በማለት ነፍስህን ቢያወጡት ምንም የማይመስላቸው ሰዎች ናቸው በምርመራ ሂደት የሚያሰቃዩህ:: ግን ፈጣሪ ከአንተ ጋር ነውና ሁሉንም መከራ ለጊዜው ብትጎዳም ታልፈዋለህ::

**ግዮን፡- በእሥር ላይ ሆነህ ከተለያዩ ክልሎች ከመጡ ወጣቶች ጋ ለመገናኘት ችለሃልና አሁን ያለውን የወጣቶች እንቅስቃሴና ሚና እንዴት ታየዋለህ?**

ዘላለም፡- ማዕከላዊም ሆነ ቂሊንጦ አልያም ሌሎች እሥር ቤቶች ውስጥ የታዘብኩት አንድ ነገር ማንበብ ከማይችለው እስከ ሊቁ፤ እኛ ሰብዓዊ መብት ጥሠት፣ የዩኤን ቻርተር የምንለውና ሌሎች ነገሮች የማይገባቸው ግን እየደረሰ ያለው የአገርና የህዝብ ችግርን የተረዱ፣ ሥርዓቱ ፍፁም አምባገነን በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ መቀየር አለበት ብለው የሚያምኑና ያንን ዕውን ለማድረግ ሠላማዊ ትግል ያደረጉ፣ የሠዎች ያለ አግባብ መታሠርና መገደልን "ለምን" ብለው የጠየቁ፣ የጻፉ በርካታ ሰዎች በእሥር ቆይታዬ አግኝቻለሁ::

በተለይ ማዕከላዊ በነበርኩበት ጊዜ አሸባሪ አላየሁም፤ ግን ሰዎች እንዴት አሸባሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግን ተመልክቻለሁ:: መብታቸውን ስለጠየቁ ብቻ ታስረው፣ በሚደርስባቸው ግፍና መከራ ሳይወዱ በግድ ወደ እዚህ መንገድ እንዲገፉ እየተደረገ ነው:: በርካታ የሱማሌ ወጣቶች እናትና እህቶቻቸው ሲደፈሩ አይተዋል:: ከዛ አልፎ እነሱ እዚህ ታሥረው ለሰው ልጅ በሚከብድ ሁኔታ መከራና ስቃይን ሲቀበሉ ተመልክቻለሁ:: ታድያ እነዚህ ወጣቶች ሥርዓቱን ከመጥላት አልፈው ለነፃነታቸው ሲሉ ሌላ ነገር ቢወስኑ ጥፋቱ የማን ነው?፡

እሥር፣ ለአንዳንዶች በቂ የመሠልጠኛ ጊዜ ነው የሆናቸው:: ያቺን በተፈጥሮ ያገኙትን እምቢ ባይነት እንዴት መብታቸውን አስከብረውና የሌላውንም መብት በምን መልኩ መጠበቅ እንዳለባቸው ከተለያዩ ታሳሪ የህብረተሠብ ክፍሎች ተምረው ነው የሚወጡበት:: በአንፃሩ በሚደርስባቸው ሥቃይና መከራ የአሸባሪነት ፅንፍ ውስጥ ተገፍተው እንዲገቡ የተደረጉትን ደግሞ የማረጋጋትና የመመለስ ሥራ እንሠራ ነበር::

**ግዮን፡- በከፍተኛው ፍርድ ቤት ክሥ ሲመሠረትባችሁ ታላላቅ የፖለቲካ ሠዎች እያሉ የመዝገቡ ሥም "እነ ዘላለም ወርቅ አገኘሁ" ነበር የሚለው፤ እዚህ ላይ ምን ታሥቦ ይመሥልሃል?**

ዘላለም፡- ማዕከላዊ ሦስት ወር ከሃያ አራት ቀን ቆይተን በከፍተኛው ፍርድ ቤት ክሥ ተመሥርቶብን ወደ ቂሊንጦ ስንወርድ መዝገቡ በእኔ ሥም መሆኑ በጊዜው ሁለት ነገር ነው የተሠማኝ:: … ከበፊት ልማዳቸው የወሠዱት አንድ ነገር ያለ ይመሥለኛል:: በጣም ታዋቂ የሆኑ ሠዎችን የክሱን ፋይል በእነሱ ሥም መክፈት በህዝብ ዘንድ ጉዳዩን ቅቡልነት ከማግኘት ባሻገር ነገሩን ማራገብ ይሆናል፤ ስለዚህ በህዝቡ ዘንድ የማይታወቀውን ሰው ከፊት ማድረግ እንደ ብልጠት የታየ ይመስለኛል::

በሌላ መልኩ ግን ከተያዝኩበት ጊዜ አንሥቶ መዝገቡን አደራጅተው ክሥ እስከተመሠረተብኝ ድረስ ያለውን ነገር ስትመለከተው ደግሞ ለእኔ ትልቅ ግምት እንደነበራቸው ደግሞ በግልጽ ያሳይሃል:: ዞሮ ዞሮ በምንም መንገድ ቢያስቡት የእኛ መያዝ ከመጀመሪያው ጀምሮ የሚዲያ ሽፋን በበቂ ሁኔታ በማግኘቱ ህዝቡ ሁኔታውን በግልፅ አውቆታል:: ሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ተይዘን ግንቦት 2008 ዓ.ም ከአንድ ዓመት አሥር ወር በኃላ ነው ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ብሎ የቅጣት ውሳኔ ያስተላለፈብን::

**ግዮን፡- የፍርድ ሂደቱ ምን ያህል ጤናማና ህጋዊ ነበር፤ በአንተ ላይስ የተበየነብህ ቅጣት ምንድነው?**

ዘላለም፡- ኢህአዴግን ትክክል አይደለህም የሚሉ ሰዎች አሥራ አራትና አሥራ ሥድስት ዓመት ማሰር የሥርዓቱ መገለጫ ሆኗል:: በፍርድ ቤት ክርክራችን ወቅትም የሆነው ይኸው ነው:: ደህንነቶች የፈበረኳቸው ማሥረጃዎች እንደ በቂ ሁኔታ ታይተውብናል:: የእኛ ጠበቃ የነበረው ጠበቃ ተማም አባ ቡልጋ ነበር:: አቃቤ ህግ ምሥክሮችን አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ጠበቃችን ተማም አንድ ዓመት በየትኛውም ፍርድ ቤት ጥብቅና እንዳይሰራ ታገደ:: ምንም አማራጭ ስላልነበረ ከዛ በኋላ ያለውን የራሴን ክርክር እኔ ነኝ ያደረግኩት::

እኛ ሀገር ያለውን ህግ ልብ ብለህ ስታስተውለው ያስቅሃል:: ለዳኝነት የተቀመጠው ሰው ከምን አንፃር ነው ውሳኔ የሚሰጠው ብለህ ብትመረምረው የፍትሕ ሥርአቱ የውሸት እንደሆነ የእኛ መዝገብ ቁልጭ አድርጎ ያሳይሃል… እኛ አንድ ላይ የታሠርነውና የተከሰስነው አሥር ሰዎች ነን፤ ተከላከሉ ያሉን አምሥት ሰዎች ስንሆን ጥፋተኛ የተባልነው ደግሞ ሦስት ሰዎች ነን:: በዚህ ሂደት ውሥጥ የመጨረሻ ውሳኔ ሲወሥኑ "አንደኛ ተከሳሽ ዘላለም ወርቅ አገኘሁ በተለይ ፍርድ ቤቱን እንዲሁም አቃቤ ህግ ያቀረበውን ማሥረጃ የሞገተ ቢሆንም" ይላል:: መሞገት ትልቅ ነገር ነው:: አንድ ፐርሠንት የሚያጠራጥር ነገር ከተገኘ ክሱ ውድቅ ነው የሚሆነው፤ የህጉን አግባብ እያወቁ ጥፋተኛ ብለው የአምሥት ዓመት ከአራት ወር እሥር ፈረዱብኝ::

በመጀመሪያ ደረጃ የቅጣት ውሳኔው መሆን የሚገባው አልነበረም:: ከዛ በተጨማሪ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ግልፅ የሆነ የመደመር ስህተት ስለነበረው "እኔ ላይ ሊፈረድብኝ የሚገባው ሦስት ዓመት ከስድሥት ወር ነው" በሚል ከድምር ስህተቱ አኳይ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብልም በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ‹‹የታችኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል›› የሚል ወረቀት በማግሥቱ በቤተሠብ በኩል ተላከልኝ፤ ያንን ይዤ ሰበር ሠሚ ፍርድ ቤት ሄድኩኝ:: በቀጠሮ ቀን እናቴ ቀረበች:: ሠበር ሠሚው "ዘላለም እንደ ቅሬታ ካቀረባቸው አራት ምክንያቶች ውሥጥ አንደኛውን ተቀብለን ሊፈረድበት የሚገባው አምሥት ዓመት ከአራት ወር ሳይሆን አራት ዓመት ከአራት ወር ነው" የሚል ውሳኔ አሳለፈ… እኔም አንድ ዓመት መቀነሱ ጥሩ ነው ብዬ ተቀብዬ ባለበት ሁኔታ፤ እናቴ የውሳኔውን ግልባጭ ለመቀበል በማግስቱ ስትሄድ የመጀመሪያው ውሳኔ የፀናበትን ወረቀት ይሰጧታል:: እሷም ‹‹እኔ ችሎት ላይ ነበርኩ፤ አንድ ዓመት ተቀንሶለታል:: ውሳኔው ይሄ አይደለም›› ስትል "አይ እኔ ስጪው የተባልኩት ይሄንን ነው" ብለው መለሷት::

እንደዚህ አይነት ፊት ለፊት የወጣ ክህደትና ወንጀል ካለማ በቃ የፈለጉትን አምሥት ዓመት ታስሬ ልጨርሥላቸው ብዬ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጌ ተውኩት:: በቅርቡ ልፈታ ሥል ያቺ ወረቀት ውዝግብ ፈጥራ አገኟት:: "እንዴ ይሄ ልጅ'ኮ 2009 ዓ.ም. ነበር መፈታት የነበረበት" እያሉ ፋይል የሚያጣሩት ሰዎች እርስ በርስ ሲከራከሩ፤ መጨረሻ የሆነ ሰው መጣና ነገሩን ግልፅ አደረገላቸው መሠለኝ እነሱም ዝምታን መረጡ፡

**ግዮን፡- ቂሊንጦ፣ ቃሊቲ፣ ዝዋይ እንደመታሠርህ እዛ ያለውን የእሥረኞች አያያዝ፣ ሠብዓዊ መብትን በተመለከተ የታዘብካቸው ነገሮች ይኖራሉና እነሱን ብትገልፅልን?**

ዘላለም፡- እሥረኞችን በማንገላታትና በማሰቃየት በተለይም ከፖለቲካ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የታሠሩ እሥረኞች ላይ ከባድ በደል በማድረስ ለሥርአቱ መፈርጠም ትልቅ ሚና እየተጫወቱ ያሉት ቃሊቲ፣ ቂሊጦና ዝዋይ እሥር ቤቶች ናቸው:: ከአደረጃጀታቸው አንሥቶ ስትመለከት ከላይ ጀምሮ እታች ድረስ ያሉት ነባር ታጋዮች ናቸው:: ለነገሩ እሥር ቤቶቹ ማረሚያ ቤት ሊባሉ አይገባቸውም:: አንድን ሠው ለማረም በቂ ሥልጠና ልትሰጠው ይገባል፣ ልታሥተምረውና የሆነ ጊዜ ላይ ከእሥር ልትለቀው ይገባል:: ተምሯል፣ተለውጧል ብለህ ሥታምን መልቀቅ አለብህ::

እኛ ሀገር 20 ወይም 18 ዓመት የተፈረደበት ሰውዬ ሊታሠር የሚገባው 12 ዓመት ሊሆን ይችላል:: ግን ይሄ ሰውዬ በአራትና አምሥት ዓመት ውሥጥ ካሥተማርከው፣ ካሰለጠንከውና የሃሳብ ለውጥ ካመጣ በምንም ወንጀል ይታሠር ለምንድነው የማትለቀው? ይሄ ሲሥተም አልተዘረጋም፤ ታድያ በምን መልኩ እነዚህ ማረሚያ ቤቶች ይሆናሉ? በተለይ የፖለቲካ እስረኞችን ተገቢ ባልሆነ አያያዝ መያዝ ኖርማል ሥራችን ነው፣ መብታችን ነው ብለው የሚያምኑ አመራሮች ነው ያሉት::

በደረቅ ወንጀሎች ላይም በጣም ዘግናኝ የሆነ የዱላ ድብደባ ይፈፀምባቸዋል:: በርግጥ የሚያጠፉና ከባድ ወንጀል ከፈፀሙ ሰዎች ጋር ነው ታሥረን የነበርነው:: እነዚህ ሰዎች እዛም መጥተው ሊያጠፉ ይችላሉ:: ግን እነዛ ሰዎች ትሪት የሚደረጉበትን መንገድ ስታየው ማዕከላዊ መች ሥቃይ አለ ትላለህ:: የሚያሳዝን ነገር ነው የሚፈፅምባቸው::

በማዕከለዊ ወይም ባህር ዳር በምርመራ ወቅት ብልቱ ላይ ሃይላንድ የተንጠለጠለበት ሰውዬ ቂሊንጦ ሲመጣ ብልቱ ቆሥሎ ህክምና ተከልክሎ ይሠቃያል፤ አሁንም ልክ እንደ60ዎቹ ዓ.ም. ትግል ላይ ነን ብለው የሚያስቡ አመራሮችና ወታደሮች ያሉባቸው ቦታዎች ናቸው:: ሲያዩህ ራሱ በጥላቻ ነው:: "የእኛን ሥርዓት ሊጥል፣ ሊያፈርስ የመጣ ነው" ነው የሚሉህ::

በጣም አስገራሚው ነገር ደግሞ የግለሰብ እሥረኞች አሉ:: የሱማሌው ክልል ፕሬዘዳንት የአቶ አብዲ አሊ እሥረኞች ጉዳይ:: ስለተቃወሙ ታሥረው መንገድ ላይ፤ መኪና ውሥጥ ነው የፍርድ ውሳኔያቸው የተሠጣቸው:: በጣም ይገርማል:: ሰውዬው ለራሱ ፓርቲ አባሎችና አብረውት ሲሠሩ ለነበሩ አመራሮችም አልተኛም:: የተቃወሙትን በሙሉ ነው በሌላ ክሥ ሃሰተኛ ማሥረጃ እያስፈበረከ ጠራርጎ ያስገባቸው:: ዝዋይ የእሱ የግል እሥረኞች ሆነው የታሠሩ በርካታ ሶማሌዎችን ታገኛለህ:: ስለዚህ የኢትዮጵያ እሥር ቤቶች ገዥውን ፓርቲ "ለምን" ብለው የሚጠይቁ ግለሠቦች በግፍ የሚታሠሩበት ብቻ ሳይሆን፤ የሚሠቃዩበት የማፊኛ ቦታዎችም ናቸው::

**ግዮን፡- እናመሠግናለን::**

**የቤተክህነት...** *ከገጽ 19 የዞረ*

ፍቅር ሲኖራቸው ነው:: አሁን ያሉት ሰዎች ግን ፖለቲካና አፍቅሮተ ነዋይ ነው ቀፍድዶ የያዛቸው:: እነዚህ ሰዎች ከተጠያቂነትም ሆነ ከነፍስም ለመዳን ከፈለጉ ከዘረኝነት ማነቋቸው መላቀቅ አለባቸው::

**ግዮን፡- በቅርብ ወደ ገዳማችሁ (በአታችሁ) ልትመልሱ ነው፤ እዛ ደግሞ እናንተ እስር ላይ ሆናችሁ የህወሓት ሰው በገዳሙ ኃላፊነት መሾሙ ይነገራል:: ገዳም ስትደርሱ ከዚያ አኳያ ምን ዓይነት ነገር ይጠብቃችኋል? መነኮሳቱስ በምን መልኩ ነው የሚቀበሏችሁ?**

**አባ ገብረ ሥላሴ**፡- አሁን እዚህ ሆነን በስልክ እዛ ካሉት ጋር እንገናኛለን:: ገዳሙ አሁን ስላለበት ሁኔታ በቂ መረጃ እናገኛለን:: በተለይ ግድብ ይሠራበታል ተብሎ የሚታሰብበት ቦታ ጥንታዊ ደኖች እየተመነጠሩ ከሠል የማክሠል ሥራ እየሰሩበት ይገኛሉ:: ይሄንን አሁንም እየተቃወምን ነው::

ስለ አቀባበሉ፤ ዋልድባ ሠፊ ነው:: ዋልድባ አብረንታንት፤ ዋልድባ ዳልሻ፣ ዋልድባ ሰቋር ነው ያለው:: አብዛኛው መነኮሳት የእኛ ነው:: ከህወሓት ሰላዮችና አመራሮች ወጪ... እነሱ ከእኛ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አይኖራቸውም:: ድመትና አይጦች ነን፤ ምክንያቱም እነሱና እኛ አላማችን የተለያየ ነው:: መቼም ቢሆን እነሱ ይቀበሉናል ብለን አናስብም፤ መከልከል ግን አይችሉም::

ስለዚህ እኛ ወደ ትግራይ ክልል ወዳለው የገዳሙ "አብረንታት" አንሄድም:: እዛ መሄድ ለአደጋ መጋለጥ ነው:: ዝም ብዬ ልሙት ማለት ካልሆነ በስተቀር:: እነዛ መነኮሳት ወደ አሉበት በትግራይ ወደ ተከለለው ገዳም አንሄድም:: በሌሎች የገዳሙ ክልሎች ግን እንደ ልባችን መንቀሳቀስ እንችላለን:: አስፈላጊ ሆኖ ካገኘነው ወደ እነ አቶ ገዱ ጋ በመሄድ በጉዳዩ ላይ እናነጋግራቸዋለን::

አሁን ወደ ጎንደር ነው የምንሄደው:: የአዲስ አበባ ህዝብ ተቀብሎ እንዳስተናገደን ሁሉ የጎንደር ህዝብም ተቀብሎ ያስተናግደናል፤ ምክንያቱም ከአብራኩ የወጣን ነንና:: የአዲስ አበባ ህዝብ ዘር ቀለም፣ ሐይማኖት ሳይለይ መጥተው ጠይቀውናል፤ ስንፈታም በደስታ አስተናግደውናል:: ታዲያ ለዚህ ህዝብ አትሞትለትም? ይሄን ምስኪን ህዝብ ፊቱ ላይ ቆመህ ስለ መብቱ ልትናገርለት ይገባሃል:: ይሄ የኃይማኖት ቀናኢነት ነው::

ጎንደር ከገባን በኋላ ሰቋር ዋልድባ አለ፣ ዳንሻ ዋልድባ አለ፤ እነሱ ገዳሞቻችን ናቸው፤ የምንኖርባቸው የምንሞትላቸው ገዳማት:: አፈሩን እናገኛለን ብለን የምንጠብቀው ገዳም ስለሆነ ወደ እዛ እንሄዳለን:: ለእነዛ ሰዎች በቂ መልስ ስላለን ዝግጁ ነን ድፍረቱ ኖሯቸው ሊጠይቁን ከቻሉ::

**ግዮን፡- በመጨረሻ ለኢትዮጵያ ህዝብ የምታስተላላፉት መልዕክት ምንድን ነው?**

**አባ ገብረ ኢየሱስ**፡- እኛ ለኢትዮጵያና ህዝቧ የምንመኝላት የቀደመ ክብሯ፣ የቀደመው ልዕልናዋ እንዲመለስ፤ ህዝቦቿ በሰላም፣ በፍቅርና በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ ነው:: የተለያየ እምነት ውስጥ ያሉ ሰዎች በነፃነት እምነታቸውን እንዲያራምዱ እንሻለን:: ይሄ ምስኪን ህዝብ ያለ መለያየት በሠላምና በደስታ እንዲኖር እንመኝለታለን:: ማንም ቢመጣ አብልቶ አጠጥቶ አስተናግዶ፣ አኑሮ፣ ድሮ የሚሸኝ ደግ ህዝብ ነው:: ይሄን ህዝብ መንካት ፈጣሪን ማስቀየም ነው::

ህዝቡን ዘመን አመጣሽ ነገር ወዲያና ወዲህ ቢያላጋውም መንፈሳዊነቱን አልለቀቀም:: ይሄንን ህዝብ ተግተን ልናገለግለው ይገባናል:: ደም አፍሳሾች እጃቸውን እንዲያነሱ፣ ህወሓትም ከቤተ ክርስትያን ላይ እጁን እንዲያነሳልን፣ በቤተክርስትያን ያሉ ሰዎች አምልኮተ እግዚአብሄርን በቅድስናና በንፅህና እንዲያደርሱ ነው የምንመኘው የምንፀልየው::



ኢትዮጵያ ውስጥ እኔ በግሌ የኃይማኖት መንግሥት እንዲመሠረት አልፈልግም፤ ነገር ግን መንግስት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ላይ እጁን እንዲቀስርባት ደግሞ አልፈቅድላቸውም:: ምክንያቱም ይህች ቤተ ክርስትያን ለዚህች አገር ባለውለታ ናት:: ብራና ዳምጣ፣ ቀለም በጥብጣ፣ ፊደል ቀርፃ ለዓለም ያስተላለፈች፣ ድንበር ጠብቃ እስካሁን ድረስ አገሪቷን አስከብራ የምትኖር ቤተ ክርስትያን ናት:: በዚች ቤተ ክርስትያን ላይ ማንም ይንገስ ማንም እጁን እንዲቀስር አንፈቅድለትም:: ቤተ ክርስቲያናችንን አክብሮ ሊይዝ ይገባዋል:: ማንም ተመረጠ ማንም ነገሰ ይሄ ግዴታው ነው:: በቤተ ክርስቲያናችን ክብር፣ በሀገራችን ክብር ላይ ግን መቼውንም አንላቀቅም:: በአገራችን፣ በእምነታችን ላይ ህይወታችንን መስዋዕት እናደርጋለን::

በመጨረሻ መላው የኢትዮጵያ ህዝብን እግዚአብሄር ያክብርልን ነው የምለው:: ሌላው ዲያቆን ዘመድኩን በቀለ፤ ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራውን በጣም አመሰግኑልን፤ ከታሰርን ጀምሮ ብዙ መረጃዎችን ለህዝብ በማድረስ ትልቅ ሚና የተጫወቱ ናቸው::

**አባ ገብረ ሥላሴ**፡- ወደ ገዳማችን ልንሄድ በዝግጅት ላይ ነን:: ፈፅሞ አንቀርም:: እዛ ቦታ ላይ በህወሓት የተቀመጡት ሰዎች እኛን በሌላ ሊያዩን ይችላሉ፤ ግን ይሄ ጉዳያችን አይደለም:: እኛ ከታሰርን በኋላ ዋልድባን ለሁለት ከፍለውታል:: አበረንታትን ወደ ትግራይ፣ ዳንሻና ሰቋርን ወደ አማራ አድርገውታል፤ ለአሁን ማለት ነው:: ስለዚህ አሁን ለህይወታችን አስጊ የሆነበትን ቦታ ትተን በእነዚህኞቹ ገዳማት እንኖራለን:: ወደፊት ግን ገደማችን ስለሆነ መሄዳችን አይቀርም:: ሌሎች መነኮሳት በደስታ ነው የሚቀበሉን:: በገዳሙ ህግና ደንብ መሠረት ማንም ሰው ሲመጣ እግር አጥበው፣ አስተናግደው በረከት የሚቀበሉ መነኮሳት ናቸው ያሉት:: ስለዚህ እንኳን ለእኛ ለሌሎችም ገዳሙ ክፍት ነው::

የኢትዮጵያ ህዝብ በዘር በጎሳ እንዳይለያይ፣ ሁሉም የራሱን ኃይማኖት ጠብቆ በመያዝ የሌላውን ሳይነካ በፍቅርና በሠላም እንዲኖር እመኝለታለሁ:: እግዚአብሄር "ወደ ሁለት ነገሮች እጅህን ስደድ፣ እኔን ብታመልከኝ ህያው ትሆናለህ፣ ትድናለህ፤ ወደ እሳቱ እጅህን ብትሰድ ግን ትሞታለህ" ነው ያለው አዳምን:: ስለዚህ እግዘአብሄር የሰጠውን ነፃነት ሰው ሊነፍገው አይገባም:: ህዝባችን ታግሎልናል፣ ብዙ መስዋዕትነት ከፍሎልናል፤ ሁሌም እናመሰግነዋለን፤ በፀሎት እናስበዋለን:: ቤተ ክርስትያን ግን ቃለ እግዚአብሔር የሚነገርባት፣ ስብሐት እግዚአብሔር የሚደረስባት፣ የተማሩ አባቶቻችን የሚያገለግሉባት፤ ውዳሴ ማርያም የሚደገምባት ቦታ እንድትሆን ነው ምኞቴ፤ መልዕክቴም ይሄው ነው::

**ግዮን፡- ከልብ እናመሠግናለን::**



ብሌን ዮሴፍ

# መገናኛ ብዙኃን የገነቡት "ያልተገነባው የኢትዮጵያ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ"

የተለያዩ የሀገራችን የመገናኛ ብዙኃን የመዝናኛ ፕሮግራም አቅራቢዎች የሀገራችንን ሙዚቃዎች በሚጋብዙበት ወቅት ስለሙዚቃውና ሙዚቀኛው አስተያየቶችን ይሰጣሉ:: ደጋግመው ከሚያነሱት ጉዳይና ከሚናገሯቸው ቃላት መካከል አድማጩንም ግራ የሚያጋቡ ኾነው የሚገኙ በርካታ ሥህተቶችን ማዳመጥ አዲስ ነገር አይደለም:: እንደውም ከመደጋገሙ የተነሣ ለምደነው ታዝበን በዝምታ የምናልፋቸው ብዙ ትርጉም የሌላቸው ሃሳቦችንም እናዳምጣለን::

በእርግጥም ሙዚቃ ብቻ ሳትሆን የሰው ሥራ ውጤት ሁሉ ለትችት ተጋላጭ ነው:: አንድን የጥበብ ሥራ ለመውደድም ሆነ ለመጥላት፤ ለማወደስም ሆነ ለመንቀፍ አብላጫው ሰው ሥልጣን እንዳለው ይሠማዋል:: በተለይ ሙዚቃ ደግሞ ጊዜና ቦታ ማመቻቸት ሳይጠበቅብን የሰርክ ሕይወታችን ጋር አብራን በመኖሯ በማንኛውም ሙያ ውስጥ የሚገኝ ሁሉ ሙዚቃ ላይ ሃሳብ ከመሠንዘር ወደኋላ አይልም::

የማይገባ መድሃኒት ሰጥቶ ቆሞ ይሄድ የነበረን ሰው እስኪያበላሽና ይህም በግልጽ እስካልታወቀ የአንድ የጤና ባለሙያ ችሎታ የሕክምና ዕውቀት በሌላው ሰው ሊመዘንም ሊተችም አይችልም:: የመሐንዲሱ ግንባታ ያለጊዜው ሲፈራርስ ብቻ ነው የሙያ ብቃቱ ትዝብት ላይ የሚወድቀው:: ብዙዎቹ ሙያዎች ይህንን መሣይ ያለመገምገምና በማንም ደርሶ ያለመተቸት ዕድል አላቸው:: ግን የጥበብ ፈጠራ ሥራን ማን የማይተቸው አለ? ማንም ሰው የማንንም የስዕል ሥራ ከቀለም ምርጫው ጀምሮ እስከ ግድግዳ ላይ አሠቃቀሉ አፉን ሞልቶ ይናገራል:: ገጣሚው ከሚቀኝበት መድረክ እግር ጥሎት የደረሰ ሁሉ ግጥሙን ከርዕሱ ጀምሮ እስከ ሰውየው የድምጽ ቃናና አቋቋም ድረስ ያለ ሃይ ባይ ይጨረግዳል:: ይህን ጽሑፍ እንድጽፍ የገፋፋኝ ደግሞ በሙዚቃና በዘፈን ላይ እጅግ የከፋው ጭርገዳ ነው::

በማንኛውም የጥበብ ውጤት ዙሪያ ማንኛውም አድማጭ ወይም ተመልካች የፈለገውን የማለት፣ መርጦም የመውደድ እና የመጥላት መብቱ ፍጹም የተጠበቀ ነው:: ቢሆንም እጅግ ግራ ያጋባን ጉዳይ፤ በጨዋታ የሚነሱ ጉዳዮችንና ነፃ የሀሳብ ስንዘራዎች ሳይቀሩ ወደ መገናኛ ብዙኃን ያለምንም ሐፍረት ይዞ አየር ላይ መውጣቱ ነው:: ልክ ያልሆኑ፤ ያልተፈጠሩ እና የሌሉ ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው ተደጋግመው ይነሣሉ:: የትኛው ጥሩ የጥኛው መጥፎ እንደሆኑ በቅጡ በማያስረዱን ሰዎች፣ ሙዚቃን ከማስጨፈሪያነት ያለፈ ሚና እንደሌላት በሚሰማቸው አቅራቢዎች ትንተናዎች ይቀርቡልናል::

ከላይ ላነሣነው ጉዳይ እንደምሣሌ አንድን ሃሣብ እንድንመለከተው ወድጃለሁ:: በርካታ የሀገራችን የመገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞች "የሀገራችን የሙዚቃ ኢንዱስትሪ" የሚለውን ሐረግ በየመሃሉ ያነሣሉ:: ከሱም አልፎ "የሀገራችን የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ወደቀ፣ ተነሣ" ይላሉ:: ለሁሉም አድማጭ ተደጋግሞ የተነገረው ዕውነት የመሠለ ውሸት ነው::

በሀገራችን የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ብሎ ነገር የለም:: ሙዚቃና ሙዚቀኝነት የግለሠቦች ጉዳይ እና በግለሰቦች ጥረት እየተካሄደ ያለ የጥበብ ሥራ መሥክ እንጂ፣ የተቋም ወይም የተደራጀ ማዕከል የሚያከናውነው ባለመሆኑ ግለሠብን እንጂ ሀገርን የሚወክል የኢትዮጵያ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ብሎ የሚያስጠራበት ምንም ዓይነት መሠረት የለም::

አንድ የሙዚቃ አልበም በምን ዓይነት ጥራት መቀረጹ፤ በምንም ያህል ኮፒ መሸጡ ወይም አለመሸጡ የተወሰኑ አካላትን አትራፊ ሊያደርግ ወይም ኪሣራ ላይ ሊጥል ይችል ይሆናል እንጂ፤ አሁን ባለንበት ሁኔታ ቅንጣት ያህል ከኢትዮጵያ የሙዚቃ ዕድገት የሚቆጠር አለመሆኑ የሚታይ ሐቅ ነው::

ሥለ አንዲት ሀገር የሙዚቃ ዕድገት ወይም ውድቀት ለማውራት በመጀመሪያ ይህንኑ ጉዳይ "ጉዳዬ" ብሎ የያዘ ማዕከል ሊኖር የሚገባ ሲሆን፤ መነሻውም የሙዚቃ ኢንዱስትሪን መገንባት ሊሆን ይገባል:: ይህም ማለት ልክ በሌላ የሙያ ዘርፍ ውስጥ እንዳሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሁሉ ተመሣሣይ ጭብጥ ያለው ተቋም ማለት ነው:: የሙዚቃ ባለሙያዎችም ሆነ በሙዚቃ ነክ የንግድ ዘርፍ ውስጥ ለመሥራት የሚፈልጉ ነጋዴዎች ሙዚቃ ሁነኛ የሥኬት መንገድ እንደሆነ በሙዚቃ ኢንዱስትሪያቸው አማካኝነት በዓለም ላይ ከገነኑና ከፍተኛ የገንዘብ ዓቅምን ከገነቡት እንደ አሜሪካ፣ ጃፓን፣ ጀርመን ከመሣሠሉት ሀገራት መረዳት ይችላሉ::

በአሁኑ ወቅት እጅግ ለቁጥር የሚያዳግቱ ነጠላ ዜማዎችና ክሊፖች፤ አልፎ አልፎም አልበሞች በተለያዩ ግለሰቦች አማካኝነት ለገበያ ይውላሉ:: ግን በአመዛኙ ጥቂት በማይባል ወጪ ተሠርተው ማንንም ሳይጠቅሙ መና ሲቀሩ እንታዘባለን፤ በገንዘብም በአስተሳሰብም ማለቴ ነው:: ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ ተጠያቂ ሊሆን የሚችል አካል ስለሌለ፤ ስለማይቻልም ሁላችንም "እንደው እኮ... እንዲህ ቢሆን..." በማለት እያጉረመረምን በዘበት ስናልፈው ኖረናል እንጂ ይህን ታላቅ ሙያና መስክ ወደ ትልቅ ኢንዱስትሪ ለመለወጥ ዕድሎች እንዳሉን እንኳ ተገንዝበን የበኩላችንን ሚና ስንወጣ አንታይም::

በተለይ ጥቂት የማይባለው ሙያተኛ በአንዲት ነጠላ ዜማ እና አልበም ካገር አገር እየዞሩ ዕውቅናና ገንዘብ ከማሳደድ፣ አድማጭና ተመልካችን ከማስጨፈር አለፍ ያለ ቁም ነገር የመስራት ዓቅምና ፍላጎት አይታይበትም:: ይልቅ ከባለ ገንዘቡ ጋር የተጣመረ አሠራርን በመዘርጋት ሳይኖረን ለዘመናት ብዙ የተባለለትን "የሙዚቃ ኢንዱስትሪ"ን ለመገንባት መወያየት፣ ጥናት ማካሄድ፣ በዕውቀትና ችሎታ መመራት፣ በገንዘብ፣ በሰው ኃይል፣ በሲስተም ተደራጅቶ መስመሩን መያዝ የሚበጅና የሚያዛልቅ ይሆናል:: ያኔ ስለ ሙዚቃ ኢንዱስትሪው መውደቅ መነሳት ለማውራት ይቻለናል:: ግን መገናኛ ብዙኃን በባዶ የገነቡትን የኢትዮጵያን የሙዚቃ ኢንዱስትሪ መገንባት እንዴት ይቻላል?

የሙዚቃ ኢንዱስትሪን መገንባት ቀላል ነገር ባይሆንም፤ "ተገቢዎቹ ሰዎች" ከተጣመሩ ግን የሚቻል ነገር ነው:: በዓለም ዓቀፉ ደረጃ ላይ የተቀመጡ የተለያዩ ሀገራት የሙዚቃ ኢንዱስትሪ አሠራርና አደረጃጀት እስኪ ምን እንደሚመስል ጠቅለል አድርገን እንይላቸው::

በኢንዱስትሪው በበለጸጉት ሀገራት ያሉ ሙያተኞች በየዘውጉ እና ሥልቱ የሚሰሩ የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪ በመሆን ይሰራሉ:: የሙዚቃ ደራሲያኑ ሥራዎቻቸውን በትክክል ለሚስማማው ዘፋኝ ይሰጣሉ:: ይህም ሲሆን የዘፋኙ የድምጽ ቃና እና ብቃት ከግምት ውስጥ ስለሚገባ፤ ድምጻዊው ከዓቅሙ በላይም በታችም ያልሆነ ሥራን እንዲያገኝ ይረዳዋል:: ሙዚቃውም የመወደድ ዓቅሙ ይጨምራል:: የሙዚቃ መሣሪያ ጨዋታውም ላይ ተመሳሳይ አሠራር አለው::

ሌላው አንድ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ከሚያከናውናቸው ሥራዎች መሃከል አልበሞችን መቅረጽ፣ ማሳተም፣ ማከፋፈል ሲሆን በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ደግሞ የበርካታ ሙያ ባለቤቶች ተሳታፊ ይሆናሉ:: የሽያጭ ወኪሎች፣ ፕሮሞተሮች፣ የህግ ባለሙያ እና ሌሎችም በርካታ ሙያተኞች ሚናቸው ከፍ ያለ ሆኖ ይገኛል:: እጅግ ከፍተኛ ገቢን ለሀገርም ለተቋምም ለግለሰብም ማስገኘት የሚያሥችለው ግን ኮንሠርት ነው::

በአጠቃላይ የሙዚቃ ኢንዱስትሪው ሙዚቃን አምራች፤ አዳዲስ ስራዎችን አቅራቢ የሆነ ለበርካታ ሙያተኞች እና በግልጽ በታወቀ ሥያሜ የሚጠራ ተቋም እንጂ እንዲያው በምናብ የተሣለ ሃሳብ ባለመሆኑ "የሀገራችን የሙዚቃ ኢንዱስትሪ" የምንላትን አባባል ወዲያ መጣል እና እንዴት መሆን እንደሚችል ማሠብ የመጀመሪያው እርምጃችን መሆን ይኖርበታል::

ቀደም ባለው የሀገራችን የሙዚቃ ታሪክ ላይ የኢትዮጵያ ሙዚቃም ሆነ ሙዚቀኞች ላይ የባለቤትነት ሥሜት የነበራቸው ተቋማት እንደነበሩ ይታወሣል:: ከሀገር ፍቅር ማኅበር በኋላም ቴአትር ቤት ከሆነው ጀምሮ በሌሎችም ቴአትር ቤቶች እንዲሁም የክቡር ዘበኛ፣ የፖሊስ ኦርኬስትራዎችና መሰሎችን ብናስታውስ በቋሚ ተቀጣሪ ሙዚቀኞችና አስተዳዳሪዎች የሚመራ ሀገርም መንግሥትም የኔ የሚለው ዓይነት የሙዚቃ ማዕከል የነበረን ቢሆንም ሁሉም ደግሞ በተለያዩ የአስተዳዳር ባሕሪይ ሥር እና በፉክክር ሥሜት እንጂ "ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ዕድገት" በሚል አካሄድ ሥላልተቃኙ የተናጠል ሥራዎቻቸው ላይ አተኩረው ሠርተዋል::

ከእነዚህ የተቋማት የሙዚቃ እንቅስቃሴ በኋላም ባለቀያይ መብራቶች የምሽት ክበቦች እና የግል ባንዶች ትንሽም ብትሆን የነበረችውን የሙዚቀኞችን የሙሉ ጊዜ የጋራ ሥራ ሙሉ በሙሉ አክሽፎት ወደ ግል እንቅስቃሴ እንዲያመራ አድርጎታል::

በጋራ የመሥራት ጥበባችንን ሳንጠቀምበት ወደ ግል ያደላ ሥራዎች ላይ ማድላታችን አንድ ወጥ የሆነ የሙዚቃ መለያ ቀለም ሣይኖረን ያለንንም ዓቅም በምንችለው ያህል ሳንጠቀም እንድንቆይ አድርጎናል:: በመሆኑም ልክ እንደ ሌሎቹ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ወይም የቴክኒክና ሙያ አገልግሎት ሰጪ ወይም ምርት አምራች ድርጅቶች ሁሉ በዕውቀትና በችሎታ የተዋቀረ እና በባለሙያዎች የጋራ ሥራ የተደራጀ የሙዚቃ

# «ወደ ከፍታ ለመድረስ የጀመርኩት ጉዞ አይቆምም!»

## አባይነሽ ጀምበር



ጊዜው የሰው ልጅ ህይወት ዋጋ የረከሰበት፣ ገዳይ የገደለውን ወገኑን ተኩሶ የመታበትን የጥይት ዋጋ እንዲከፈለው የሚጠይቅበት፣ ኢትዮጵያ እንደ አገር ወደ "ቦኪም"ነት ተቀይራ ማልቀሻ ምድር የሆነችበት፤ የቀይ ሽብር ወቅት ነበር፡፡

አባትና እናቷ ታላቅ ወንድምዋን ይዘው ህይወታቸውን ለማትረፍ የሞቀ ቤታቸውን በር መለስ አድርገው ሳይዘጉ ወደ ሱዳን ተሰደዱ፡፡ ዛሬ "ወደ ከፍታው ለመድረስ የጀመርኩት ጉዞ አይቆምም!" የምትለው አባይነሽ ሱዳን ስደተኛ ካምፕ ውስጥ ነበር የተወለደችው፡፡

አባይነሽን ለመውለድ ምጥ የያዛት ሚስቱን የህክምና ትምህርት የተማረው ባልዋ (የህፃንዋ አባት) ራሱ ነበር ያዋለዳት፡፡ በታላቁ የአባይ ወንዝ ዳርቻ ካለ የሱዳን ስደተኛ ካምፕ ውስጥ ሁለት አመት በእንክብካቤ የቆየችው አባይነሽ ጀምበርና ቤተሰቦቿ ወደ አሜሪካ የመጓዝና በስደተኝነት የመኖር እድል አጋጥሟቸው ወደ ስፍራው አቀኑ፡፡

"ኢትዮጵያዊ መልኩን፤ ነብር ዥንጉርጉርነቱን አይቀይርም" እንደሚባለው ወላጆች በስደተኛ ካምፕ ውስጥ የተወለደችው ልጃቸው አባይነሽን ስለኢትዮጵያ ታሪክ፣ ባህልና ወግ፣ ስለ ህዝቦችዋ ገናና ታሪክ እያስጠኑ ነበር ያሳደጓት፡፡ እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ በሲያትል በሚገኝ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትዋን ተከታትላ ያጠናቀቀችው አባይነሽ፤ ወላጆችዋ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ስለአገርዋ የነገሯት ታሪክ በህፃንነት አዕምሮዋ ታትሞ ዛሬ ድረስ ትዝ ይላታል፡፡

አባይነሽ ዛሬ ላይ ሆና ለደረሰችበት ስኬት እንድትበቃ ገና ከህፃንነቷ ጀምሮ የወላጆችዋ ሚና ከፍተኛ እንደነበር ትናገራለች፡፡ "…እናቴ፣ ቤተሰባችን ከሱዳን የስደተኛ ካምፕ ወደ አሜሪካ ሲገባ ፈፅሞ እንግሊዘኛ መናገርም ሆነ መስማት አትችልም ነበር፡፡ አባቴም የህክምና ትምህርቱን አጠናቆ ለመመረቅ ሰንቆት የነበረውን ዓላማ በመተው ጥድፊያ በሞላው የአሜሪካ ኑሮ ህይወት ውስጥ ቤተሰቡን፤ በተለይም ሁለት ልጆቹን የተሻለ ደረጃ ላይ እንድንገኝ ያገኘውን እየሰራ ነው ያሳደገኝ፡፡…

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቅቄ የከፍተኛ ትምህርት ለመማር ስበቃ የወሰንኩት ውሳኔ፤ የእጅ ስራ ሙያ ተሰጥኦ ስላለኝ፤ በፊላደልፊያ በሚገኘው ዌርክሲል ዩኒቨርሲቲ በመገባት በፋሽን ዲዛይንና ጌጣ ጌጦች የተለያዩ አልባሳትን ለገበያ ለማቅረብ የሚያስችል የትምህርት ዘርፍን መርጬ የከፍተኛ ትምህርቴን ተከታትዬ አጠናቀቅሁና ወደ ኒው ዮርክ አመራሁ፡፡

…ሆኖም በዚያ ከሚገኙ በአለም አቀፍ ደረጃ ስማቸው ከገነነ የፋሽን ኢንዳስትሪዎች ውስጥ ለመቀላቀል ያለው ሂደት ግን ቀላል አልነበረም፡፡ ከልጅነቴ ጀምሮ በውስጤ ያለው አይበገሬነት ረድቶኝ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በአንድ የመነፅር አምራች ካምፓኒ ውስጥ ረዳት የምርት ሂደት ተቆጣጣሪ ሆኜ ተቀጠርኩ፡፡…

በስራዬ ብዙ ልምድ አካበትኩኝ፡፡ በመቀጠል ወደሌላ ታዋቂ የመነፅር አምራች ኩባንያ ስራዬን በመቀየር የሲኒየር ፕሮዳክት ማኔጀሩ ላይሰንስድ ብራንድ ማናጀር ሆኜ በጥሩ ክፍያና ላቅ ያለ ሃላፊነት ተሰጥቶኝ ነው የተቀጠርኩት፡፡ በአጠቃላይ ለሰባት ዓመታት በሁለቱ የመነፅር ፋብሪካዎች በተለያዩ ሃላፊነቶች ስሰራ ስለ መነፅር ማምረት፤ እንዲሁም ገበያና በተፈላጊነት ዙሪያ በቂ እውቀትን አካበትኩኝ፡፡

በተጨማሪም፤ በሰባት ዓመት ቆይታዬ ኢንዱስትሪው የሚያስፈልገውን ሁሉ እንዳውቅ ያደረገኝ የትምህርት ጊዜም ሆኖ ለእኔ ጠቅሞኛል፡፡ ለዚህም ይመስለኛል የራሴ የሆነ የመነፅር ማምረትና ለገበያ የማቅረብ ስራ ለመጀመር የወሰንኩት፡፡ እናም ለአንድ አመት ከስድስት ወር ቅደመ ዝግጅት ሳደርግ ከቆየሁ በኋላ ከዛሬ 3 አመት በፊት "ጀምበር አይ ዌር" የተባለውን ኩባንያ ከፈትኩኝ…" ትላለች የ36 አመትዋ አባይነሽ ጀምበር፡፡

"…ፀሐይ ሁልጊዜም እንደምትወጣ ሁሉ ሰዎችም ለአይኖቻቸው መነፅር ማድረግ አያቆሙም፡፡ ስለዚህ የጀምበር መነፅር ስራ የወደፊት እቅድ ከዚህ እስከዚያ ነው የሚል መድረሻ የለውም፡፡ ወደ ከፍታው ለመድረስ የጀመርኩት ጉዞ አይቆምም!" ትላለች የወደፊቱ ራዕይሽ ምንድን ነው ተብላ ስትጠየቅ፡፡

ዛሬ የአባይነሽ ጀምበር የፈጠራ አሻራዎች ያረፈባቸውና የእርሷ ኩባንያ ያመረታቸው መነፅሮች ከኒው ዮርክ አንስቶ ችካጎ እና በቅርቡ የአውሮፓ ገበያ ውስጥ በስፋት መግባት ጀምረዋል፡፡

የጀምበር አይ. ዌር ምርቶች ኢትዮጵያዊ አሻራ እንዲኖራቸው በማድረግ ከመነፅር መያዥያው ፓኮ እንዲሁም በመነፅሩ ፍሬም ላይ ኢትዮጵያዊ ቅርፃ ቅርፆችን የሚያሳዩ ወርቃማ ጌጣጌጦች እንዲሁም የሌንሱ መጥረጊያ ጨርቅ ሳይቀር በኢትዮጵያ የተመረተና በኢትዮጵያ ሸማኔዎች የተሸመነ ጨርቅ የተለበጠ ነው፡፡

"…ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ የኢትዮጵያዊያንን ዘመናት ያስቆጠረ ጥበብ በአለም አቀፍ ደረጃ ማስተዋወቅ ሌላው ተግባሬ ነው፡፡" የምትለው አባይነሽ ከዓመታት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በማቅናት የተለያዩ አካባቢዎችን ጎብኝታለች፡፡

የጀምበር አይ. ዌር መስራችና ስራ አስኪያጅ የሆነችው አባይነሽ ጀምበር ለስኬት የበቃችበት መንገድ ቀላልና ምቹ እንዳልነበር፤ ይልቁንም ፈታኝ ችግሮችን ማለፍዋን ስትናገር "…ብዙ ተስፋ የሚያስቆርጡ ነገሮች ሲገጥሙኝ በድፍረትና በቆራጥነት በመቋቋም እጋፈጣለሁ፡፡ ደግሞም የሚያስደስተኝን ነገር ለማግኘት ያለ እረፍት እሰራለሁ፡፡ …ወደፊት ለመሄድና ያሰብክበት ለመድረስ በምታደርገው ትግል ልትወድቅና ሊታክትህ ይችላል፡፡ ዋናው ነገር ከውድቀት ተምረህ በመነሳት ወደፊት መንቀሳቀስህ እንጂ ሌላው ነገር አያገባህም፡፡ ወድቆ ተነስቶ ያሰቡበት መድረስ ትልቁ የህይወትህ ስኬት መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው፡፡…" ትላለች፡፡

በታዋቂዎቹ የአፍሮ አሜሪካውያን የፋሽንና የፊልም ኢንዱስትሪዎች ዙሪያ በሚያተኩረው የኢቦኒ እና ሌሎችም ታዋቂ መፅሔቶች ስለ ስኬትዋ፣ ለገበያ ስለምታበቃቸው መነፅሮች ሰፊ ዘገባ ባቀረቡ ጋዜጦችና መፅሔቶች ለወጣቶች ምን ትመክሪያለሽ? ተብላ ለቀረበላት ጥያቄ አባይነሽ ጀምበር የሰጠችው ምላሽ "ሁልጊዜም ማለዳ ላይ ስትነሱ ወደምታስቡት ስኬትና ከምኞታችሁ መጨረሻ ለመድረስ የሚያስችላችሁ ፅናትና ጥንካሬ ኖሯችሁ ተንቀሳቀሱ፤ ያን ጊዜ ይሳካላችኋል፡፡" ብላለች፡፡

Flintstone Homes for you®

Leading by example




Call: 8188
Click: www.flintstonehomes.com
Addis Ababa,Ethiopia